


## ከሕይወት የሚበልጥ ዓላማ የለም

በእውቀቱ ስዩም
(ደራሲና ገጣሚ) 7



## ጦማረ አሚን

ገጣሚ
ኤፍሬም ስዩም

11

## ትራንስፎርሜሽን ምን ማለት ነው? ማን ገብቶታል?



ፕሮፌሰር መስፍን
ወ/ማርያም 3

ቅፅ 5 ቁጥር 187 አርብ ግንቦት 3 2004 ዓ.ም www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia ዋጋ 7.00 ብር




# የመጅሊስ አመራሮች በቅርቡ ሥልጣናቸውን ሊያስረክቡ ነው

### * የምርጫው አፈፃፀም ስጋት ፈጥሯል ተባለ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት /መጅሊስ/ አመራሮች ሥልጣናቸውን በምርጫ ለሚተካው አዲስ ምክር ቤት ለማስረከብ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ጋር ባለፈው ሃሙስ መግባባት ላይ መድረሳቸውን የፍትህ ምንጮች አስታወቁ:: ለመጅሊስ አመራሮች የመንግስትን ውሳኔ ያሳወቋቸው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያም እና የጠ/ሚ መለስ አማካሪ አቶ ፀጋዬ በርሔ ናቸው ተብሏል::

በመጪው ሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ የምርጫው ዝግጅት እንደሚጀመር የነገሩን ምንጮቻችን በሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ በቀበሌ እና በወረዳ ለመተግበር መርሃ-ግብር የወጣለት ሲሆን ምርጫውን የኡላማዎች ምክር ቤት እንዲያካሂደው፣ በምርጫው ላይ መሳተፍና መታዘብ የሚችለው የነባሩ እስልምና ተከታይ ብቻ መሆን እንዳለበት እና የአወሊያ እስልምና ኮሌጅም በአዲሱ መጅሊስ ሥር እንዲተዳደር በመጅሊስና በፌዴራል ጉዳዮች ሚንስትር ተወስኗል ብለውናል::

በዚህ በመጅሊስ የመጨረሻው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተሳተፉ የአዲስ አበባ እና የኦሮሚያ ክልል መጅሊስ አመራሮች ምርጫው በመንግስት መዋቅር በቀበሌ ሳይሆን መካሄድ ያለበት በመስጂድ ሊሆን ይገባል፤ በቀበሌ መካሄዱ ሕዝበ ሙስሊሙ የማይፈልጋቸው ካድሬዎች በቀላሉ ሊሰርጉበት ይችላሉ፤ ምርጫውንም በበላይነት መቆጣጠር ያለበት በሚፈርሰው መጅሊስ ሥር የሚተዳደረው የህዝበ ሙስሊሙ ድጋፍ የሌለው የኡላማዎች ምክር ቤት ሳይሆን

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# 21 የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንደታሰሩ ይገኛሉ

### አንድ ተማሪ በጥይት ቆስሏል፣ በከባድ ሁኔታ የተደበደቡ ተማሪዎች በርካታ ናቸው

‹‹በርካታ ፖሊሶች በዩኒቨርስቲው ግቢና ውጪ በመኖራቸው በነፃነት መንቀሳቀስ አልቻልንም›› /ተማሪዎች/

**አቡነ ጳውሎስ የሲኖዶስ ውሳኔን በመጣስ የልማት ኮሚሽኑን ሊቀጳጳስ አቡነ ሳሙኤልን ከቼክ ፈራሚነት ሰረዙ**
. ሲኖዶሱ በመነጋገሪያ አጀንዳዎች ላይ እየተወያየ ነው 15

**የ78 ዓመቱ አርሶ አደር በማዳበሪያ እዳ ራሳቸውን አጠፉ** 11

**ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ዓለም አቀፍ ሽልማት ተሸለመች** 11

**በመድረክ ከፍተኛ አመራር ላይ አራት የመከላከያ ምስክሮች ትናንት ተደመጡ**
. እነ እስክንድር ነጋ ዛሬ ለፍርድ ይቀርባሉ 15

**‹‹ከመቃብር ተመልሶ የመጣውን የሳንሱር መቀስ እንቃወማለን፤ ወደ መቃብሩ እንዲመለስ እንታገለዋለን››** 15

**ሲፒጄ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ያቀረበው ውል ቅድመ-ምርመራ ነው ሲል ተቃወመ** 11

# የእርዳታ እና የችጋር ፖለቲካ



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

በ1990ዎቹ መጨረሻ ከዚህ ቀደም የሥርዓቱ ወዳጅ ሀገራት ተብለው የሚጠሩት ምዕራባውያን የ1997ቱን የምርጫ ውጤት አስመልክቶ የወሰዱት መረዳት ይሰጡት በነበረው ዕርዳታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን ፈጥሮ አልፏል፡፡ በዚህም ቀጥተኛ የባጀት ድጋፍ ከማድረግ ይልቅ የሚያደርጓቸውን እርዳታዎች በቀጥታ ወደሚደግፏቸው ፕሮጀክቶች ለማዞር ሞክረዋል፡፡ ይህ ሙከራቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚመጣውን ዕርዳታ ኢህአዴግ ለፖለቲካዊ አፈና ይጠቀምበታል በሚል በተለያዩ ተቋማት የሚቀርብበትን ክስ ለማረም የተደረገ መሆኑን አንዳንድ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ ሄለን ኢፒሲቲን "Cruel Ethiopia" በሚል ርዕስ በኒውዮርክ ጋዜጣ ላይ ባሳተመችው መጣጥፍ ኢህአዴግ የአለም ባንክን ዕርዳታ ተቃዋሚዎችን ይደግፋሉ ብሎ የሚጠረጥራቸውን መምህራንን ጨምሮ ሌሎች ሲቪል ሰራተኞችን ለመቅጣት ይጠቀምበታል ስትል ትከሳለች፡፡ ይህን የተረዳው የሚመስለው የአለም ባንክም "Ethiopia: country brief" በሚለው የባለፈው ዓመት ዘገባው ከ97 ወዲህ የተደረጉት የምርጫ ውጤቶች የዴሞክራሲ ሽግግሩን እንዳቃወሱት ተናግሯል፡፡ የአቶ መለስን ስርዓት በሰብዓዊ መብት ጥሰት በተደጋጋሚ የሚከሰው ሂውማን ራይትስ ዎች "Development with out freedom: How Aid underwrites Repression in Ethiopia" ብሎ በሰየመው ጥናቱ የእርዳታ እህሎች፣ አነስተኛና ጥቃቅን ብድሮች እንዲሁም የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን ሥርዓቱ ለደጋፊዎቹ ብቻ በማቅረብ የምዕራባውያኑ እርዳታ ለፖለቲካዊ ጠቀሜታ እንደሚውል በዝርዝር አትቷል፡፡ የእነዚህ እና የሌሎች ተቋማትና ሀገራት ክሶች ገዢውን ፓርቲ ወደ ቻይና እንዲያዘነብል እንዳደረገው የሚያነሱ ሌሎች ፀሐፊዎች፤ ፓርቲው ለሚከሰስበት የፖለቲካ መብት ጥሰቶች ግድ የሌላት የምትመስለው ቻይና፤ እርዳታዎቿን እንደ ምዕራባውያኑ ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶችን መሰረት ከሚያደርጉ ቅድመ-ሁኔታዎች ያላቀቀች መሆኗ ለኢህአዴግ ማዘንበል ዋነኛው ግፊት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ በስፋት የፃፋቸው ክሪስቲያን ሃክኔሽ "Competing for development? The European union and China in Ethiopia" በሚለው ጥናታዊ ፅሁፉ ቻይና እና የአውሮፓ ህብረት በልማት ትርጓሜ፣ በእርዳታ አሰጣጥ ላይ እና እርዳታዎች ከምን ዓይነት ሌሎች የትብብር ዓይነቶች ጋር መተሳሰር እንዳለባቸው ያላቸው መሰረታዊ ልዩነት የፓርቲውን እና የቻይናን ግንኙነት እንደሚያብራራ አትታለች፡፡ እንደ ብዙ ፀሐፊዎች እምነት እነዚህን ጉዳዮች በከፊልም ቢሆን ለመረዳት እርዳታን በተመለከተ ኢህአዴግ በተለያዩ ወቅቶች የገጠመውን ማየት የተሻለ ይመስላል፡፡

## ሀሳብ አልባ ዓመታት

በአስራ ስድስት ዓመታት የትጥቅ ትግል ጊዜያት ኢትዮጵያ በአልባንያ አምሳያ መቅረፅ እንዳለባት ያምን የነበረው ኢህአዴግ የቀዝቃዛው ጦርነትን ማብቃት ተከትሎ ግራ-ዘመም ሀሳቦቹን ወደ ጎን መግፋት ጀመረ፡፡ ዶ/ር ደረጄ ፈይሳ እንደሚሉት ፓርቲው የምዕረባውያንን ድጋፍ ለማሰባሰብ ሲል የብሉይ ሊበራል ዕሴቶችን ያቀፈ የሽግግር ጊዜ ቻርተር ቀጥሎም የ1987ቱን ህገ-መንግስት አዘጋጅቷል፡፡ ምዕራባውያኑ በእነዚህ የፓርቲው ሙከራዎች የተሻለ ቢነቃቁም በዚህ ወቅት ኢህአዴግ በእርዳታ ሰጪዎቹ ሀገራት ተፅዕኖ ስር እንዲወድቅ ያደረጉት ሁለት ሁነቶች እንደነበሩ ዶ/ር ደረጄ "Aid negotiation; the uneasy " partner ship" between EPRDF and the donors" በሚለው ጣናታዊ ፅሁፋቸው ይጠቅሳሉ፡፡ የመጀመሪያው በወቅቱ ከሁለት የፖለቲካ ሀይሎች በኩል ይደርስበት የነበረው ጫና ፖለቲካዊ ቅቡልነቱን ማሳሳቱ ነው፡፡ በኤርትራ መገንጠል እና በዘውግ ፖለቲካ መጦዝ ያልተስማሙ ፖለቲካዊ ስብስቦች በአንዱ ጫፍ፤ መገንጠልን አልያም የተሻለ የብሄር ውክልናን የሚፈልጉ ዘውጊ ብሄርተኞች በሌላ በኩል ኢህአዴግን በከፍተኛ ብርታት መሞገታቸው መንግስታዊ ስልጣኑ እንዳይረጋጋ አድርጎታል፡፡ በዘመኑ ለነበረው የምዕራባውያኑ ተፅዕኖ ተጋላጭነት ሁለተኛው ተለዋጭ በጊዜው ፓርቲው ይሄ ነው የሚባል አንድ ወጥ ርዕዮተ ዓለም ያልነበረው መሆኑ ነበር፡፡ ጆን ያንግ እና መድህኔ ታደሰ "TPLF: Reform of decline?" በሚል ርዕስ ሪቪው ኦፍ አፍሪካን ፖለቲካል ኢኮኖሚ ጆርናል ላይ ባሳተሙት ጥናት እንደሚያወሱት ኢህአዴግ ከትግሉ ወቅት ጀምሮ ይዞ የመጣውን አብዮታዊ ዴሞክራሲን መሰረት ያደረገ የልማታዊ መንግስትነት ሀቲት ይዞ የቀረበው ከ1993ቱ የህወሓት መፈርከስ በኋላ ነበር፡፡ ‹‹እስከዚህ ወቅት ድረስ ቅርፅ ያለው ርዕዮተ እንዳልነበረው ፓርቲው ራሱ ያምናል›› ይላሉ እነ ጆን ያንግ፡፡ በእነዚህ ሁለት ተመጋጋቢ ምክንያቶች እና በተለይም አሜሪካ በድህረ-ደርግ ኢትዮጵያ እንዲኖራት ካቀደችው የበላይነት ግብ የተነሳ ኢህአዴግ አሁን አሁን በይፋ እስከመዘለፍ የደፈራቸውን አለም አቀፎቹን የፋይናንስ ተቋማት ያቀረቡትን የመዋቅራዊ ማሻሻያ ፕሮግራም /SAP/ ካለምንም ማንገራገር ተቀበለ፡፡ የብርን የገበያ ዋጋ ማሳነስ፣ የህዝባዊ ድርጅቶችን ወደ ግል ማዛወር፣ የንግድ ስርዓቱ በከፊልም ቢሆን ከመንግስት ተፅዕኖ መላቀቅ እና የግል የኢኮኖሚ ዘርፍ እንቅስቃሴ መጀመር የፕሮግራሙ ተግባራዊ ውጤቶች ነበሩ፡፡ ፕ/ር ማሪያን አታዌይ እንደሚጠቅሱት የተቀናቃኝ ፓርቲዎች መበራከት ፓርቲው በጊዜው ያገኝ ለነበረው እርዳታና ድጋፍ ከተጠቀሱት የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ሌላ ተጨማሪ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ‹‹እነዚህ ሁነቶች›› ይላሉ ፕ/ር ኦታዌይ "The Ethiopian Transition democratization or new authoritarianism?" በሚለው ፅሁፋቸው ‹‹አቶ መለስም ሆነ ስርዓታቸውን እንደ ሽግግር ፖለቲካ ስርዓትነት እንዲቆጠሩ አስችሏቸዋል፡፡›› ዶ/ር ደረጄ በበኩላቸው በነዚህ የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ዓመታት የነበረውን የእርዳታ ፖለቲካ የረጂዎች ፍላጎት ብቻ የተፈፀመባቸው እንደነበሩ ይናገራሉ፡፡

## ድህነትና ሽብርተኝነት

እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ድርስ የተሞከረው መዋቅራዊ የማሻሻያ ፕሮግራም በውድቅት መጠናቀቁ በራሳቸው በእቅዱ አፍላቂዎች በታመነ ማግስት በአፍሪካውያኑ እና በእርዳታ አድራጊዎቻቸው መሀከል ያለውን ግንኙነት የሚበይን ሌላ እቅድ ብቅ አለ፡- ዛክ ዊልያምስ እና ሂልስ ሞሸን የተባሉ አጥኚዎች "Africa: from SAP to PRSP" በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚሉት የመዋቅራዊ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ደሀ ሀገራት በአለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ወደ ጥግ እንዲገፉ በማድረጉ እ.ኤ.አ. በ2015 ድህነት ከአለም ላይ ማጥፋትን ግቡ ያደረገውን የሚሊንየሙ የልማት ገቦች መቀረፅ መሰረት የሆነውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ /PRSP/ አዲሱ የእርዳታ ፖለቲካው ማዕከል ሆነ፡፡ ፀሐፊዎቹ እንደሚሉት ይህ ዕቅድ እንደቀድመው ፕሮግራም ለምዕራባውያኑ በግልፅ የተፅእኖ ፈጣሪነት ዕድል ባይሰጥም ለእቅዱ ግብ መሳካት በሚል በየሀገሩ የሚተገበሩትን ታላላቅ የልማት ዕቅዶች የመወሰን እና የመፈፀም አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል፡፡ ራሱን በዚህ አውድ ውስጥ ያገኘው ኢህአዴግ ከዚህ የተቋማቱ ሙግቶች ጋር በሚዛመድ መልኩ የልማታዊ መንግስትነቱን ቀዳሚ ግብ ‹‹ድህነትን ተረት ለማድረግ›› በሚል በመቃኘቱ ከእርዳታ ሰጪዎቹ ጋር የነበረው ግንኙነት ሀገሪቱን ወደ ሚሊኒየሙ ግብ በመግፋት የተወሰነ ነበር ይላሉ ዶ/ር ደረጄ ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው፡፡

ሶስተኛው ተጠቃሽ ምክንያት የሽብርተኝነትን መጎልበት ተከትሎ የምዕራብ ሀገራት የአፍሪካ ቀንድን በተመለከተ የነበራቸውን ዕይታ መቀየራቸው ነው፡፡ አልቃይዳን እና ቢን ላደንን በማስጠለሏ ትከሰስ ከነበረችው ሱዳን መታየት የጀመረው የእስልምና ፅንፈኝነት አልፎም በናይሮቢ እና በዳሬ ሰላም የአሜሪካ ኢምባሲዎች ከደረሰው ጥቃት በመነሳት አሜሪካ አንድ ወሳኝ የውጭ ጉዳይ ስትራቴጂ ቀየሰች፡፡ ኤድምንድ ኬለር እና ሩት ኢዮብ "The Horn of Africa; the us and security challenges" በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚከራከሩት አሜሪካ ሱዳንን በስትራቴጂካዊ ከበባ ውስጥ ለማስቀመጥ በማሰቧ ‹‹ከፊት የሚቆሙ መንግስታት›› /Front line states/ በሚለው ዝርዝር ውስጥ ኢትዮጵያን አስገብታለች፡፡ እንደ እነ ኬለር ሙግት አሜሪካ የመስከረም 2001ን ጥቃት ተከትሎ የእርዳታ ፖሊሲዎቿን ለፀረ-ሽብርተኝነት ጦርነቷ ደጋፊነትን ወሳኝ መወሰኛ ማድረጓ እና በኢትዮጵያ መንግስት በኩል አሊታድን መሰል ድርጅቶችን ወደዚህ የምዕራባውያኑ ተባባሪ አገራት ለመቀላቀል እንደ ማሳመኛ መሸጋገሪያ መጠቀሟ አገሪቱ ‹‹መንጠልጠያ አገር›› (Anchor state) ተብላ እንድትሰየም ዳርጓታል፡፡ ከዚህ በመለስ ዶ/ር ደረጄ "Potential for and signs of religious radicalization in Ethiopia" በሚለው ሌላ ጥናታዊ ስራቸው አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ እየፋፋ የመጣውን ጠርዘኛ እስልምናዊ ተጋብሮት በመንተራስ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን በጥርጣሬ ማየቷ ለኢህአዴግ ጥቅም ተኮር የመደራደሪያ አቅም ሰጥቶታል፡፡ ይህ ሽብርተኝነት ክስተት ምዕራባውያኑ እርዳታን በተመለከተ ያላቸው ዕይታ ድህነትን፣ የመንግስትነት ውድቀትን እና የሃይማኖት ፅንፈኝነትን ያካተተ አዲስ የእርዳታ ተዋስኦ እንዲኖራቸው ገፍቷል፡፡ በተለይ ‹‹የወደቁ መንግስታት›› (Failed states) በሚለው ተርታ ውስጥ ለማረፍ ኢትዮጵያ ጥቂት የቀራት መሆኗን እና ይኸም በርስ በእርስ ጦርነት ፖለቲካዊ ያለመረጋጋት በተጠናወተው የአፍሪካ ቀንድ ሌላ ሱማሊያ እንዳትፈጠር መስጋታቸውን የሚያመላክተው ‹‹ለተቋማት ግንባታ›› በሚል የሚሰጡት እርዳታዎች መብዛት በቂ ማሳያ ነው ይላሉ የነገሩ ተከታታዮች፡፡

## የግጭት መስመር?

በኢህአዴግ እና በምዕራባውያን መሀከል ያለውን የእርዳታ ፖለቲካ ያጠኑ ፀሐፊዎች እንደሚያሱት በተለያዩ ጊዜያት በፓርቲውና በሀገራቱ/ተቋማቱ መካከል የርዕዮተ-ዓለም ልዩነትን ሽፋን ያደረጉ ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን ተንተርሶ የተነሳው የኢህአዴግና የአይ.ኤም.ኤፍ ሰላም የማስፈን ቅድመ ሁኔታ ጉዳይ፣ በድህረ-97ቱ ምርጫ የተፈጠረው ንትርክ፣ ከረዥም ጊዜ እርዳታ ሰጪዋ ኖርዌይ ጋር የተከሰተው እሰጣገባ እና የግልገል ጊቤ ሦስትን ፕሮጀክት የአለም ባንክ እና ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት አንደገፍም ማለታቸው ተጠቃሽ ሁነቶች ናቸው፡፡ በቅርቡ የትራንስፎርሜሽኑን ዕቅድ ለማሳካት ወደ አራት መቶ ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ከሀገር ውስጥ እና ከባህር ማዶ ለመበደር ያቀደው ኢህአዴግ፤ በዚህ ግዙፍ ተበዳሪነቱም የተነሳ በአምስቱ ዓመት የሚፈጠረውን የፊስካል ጉድለት ለመሙላት 75.4 ሚሊዮን ብር መፈለጉ የፓርቲውን ‹‹ወዳጅ›› ተቋማትና መንግስታት አስቆጥቷል፡፡ እኚህን መሰል ግጭቶችን አንዳንድ ተንታኞች የርዕዮተ-ዓለም ልባስ ይሰጧቸዋል፡፡ የልዩነቱንም መሰረት ፓርቲው ከመረጠው ‹‹የልማታዊ መንግስት›› ሀቲት እና ከኒዮ-ሊበራሊዝም ሙግት አንፃር ሊታይ እንደማይችል ያነሳሉ፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት የተከሰተውን የአለም አቀፉን የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እንደ ኒዮ-ሊበራሊዝም ውድቀት የሚያየው ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ የሚንጠለጠለውን ልማታዊ መንግስትነት ለምዕራባውያን ሀገራት ጭምር ለተሻለ እንደሚሆን እስከመሞከር ድረስ ሄዷል፡፡ አቶ መለስ በ4ኛው የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮንፈረንስ ላይም ‹‹ኒዮ-ሊበራሊዝም መልካም ድምዳሜዎች እንደማይኖሩት እናውቃለን፡፡ በተስተካከለ ጅማሮ በጎ ውጤቶች ካላመጣ በኮረኮንቻማ መንገድ ተጉዘን ሰናይ ግቦችን መጠበቅ ዕብደት ነው›› ሲሉ የምዕራባውያኑ ለኒዮ-ሊበራሊዝም ተተግባሪነት የተሻለ የማህበረ-ፖለቲካ ድልድል መኖራቸው የደረሰባቸውን የኢኮኖሚ ክስረት፣ በተበላሸ የፖለቲካ ስርዓት ላይ ‹‹እንድንሞክረው እየተገደድን ነው›› የሚሉት ርዕዮተ-ዓለም ከሚያመጣው ‹‹ችግር›› ጋር አነፅረዋል፡፡

በኢህአዴግ እና በእርዳታ ሰጪ ሀገራትና ተቋማት መሀከል አለ የሚባለው የርዕዮተ-ዓለም የልዩነት መሰረት ግልፅ ነው፡፡ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ጣልቃ ገብነት የተመጠነ መሆን፣ የኢኮኖሚው አውታሮች በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ መያዝ አልፎም የግለሰብ ነፃነት የፖለቲካ ስርዓቱ ማዕከል መሆን በሀገራቱ የሚቀነቀኑ የሊበራል ዕሴቶች ናቸው፡፡ የኢህአዴጉ የልማታዊ መንግስት መከራከሪያ ከኒህ ሀሳቦች በተፃራሪ ይቆማል፡፡ በ1993 ዓ.ም. በፓርቲው የታተመው ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች›› የሚለው ሰነድ እና አቶ መለስ ለኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ያቀረቡት "African development: Dead ends and now beginnings" የተሰኘው የ3ኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ሀሳቡን ለመረዳት ተጠቃሽ ሰነዶች ናቸው፡፡ የሀሳቡ ጠንሳሽ አቶ መለስ ሀሳቡን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አደባባይ ያመጡት እ.ኤ.አ. በ2006 ዓ.ም. በማንቼስተር ዩኒቨርስቲ በተካሄደው የአፍሪካ ታስክፎርስ ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ በዚህ ንግግራቸው ሀሳቡን ከመከተላቸው በፊት እና በኋላ ተከትሎ የመጣውን ‹‹ጉዳት›› ዘርዝረዋል፡፡ ‹‹ከዚህ ቀደም አይ.ኤም.ኤፍ. እና የአለም ባንክ ኒዮ-ሊበራል ማሻሻያዎችን እንድንተገብር ሲጠይቁን አማራጭ አድርገን የያዝነው አቋም አልነበረንም፡፡ ስለዚህም የተጠየቅነውን ማሻሻያ በማዘግየት የማዕከላዊ መንግስቱ ሚና የዘበኛ መንግስትነት (watch man state) እንዳይሆን ተከላክለናል፡፡ ነገር ግን በ1990ዎቹ መጀመሪያ የመረጥነው የዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት አካሄድ በ1993 የተከሰተውን የፓርቲውን መከፋፈል ድረስ ዋጋ አስከፍሎናል፡፡›› ሲሉ የፓርቲያቸውን አቋም አስረድተዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የፓርቲው ሰነዶች ላይም ሆነ በሰውየው ቃለ-ነቢብ /rhetoric/ የኪራይ ሰብሳቢነት ባህርይ የማይታይበት የግል ክፍለ-ኢኮኖሚው ጠንካራ መሰረት እስኪይዝ ድረስ ማዕከላዊ መንግስቱ ከገንዘብና ከአስተዳደራዊ አቅም ገደቦች ውጪ የማይሳተፉበት የኢኮኖሚ ክፍል አይኖርም፤ ይህ የማይሆን ከሆነ ኪራይ ሰብሳቢ ተቋማት የበረከቱበትና በገበያ ጉድለቶች የተሞላ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ስርዓት ይነብራል የሚለው ዋነኛ መከራከሪያ ጭብጥ ሆኖ ወጥቷል፡፡

## የችጋር ፖለቲካ

ካለፉት አስራ አምስት ዓመታት ወዲህ የችግርን ተደጋጋሚነት አስመልክቶ የተሰሩ ጥናቶች በክስተቱ መነሻነትም ሆነ መፍትሔነት የሚያቀርቡት መከራከሪያ የፖለቲካ ስርዓትን ይንተራሳል፡፡ የትኛው የፖለቲካ ስርዓት በውስጡ ያሉትን ህዝቦች በተሻለ ሁኔታ በችጋር ከማለቅ ይጠብቃል የሚለው የእኒህ ጥናቶች ወሳኝ ማጠንጠኛ ርዕስ ጉይይ ሆኖ መጥቷል፡፡ ይህን ክርክር ከሚገፋት ቀዳሚ የሆነው አማርቲያሴን የችጋርን መከሰት ወይም አለመፈጠር ከተተግባሪ /Functional democracy/ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ህልው መሆን ጋር ያዛምደዋል፡፡ "Development as freedom" በሚለው ተወዳጅ ድርሳኑ እንደሚሟገተው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በሰፈነበት፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በሚከወንበት አልፎም የነፃ ፕሬስ ነፃነት ባልተገደበበት አውድ ችጋር ማህበረሰባዊ ተግዳሮት አይሆንም፡፡ ከእርሱ ይህን መሰሉ ሙግት በፊት ለችጋር በመፍትሔነት የሚቀርበው ለኢኮኖሚያዊ ህዳጣን የማህበረሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚ ተኮር ድጋፎች ማድረግ ክስተቱ እንዳይፈጠር ያደርጋል የሚል ነበር፡፡ ፕ/ር ሴን በበኩሉ እኒህ የኢኮኖሚ ድጋፎች እየተተገበሩ እንኳን ክስተቱ ያልረገበባቸውን የተለያዩ ሀገራትን ነባራዊ ሁነት በመጥቀስ ካለ ሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች መከበር ችጋርን መግታት እንደማይቻል ይከራከራል፡፡ በቀድሞው የሴንጋፑር ፕሬዚዳንት ሊ ኳን ያው ስያሜውን ያገኘው ‹‹የሊ ሀቲት›› ለዚህ የሴን ሙግት የቀረበው ሌላው የትችት ጫፍ ነው፡፡ ዳን ባኒክ የተባሉ አጥኚ "Democracy, drought and starvation in India: Testing sen in theory and practice" በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚያብራሩት ቻይና፣ ሴንጋፖር እና የቅድመ ዴሞክራሲዋ ደቡብ ኮሪያ ያሳዩትን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በመጥቀስ ካለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የተሻለ ሀገር መገንባት ይቻላል የሚለው ይህ ሀቲት የቆመው ምሁራዊ አቅምን በሚያሳንሱ ቁንፅል መረጃዎች ላይ ሲሆን እንደባኒክ ክርክር በእኒህ ሀገራት ችጋር የሚከሰትበት ዕድል አሁንም ቢሆን ሰፊ ነው፡፡

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ወዲህ ሲከሰቱ የተስተዋሉትን ችጋሮች እንዳይከሰቱ ይቻል የነበረበትን እድል ለማስመልከት ‹‹አዲሶቹ ችጋሮች›› ሲሉ የሚጠሯቸው የጉዳዩ ፀሐፊዎች አማርቲያ ሴን ከተጠቀሰው ስራው በተጨማሪ በቅርቡ ባሳተመው "The Idea justices" መድብል ለተሟገተለት ሀቲት ተጨማሪ የድጋፍ መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ በዚህ መንፈስም ፕ/ር አሌክስ ዲ ዋል በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ነኝ በሚል መንግስት መፈፀም አለበት ያሉትን ‹‹የፀረ-ችጋር ውል›› /anti- famine contract/ ወደ የችጋር ፖለቲካው ተዋስኦ ቀላቅለዋል፡፡ ፕ/ር ዲ ዋል "Democratic political process and the fight against famine" በሚለው ጥልቅ ጥናታዊ ስራቸው እንደሚያትቱት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፈን ብቻውን ችጋርን ለመግታት በቂ አይሆንም፡፡ እንደ እርሳቸው በመጀመሪያ ችጋርን ፖለቲካዊ ገፅ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ችጋርን ፖለቲካዊ ልባስ ለመስጠት በመንግስት እና በህዝብ መሀከል ‹‹የፀረ-ችጋር ውል›› መፈፀም ይኖርበታል፡፡ ይህ ውል ችጋርን ፖለቲካዊ ገፅ ስለሚሰጠው በመንግስታት ሀገራዊ ዕቅድ ውስጥ ቀዳሚን ስፍራ ይይዛል፡፡ እንደ ፕ/ር ዲ ዋል ክርክር የዚህ ውል መፈፀም በሀገሪቱ ውስጥ በሚደረጉት የፖለቲካ ምርጫዎች ችጋር ዋነኛው የአደባባይ ጥያቄ ይሆናል፡፡ በአንድ ወቅት ይህን ውል የፈፀመ መንግስት የሚቀጥለውን ምርጫ ለማሸነፍ በሀገሪቱ ውስጥ ችጋር የማይከሰትበትን ሁኔታ ማመቻቸቱን ለፖለቲካው ማህበረሰብ ማሳመን ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ፕ/ሩም እንደሚያምኑት የዚህን ውል ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ሴን የሚጠቅሰው ተተግባሪ አጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ የዴሞክራሲ ተከዋኝነት መሰረት ፍትሃዊ ምርጫ መካሄዱ እና የሚዲያ ነፃነት መከበሩ ግዴታ በመሆኑ በህዝቡ እና በመንግስት መካከል የተፈረመ ውል መሟላት አለመሟላቱን ማህበረሰቡ የሚረዳበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ‹‹በዚህ መሰረት›› ይላሉ ፕ/ር ዲ ዋል ከላይ በተጠቀሰው ስራቸው ‹‹ችጋርን መግታት የቅቡልነት መሰረት ሲሆን የክስተቱ ተደጋጋሚነት ደግሞ ፖለቲካዊ ቅሌትን ይፈጥራል፡፡››

በአስከፊነቱ ከሚጠቀሰው የ1960ዎቹ ረሀብ ጀምሮ በችጋር ፖለቲካ ተዋስኦ ውስጥ በእነ አማርቲያ ሴን ጭምር ስሟ የሚነሳው ኢትዮጵያ በዚህ ሙግት መሰረትነት ሊመረምሯት የሞከሩ ፀሐፊዎች እጅግ ጥቂት ናቸው፡፡ ከሀገር ውስጥ መምህራን ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ብቸኛ ይመስላሉ፡፡ ‹‹ለችጋር የሚኖር ተጋላጭነት›› \"vulnerability to famine/ የሚለውን ሀሳብ ለችጋር ፖለቲካው ተዋስኦ ያስተዋወቁት ፕ/ር መስፍን "Suffering under God's environment" በሚለው መፅሐፋቸው ለችጋር ተደጋጋሚነት የፖለቲካና ማህበራዊ ተቋማትን ድቀት፣ የግለሰብ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# ትራንስፎርሜሽን ምን ማለት ነው? ማን ገብቶታል?



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

‹‹ትራንስፎርሜሽን›› የእንግሊዝኛ ቃል ነው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአማርኛ ችሎታው የሚደነቅ ሲሆን ለምን ይህንን የእንግሊዝኛ ቃል በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ደነቀረውና ሰውን ሁሉ አደናገረው? ሰፊና ጥልቅ ማኅበረሰባዊ ለውጥ በማኅበረሰቡ ውስጥ ነውጥ (ይቺ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቃል ነች!) በሚፈጠርበት ጊዜ አእምሮም መንፈስም ይነካል፤ ግንበ ሰናኦርን ወደሰማይ ሲክቡ የቋንቋ አለመግባባት እንደተፈጠረና ሰዎቹ ሥራቸውን ለማከናወን እንደተሳናቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፤ በተጨማሪ በአብዮት ጊዜ እንዲሁ የቋንቋ መዘበራረቅ እንደሚፈጠር ሌኒንም ማኦም በቁጣ ጽፈዋል፤ በኢትዮጵያ አብዮቱ በጦፈበት ጊዜ ቋንቋ ድራሹ ጠፍቶ ነበር፤ አፍ ላይ የመጡትን ቃላት እንደልብ እየደረደሩ ሀሳብ የሌለበት ንግግር ማድረግ የዘመኑ ፈሊጥ ነበር፤ በዚያን ዘመን አዲስ ዘመን ‹‹ስለእርባታ ኃይሎች›› ሲያወራ ስለከብት እርባታ የመሰላቸው ሰዎች ነበሩ፤ አንዴ ደግሞ ርእሰ አንቀጹ ‹‹ሳይንሳዊ ቅጥፈት›› የሚል ነበር፤ የጋዜጣው አዘጋጅ ሳይንስና ቅጥፈት ሊዛመዱ የማይችሉ መሆናቸው አልገባውም ነበር፤ ወይም እንዳይገባው ተደርጎ ነበር! እውቀት በሥልጣን በኩል ተገኘ ሲባል ይህን ያመጣል።

ወደ ትራንስፎርሜሽን እንመለስና፣ በ‹‹ትራንስ›› የሚጀምሩ የእንግሊዝኛ ቃላት ብዙ ናቸው፤ ትራንስፖርቴሽን፣ ትራንስሌሽን ሁለት ምሳሌዎች ናቸው፤ ትራንስፖርቴሽን ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ማዛወር ወይም ማንቀሳቀስ ነው፤ ያንኑ ነገር ቦታውን መለወጥ ብቻ ነው፤ ትራንስሌሽን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጎም ነው፤ ይህ ደግሞ አንዱን ነገር ከተቻለ ነፍሱን ብቻ በውስጡ አስቀርቶ አካሉን በሙሉ መለወጥ ነው፤ እንዲሁም ትራንስፎርሜሽን ማለት መልኩን መለወጥ ነው፤ በዚህ ትርጉሙ ከተረዳነው የሕዝቡን መልክ መለወጥ አይቻልምና ገና በጥንስሱ ሰዎችን የመለወጥ ዓላማ አልነበረበትም ማለት ነው፤ ሕዝቡን አይመለከትም ማለት ነው፤ ለከተማዎች መልክ ሳይሆን አይቀርም፤ ትራንስፎርሜሽንን በአዲስ አበባ ላይ ስለጥፈው ትክክል ይመጣል፤ ተወልጄ ያደግሁበትን ከተማ፣ ከእንጦጦ እስከብሾፍቱ፣ ከኮተቤ እስከአምቦ፣ ከጊዮርጊስ እስከዝቋላ በእግሬ እየሮጥሁ ያደግሁበትን ከተማ ዛሬ አላውቀውም፤ በየሄድሁበት ይደናገረኛል፤ እኔ የማውቀው ሰፈር ድራሹ ጠፍቶ፣ ወይ የእንጦጦን፣ ወይ የኤረርን፣ ወይ የዝቋላን፣ ወይ የወጨጫንና የመናገሻን ተራራዎች እየሸፈነ ወደሰማይ ያንጋጠጠ ግንብ ሰናኦር፣ የቤት አነባበሮ ተሠርቶአል፤ ትራንስፎርሜሽን ማለት ይሄ ነው፤ ዱሮ ዱሮ መደማመጥ በነበረበት ዘመን በአራት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ውስጥ በነበረው ርዕደ-ምድር መካነ ጥናት በአዲስ አበባ ውስጥ ከአምስት ፎቅ በላይ እንዳይሠራ መባሉን አስታውሳለሁ፤ ትራንስፎርሜሽኑ የከርሰ-ምድርን ሁኔታ በጣም የናቀው ይመስላል፤ በዚያ ላይ የመብራት ኃይል ምን ያህል አስተማማኝ ቢሆን ነው አሥርና ሃያ ፎቅ የመውጣትና የመውረዱ ችግር ያልታሰበው!

የአዲስ አበባ መልክ ተለውጦአል፤ አያጠራጥርም፤ እዚህ ላይ አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ፤ አዲሱ የማዘጋጃ ቤት ሕንጻ ከጊዮርጊስ በታች ተሰርቶ ለአዲስ አበባ አዲስ ጌጥ ሊሆን በተቃረበበት ጊዜ በጊዜው የነበሩት ከንቲባ ከአንድ ጓደኛቸው ጋር ይጨዋወታሉ፤ ከንቲባውን በነገር ለመውጋት የከንቲባው ጓደኛ ‹‹አሁን ይሄ ሕንጻ ሲያልቅ እናንተው ናችሁ የምትገቡበት?›› ብለው በማሾፍ ጠየቁ፤ ከንቲባውም የዋዛ ሰው አልነበሩምና ‹‹ደምበኞቻችንም እኮ እናንተው ናችሁ!›› ብለው በማሾፍ መለሱላቸው፤ ከንቲባውና ጓደኛቸው ቢቀልዱም ንግግራቸው ትልቅ ቁም-ነገርን የያዘ ነበር፤ ሕንጻው አዲስ ነው፤ አላሉትም እንጂ ትራንስፎርሜሽን ሊሉት ይችሉ ነበር፤ በጊዮርጊስ ፊት ለፊት ከሚታየውና የአዲስ አበባን ሕዝብ ከሚመስለው የዱሮው ማዘጋጃ ቤት ጋር ሲወዳደር ለውጡን ትራንስፎርሜሽን ቢሉት ዘመናዊ ያደርገዋል፤ አዲስና ዘመናዊ ሕንፃ ገንብተው በዚያ ውስጥ ገብተው የሚሰሩትና በዚያው ሕንጻ ውስጥ ለአገልግሎት የሚመጡት የሕንጻው አዲስነትና ዘመናዊነት በጭራሽ ያልነካቸው ከሆኑ የሕንጻው መገንባት ፋይዳው ምኑ ላይ ነው?

በትራንስፎሜሽን የአዲስ አበባ ሕንጻዎችና መንገዶች በጣም ተለውጠዋል፤ አምረዋል ለማለትም ያስደፍራል፤ ከሕንፃዎቹና ከመንገዱ ሳንወጣ ስንት ዓመት እንዳማረባቸው ይቆያሉ? መንገዶቹስ ስንት ክረምት ያሳልፉናል?

ትልቁና ዋናው ቁም-ነገር ሕንጻዎቹና መንገዶቹ የተሰሩት ለማን ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፤ ሰፊ አስፋልት መንገድ ተሠርቶ ለአህዮች መንጃ የሚውል ከሆነ፣ ወይም በቀለበት መንገድ ግራና ቀኝ የሚኖሩ ሰዎች መንገዱን ለማቋረጥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፣ ልጆችም ሆኑ ሕጻናት ከመኪና ጋር ሲሽቀዳደሙ የሚደርስባቸው ፈተናና አደጋ የሚያሳዝን ከሆነ፣ ትራንስፎርሜሽን የተባለው ከሰዎች ጋር ግንኙነት እንደሌለው ከዚህ በላይ ማስረጃ አያስፈልግም፤ መንገዱ ሲሠራ ሰዎቹ ተረስተው የነበረ ይመስላል፤ ጎጆዎቻቸው ፈርሰውባቸው መድረሻ ያጡትን ሰዎች እናስታውሳቸው፤ በሕንጻና በመንገድ ግንባታ የብዙ ሰዎች ኑሮ ፈራርሶአል፤ ብዙ ሰዎች ፈራርሰዋል።

ትራንስፎርሜሽን ለውጥ ማለት ሲሆን፣ ለውጥ ማለት ልማትን ብቻ ሳይሆን መሻገትንም ይጨምራል፤ ስለዚህም ለልማት የሚደረገው ለውጥ መሻገትን ካላቆመ ለሕዝብ የኑሮ እድገት አይመጣም፤ ግሩም ሕንጻ ተሠርቶ የተፈለገው ስም ቢሰጠው በሚሰጠው አገልግሎት ላይ በጎ ለውጥ፣ ለተገልጋዩ ሕዝብ የሚበጅ ለውጥ ካላመጣ ለግምቡና ለሰራተኞቹ የሚወጣው ኪሳራ ሊሆን ይችላል፤ በቅንነት ለመሥራት በጎ ፈቃድ ሲኖር የችሎታ ማነስንም ሊያሸንፍ ይችላል፤ ቅን መንፈስ በጎደለበት ሥልጣንና ተንኮል ሲገናኙ ሕግን መጫወቻ ያደርጉታል፤ በቅርቡ አንድ ከምርጫ ቦርድ ለአንድ እጩ የፖለቲካ ቡድን የተጻፈ ደብዳቤ አይቼ በጣም አዘንሁ፤ የትራንስፎርሜሽኑ የልማት መንፈስ መሥሪያ ቤቱን እንዳልነበኘውና በአንጻሩ የማሻገት ኃይሉ የማያራምድ እንደሆነ በግልጽ ይታያል፤ ሌላም ምሳሌ በትግራይ የውሃ ጉድጓድን በሚመለከት የዛሬ ሳምንት በኢንጂነር (ዓብድልዋሃብ ቡሽራ ፍትሕ ጋዜጣ የሚያዝያ 26 ዕትም) አሳዛኝ መረጃ ተሰጥቶ ነበር፤ ደርግ የለውጥ ሐዋርያ የሚባሉ በየመሥሪያ ቤቱ ሾሞ ነበር፤ ዞሮ ዞሮ የለውጥ ሐዋርያቱን ከየት እናመጣቸዋለን? የዚሁ ማኅበረሰብ አካል ናቸው፤ ባህሉ፣ ችግሩ፣ ሕመሙ፣... ምኑም ምኑም ያለባቸው ናቸው፤ ስማቸውን በመለወጥ ባሕርያቸውን መለወጥ አይቻልም።

ዱሮ. ዱሮ የአዋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን የሚባል መሥሪያ ቤት ተቋቁሞ ነበር፤ ለወንጂ ሸንኮራ አገዳ እርሻ መሬት ሲባል በዚያ አካባቢ ከብቶቻቸውን እያረቡ በዘላንነት የሚኖሩ ሰዎችን ወደዳር ገፍተው የበይ ተመልካች አደረጓቸው፤ ይህንን ለውጥ በመኮነን በኢትዮጵያ የጂኦግራፊ መጽሔት ላይ ጽፌ ነበር፤ የሰማኝ አልነበረም፤ ነገር ግን ልማት ብለው ከገቡት ውስጥ ዛሬ አንድም የለም፤ ትምህርት ሳይሆነን ቀርቶ ዛሬም በከረረ መልኩ እየተደገመ ነው፤ መሬትን መቆፈር፣ መጠፍጠፍ፣ መዳመጥ ቀላል ነው፤ በመሬት ላይ ለውጥ ለማምጣት ቀላል ነው፤ ነገር ግን ይህንን ቀላል ለውጥ ከማምጣት በፊት ሁለት ቀላል ጥያቄዎችን ማንሣት ያቅተናል፤ አንድ፣ በመሬቱ ላይ የሚደረገው ለውጥ (እርሻም ሆነ ግንባታ) ማንን ይጠቅማል? ማንንስ ይጎዳል? ቁጥራቸውስ ምን ያህል ነው? ሁለት፣ የለውጡ ኃይል ማን ነው? አዲሱ ለውጥ የአካባቢውን ነዋሪ፣ ባለቤቱን ያለማዋል? ወይስ ያሻግተዋል? ነዋሪዎቹ፣ ባለቤቶቹ ለውጡ የሚጠቅማቸውና የሚያለማቸው ከሆነ ፈቃዳቸውን ማግኘት ለምን ያቅታል?

በአዲስ አበባና በአካባቢዋ የሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ ከዚያ አልፈው ወደገጠር አካባቢ ሲደርሱ ሁኔታዎች ኮረኮንች ይሆናሉ፤ የአዲስ አበባ ሕዝብ ውጥንቅጥ ነው፤ ብቻውን አዝኖ ብቻውን ይችለዋል፤ በገጠር የሕዝቡ ኑሮ በብዙ መንገድ የተሳሰረ ነው፤ አዲስ አበባ የቻለውን ለውጥ ሁሉ በሌላም ቦታ ለማድረግ መሞከሩ አደጋ አለበት።

የለውጡ ዓላማ ምንድን ነው? ለውጡ ሰዎችን ይጨምራል ወይ? ሰዎችም እንደመሬት ተለዋጭ ናቸው? ወይስ ለዋጭም ናቸው?

# ወይ ሀገሬ!

## (ከልማት አድማስ ባሻገር)

ዓለማየሁ ገላጋይ

አሁን በዚህ ሰሞን ‹‹የሀገር ጉትያ›› ሊባል የሚችል ሰማይ ጠቀስ ምናብ ላይ ወጣሁ። ሀገሬ ካርታዋን የተከተለ፣ ድንበሯን ሙጥኝ ያለ የአድማስ-ክፍክፍቷ አይነ-ህሊናዬ ላይ ተደቀነ - ለምናብ ምን ይሳነዋል? ወይ ሀገሬ! የስንት አገዛዝ ጀንበር ወጥቶ፣ የስንት መንግሥት ፀሐይ-ግባት ተከናወነ? ከአክሱም መገንባት ወዲያና ወዲህ፣ ከጐንደር ቤተመንግሥት መድመቅ ወዲያና ወዲህ፣ የጢያ ሀውልቶች ከመቆማቸው ወዲያና ወዲህ፣ ከላሊበላ አቢያተ ክርስቲያናት መተከል ወዲያና ወዲህ.... የብዙ ዜጐች መማሰን በትውልድ ቅብብሎሽ ሲከናወን፤ ቅጥልጥሎሹ እንደ ሰሜን ተራሮች ገዝፎ ይታየኛል።

ወይ ሀገሬ!

ከጊዜ በላይ፣ ከወቅት በላይ፣ ከሰው በላይ፣ ከተፈጥሮ ህግ በላይ፣ ከፍጡራን በላይ፣ ከተረታ ተረታት በላይ፣ ከአፈ-ታሪክ በላይ፣ ከሚመስለውና ከማይመስለው በላይ... የምናብ ማማ ላይ። ታሪክ እንደግራር ከበቀለበት መልክአ-ዘመን ባሻገር በተረትና በአፈታሪክ ጭንብስብስ ውስጥ'ኳ እዚያ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ይታየኛል። እስከ ህንድ የተዘረጋች ኢትዮጵያ፣ እስከ የመን የተንሰራፋች ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲን የተነጠቀች ኢትዮጵያ፣ ኤርትራን የተደገመች ኢትዮጵያ...

ወይ ሀገሬ!

ዜጐች ከመማሰን ያልተፋቱባት ምድር፣ የላብ ቱሩፋት፣ የወዝ አስራት ያልተቋረጠባት አገር። የዕድገት ሾተላይ የተጠናወታት፣ የዘመን ደም የመታት። የጋሸበ፣ ከፍሬው ቁመቱ ቀድሞ መርዘሙ የጣለው ሥራ የሚበዛባት። ስንቴ ደምቃ? ስንቴ ጠልቃ? ስንቴ ሞታ? ስንቴ ተነስታ? ስንቴ ጠፍታ? ስንቴ በርታ?

ወይ ሀገሬ!

ከመልክአ-ታሪክ ባሻገር፣ እዚያ የዘመን ገመገም ውስጥ መላ ዓለምን ያማለለች ኢትዮጵያዊ ንግሥት ነበረች ንግሥተ ሳባ (Sheba) የተባለች። አድሐናት (Adhanat) የተሰኘውን ወንዝ የገደበች፣ ዝናብን እንደምርት የሰበሰበች፣ ቢርካ አበጅታ ተክሎቿን ያጠጣች፣ በቅመማ ቅመምና በፍራፍሬ የታወቀች፣ ወርቅና እንቁ ያከማቸች። ከ2ሺህ 500 ዓመታት አስቀድሞ (በ542 ቅድመ ክርስቶስ) የሥልጣኔ ጣሪያ የነካች። ማሪብ (Marib) የተሰኘ ከተማዋን ከበረሃ አሸዋ መናወፅ ለመከላከል 60 ጫማ ርዝመት ያለው ግንብ ያስገነባች ቅዱስ ቁርአን ላይ እንዲህ ይላል "The people of Sheba had beautiful gardens in which the most costly fruits repened" (የሳባ ሰዎች ከሁሉም በላይ ውድ የሆኑ ፍሬዎችን የሚያበቅል የአትክልት ሥፍራ ነበራቸው)

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ "And when the queen of Sheba heard of the fame of Solomon, she came to prove Solomon with hard questions at Jerusalem." (ንግሥተ ሣባ የሰለሞንን ዝና በሰማች ጊዜ ይሄንኑ ለማረጋገጥ ከባድ እንቆቅልሾችን ይዛ ወደ ኢየሩሳሌም መጣች)

እናስ? ይሄ የሳባ ኢትዮጵያዊ ፀሐይ እንዴት ጠለቀ?

ቅዱስ ቁርአን የሳባ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በመጓደዳቸው በመጀመሪያ የውሃ ማጠራቀሚያቸውን መታ፣ ቀጥሎም የአትክልት ሥፍራቸው መራር ፍሬዎች እንዲበቅሉበት አደረገ ይለናል።

ወይ ሀገሬ!

የኢትዮጵያ መውደቅና መነሳቷ፣ መብራትና መጥፋቷ ከዚህ ይጀምራል። የተካበው ሲናድ፣ የተሰራው ሲፈርስ፣ የተጠራቀመው ሲፈስ... ከተረቱና ከአፈ ታሪኩ ባሻገር ያለው የታሪካችን መልክአ ምድር ወጣ-ገባ ነው። ኢትዮጵያዊነት ደግሞ ይሄንን የትውልዶች ስርንጉጥ ያለምንም ተጨማሪ ማነቃቂያ ስለሀገር ፍቅር ብቻ መጓዝ።

ወይ ሀገሬ!

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ‹‹ረሃብና ተስቦ በኢትዮጵያ›› በተሰኘው ጥናታቸው ማጠቃለያ ላይ እንዲህ ይላሉ ‹‹ከታሪካችን ታላላቅ ምዕራፎች አንዱ የሚመሰክረው የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያን የልጆቿን ደም ጠጥቶ፣ በልጆቿ ሥጋ ዳብሮ፣ የልጆቿ አጥንት የሚመረትበት መሆኑን ነው›› እዚህ የኢትዮጵያውያን የደም፣ የሥጋና የአጥንት ግብር ውስጥ ረሃብ፣ ጦርነትና ተስቦ ትልቁን ድርሻ ቢወስዱም ለልማት የተከፈለ መስዋዕትነትም አለበት። ሌላው ቀርቶ በአጤ ምኒልክ የባቡር መስመር ዝርጋታ ወቅት ከድሬደዋ አቃቂ እስኪደርስ 1ሺህ 900 ሰዎች አልቀዋል። አፄ ዳዊት ስለግብፆች መጥገብ አባይን ሲገድቡ የስንት ኢትዮጵያውያን ደም፣ ሥጋና አጥንት ገበሩ? ትልቁ አፄ ፋሲል በአባይ ላይ ባለ ሰባት ቅስት ድልድይ ሲያስገነቡስ፣ ምን ያህል ኢትዮጵያውያን ተሰዉ? የንጉስ ላሊበላ ትልቁ ቤተመድኃኒያለም ሲታነፅስ? አፄ ቴዎድሮስ ሴባስቶፖል መድፍን ከጋፋት ወደ መቅደላ አፋፍ ሲያስገፉ በዚያ ሰባት ወር ውስጥ ስንት ሰው አለቀ?...

...የኢትዮጵያውያን ታሪክ ከገገርዎቻቸው ህልም በስተጀርባ አገራቸውን የመፈለግ መማሰን ነው። የጦርነት ህልም፣ የመንፈሳዊነት ህልም፣ የልማት ህልም። ስለሀገር፣ በሀገር፣ ለሀገር ከሆነ ኢትዮጵያውያን የትኛውንም መከራ ታጋሾች ናቸው። ታዲያ ምነው ዛሬ? ታዲያ ምነው አሁን? ታዲያ ምነው በዚህ ትውልድ?... ሠፈር ልቀቁ ስንባል ያጥወለውለናል፣ አዋጡ ስንባል ያመናል፣ ቦንድ ግዙ ስንባል ደም ያስተፉናል። ለምን?

ወይ ሀገሬ!

ይራበን፣ ይጥማን፣ እንታረዝ... ይሄ ችግራችን ሀገር ቅልቅል፣ ባንዲራ ቅይጥና ሉአላዊ ድብልቅ ከሆነ እንታገስም አልነበር? ታዲያ አሁን ‹‹ተገነባ›› ሲባል የማይሞቀን ‹‹ተደነባ›› ሲባል የማይበርደን ስለምን ነው? እንኳ ተገንብቶ እስኪገነባ አላስችል ብሎን ገገርዎቻችን ፊት ቀርበን አቤት እንል አልነበር?

በ1956 ዓ.ም. ላይ ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት ሄደው ጃንሆይ ፊት ቀረቡ። ‹‹በሥልጣኔ ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ ወደ ኋላ ቀረን›› ብለው አቤት አሉ። ግርማዊነታቸው እንዲህ ሲሉ ምላሽ ሰጡ አሉ።

‹‹ኢትዮጵያን ማወዳደር ያለባችሁ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ጋር ነው›› ተማሪዎቹ ልባቸው እያለቀሰ፣ ጥርሳቸው እየሳቀ ተመለሱ።

ታዲያ አሁን ሳይጠየቅ አገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጋር ለመደባለቅ የተነሳ መንግሥት እንዴት ሙሉ ድጋፍ ያጣል? እንደምንስ እምነት ይነፈጋል?

ወይ ሀገሬ!

በኢትዮጵያ ውስጥ ድጋፍ የተነፈገው፣ እምነት ያልተጣለበት ‹‹ልማታዊ መንግሥት›› አንድ ብቻ ነበር። አንጡራ ኢትዮጵያዊ ችላ ያለው ልማት፣ ችላ ያለው ድህነት ማጥፋት፣ ችላ ያለው የመልካም አስተዳደር ሥራ ነበር። ያ‹‹ልማታዊ መንግሥት›› የፋሽስት ኢጣሊያ አገዛዝ ነበር። ‹‹የቄሣር መንግሥት መልክተኛ›› የተሰኘው የፋሽስቱ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 1933 ዓ.ም. ዕትሙ እንዲህ ይላል፡-

‹‹ስሙ፣ ስሙ፣ ስሙ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ከያዘ ዛሬ አምስተኛ አመት መሆኑ ነው። በዚህም በአምስት አመት ውስጥ የተሰራው ቤት፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ የተማሪ ቤት፣ ኤሌክትሪክና የመታከሚያ ቤቶች ሌላውም የተሠራው ሥራ ብዙህ ነው። የኢጣሊያ መንግሥት ለየሥራው ለህዝቡ እርዳታ ያወጣው ገንዘብ ከመቶ ሚሊአርድ ይበልጣል። ለገንዘቡ አይሰስትም፣ ሕዝብ እንዲበለጥግ፣ አገር እንዲለማ ነው የሚፈልግ። በኢትዮጵያ መንግስት ጊዜያት ግን ድሃን እያስለቀሱ ገንዘብ መቀማት፣ ማሰር፣ መፍታት ነበር ሥራቸው። ለድሃው ትንሽ አያዝኑለትም ነበር። የኢጣሊያ መንግሥት ለቸርነቱ ወሰን የለውምና ለወደፊቱም ለሥራና ለተቸገረ ሰው መርጃ እንዲሆን ብሎ ከባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ ብዙኅ ሚሊአርድ ነው። እናንተም የኢትዮጵያ ልጆች በቅንነት መንግሥትን ካገለገላችሁ ጥቅሙን ወደፊት ታገኙታላችሁ። ለጊዜውም ባላገሩ ሠርቶ እንዳይበላ ነጋዴውም እንደልቡ እንዳይነግድ ዋና ጠላት የሆኑት ሽፍቶቹ (አርበኞቹን ማለቱ ነው) ናቸው። እነሱ ሲጠፉ ወይም ወደመንግሥት በገቡ ጊዜያት የኢትዮጵያን ማማር፣ የሕዝቡን መበልጠግ በዚያን ጊዜያት ታዩታላችሁ።››

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# መንግስት ብቻ የሚያለማበት አገር?

መንግስት በተለያዩ መስኮች ሰፋፊ የልማት አውታሮችን ቀይሶ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ደጋግሞ ሲገልፅ ይሰማል፡፡ ነገር ግን ፕሮፓጋንዳውን እንደወረደ እንቀበል ቢባል እንኳ ሁሉም የመንግስት እቅዶች በህብረተሰቡ ዘንድ በሙሉ ድጋፍና ተቀባይነትን አግኝተው ነው ወደ ስራ የተገባው ብሎ መደምደሙ አስቸጋሪ ነው፡፡ ለእነዚህ ሁሉ የልማት አውታሮች አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ከመንግስት ጐን በቅን መንፈስ እንዳይቆም ካደረጋቸው ብዙ ምክንያቶች ውስጥ በተወሰኑት ላይም ቢሆን መንግስት ቆም ብሎ ለመነጋገር እድሉን ማመቻቸት ሲጠበቅበት እስከዛሬ ግን ሲያደርገው አልተስተዋለም፡፡ እናም የህብረተሰቡ ሙሉ ይሁኝታ እና ትብብር ያልታከለበት የልማት እቅድ ስኬታማ ይሆናል ብሎ መጠበቅ አዳጋች ከመሆኑም በተጨማሪ ለወደፊቱም ቢሆን በዘላቂነት የተሰሩትን ስራዎች ተንከባክቦ ለማቆየት የሚኖረው ተነሳሽነት የደበዘዘ ነው የሚሆነው፡፡

በፍትህ እምነት ፖለቲካ እና ልማት ተያይዘው የሚጓዙ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ በፖለቲካው መስክ የተሻለ ውጤት ያላስመዘገበ አገር በልማቱ መስክ መልካም ውጤት ሊያገኝባቸው የሚችልባቸው መንገዶች በጣም ውሱን ነው የሚሆነው፡፡ ማህበረሰቡ በአገሩ ጉዳይ በነፃነት የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ እና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን በአግባቡ እስካላገኘ ድረስ ዜጎች በአገራቸው የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ በንቃት በመሳተፍ ውጤታማ ይሆናሉ ብሎ መጠበቅ ደግሞ የዋህነት ነው፡፡ በተለይ በመንግስት እና በህብረተሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመተማመኖች ዋነኛው መነሻቸው አገሪቱን በሚያስተዳድረው መንግስት ባህሪ የሚነሳ በመሆኑ ነው፡፡ አምባገነንና ሙሰኞች የበዙበት ስርአት ባለበት አገር፣ገዢው ፖለቲካ በውስጡ ተጠያቂነትን እስካላዳበረ ድረስ መንግስት ለሚከውናቸው አገራዊ ዘርፈ ብዙ ተግባራት የህዝቡን ይሁኝታ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

መንግስት በተከታታይ ‹‹እያካሄድኩ ነው›› የሚለውን የልማት ተግባራቶች ለማስተባበር ሲታሰብ ብዙውን ጊዜ ከውዴታ ይልቅ ግዴታ ተመራጭ ሆኖ ይታያል፡፡ ብዙዎቹም ተግባራት የዜጐችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከህገ-መንግስቱ ድንጋጌ አንፃር ሲጥሱ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ ለልማት በሚፈለግ መሬት ላይ ዜጐች እንዲነሱና ወደ ሌሎች ቦታዎች እንዲሰፍሩ የሚደረግበት አግባብ ብዙውን ጊዜ የተፈናቃዮችን ይሁኝታ ያገኘ አይደለም፡፡ በጋምቤላ የተካሄደው የመሬት መቀራመት (Land grabbing) ለዚህ ተጠቃሽ ምሳሌ ነው፡፡

በፍትህ እምነት የውጭ ዜጐችን በልማቱ እንዲሳተፉ ከማድረግ በፊት የአካባቢው ህብረተሰብ ይሁኝታ እና በጐ ፍቃድ በእያንዳንዱ እርምጃ ላይ መንፀባረቅ ይገባዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ፓኪስታኖቹ ላይ እንደደረሰው አይነት አደጋ በሌሎቹም ላይ ላለመድረሱ ማስተማመኛ ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰቡ ይቸግራል፡፡ በውጭ አገር ዜጐች ላይ አደጋ ሲደርስ ይህ የመጀመሪያው አይደለም፡፡ በኦጋዴን የነዳጅ ማውጣት ቁፋሮ ላይ የተሰማሩት ቻይናውያን ላይ ከጥቂት አመት በፊት የደረሰውን እልቂትም እዚህ ጋር ማንሳቱ ተገቢ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተደጋጋሚ አደጋዎች መሰረታቸው አንድና አንድ ነው፡፡ የአካባቢ ነዋሪዎች ከልማቱ ስለሚገኘው አጠቃላይ ትርፍ ግንዛቤውን ሳይጨብጡ፣ ከመንግስት አካላት ጋር መግባባት ላይ ሳይደርሱ በግድ የሚፈፀሙ በመሆናቸው ነው፡፡

ፍትህ የዜጐችን መፈናቀል፣ ስቃይ እና እንግልት አንዱ የልማት መገለጫ መሆን አለበት የሚል እምነት የላትም፡፡ በማንኛውም መልኩ ዜጐች በልማቱ መተማመኛ እንዲያገኙ አስቀድሞ ሰፊ የማስገንዘቢያ፣ የውይይት እና የክርክር መድረኮችን መንግስት ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ በተለይ የልማት ስራዎችን ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ በህብረተሰቡ ውስጥ የማሳመን ተልዕኮን ይዘው የሚላኩ አካላት ከካድሬ ይልቅ ባለሙያዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ በጋዜጣችን እምነት በተለይ ለዚህ ተልዕኮ የሚመለመሉት ወጣትና የተማሩ ከመሆናቸውም ባሻገር የፌዴራል ስርአቱ በተተገበረበት መንገድ ለልማት ከሚፈለገው አካባቢ የተውጣጡና የብሔሩን ቋንቋ፣ ወግና ባህል በሚገባ ጠንቅቀው የሚያውቁ ቢሆኑ ስራውን ቀላል ያደርገዋል፡፡

ዋናው አላማ ነገሮችን በጉልበት ከማድረግ ይልቅ በመግባባት ማድረጉ የበለጠ አትራፊ ያደርገዋል ከሚል ቅን አመለካከት የሚመነጭ ነው፡፡ ተያይዞም የታለመለትንም እቅድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ አይነተኛ አማራጭ ይሆናል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ በግዳጅ የሚከናወን ልማት፣ አልሚዎቹን ሰለባ ከማድረጉም በላይ ወደፊት ወደ አካባቢው መጥተው ተመሳሳይ ተግባራትን ለማከናወን የሚፈልጉ ቡድኖችን እንዳይበረታቱ ያደርጋቸዋል፡፡

ሌላው ትኩረት የሚሻውና የፖለቲካ ውድቀት በጉልህ የሚንፀባረቀው ትላልቅ አገራዊ የልማት ውጥኖች ላይ ነው፡፡ አገራችን በውስጧ ብቻም ሳይሆን ከሌሎች ጐረቤት አገራት ጋር ሁሉ በሚያያይዟት የልማት ፕሮግራሞች ላይ ህብረተሰቡ ቸልተኛ የመሆኑ ነገር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሚሆነው የውኃ ኃብትን የማልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡ ዋናዎቹ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚገነባባቸው ታላላቅ ወንዞቻችን አገር አቋርጠው የሚጓዙ ናቸው፡፡ በእነዚህ ወንዞች ላይ የሚገነቡ ተከታታይ ግድቦች በመንግስት እና በህብረተሰቡ አቅም ብቻ ይገነባሉ ተብለው አይታሰቡም፡፡ ሌሎች የልማት አጋር የሆኑ ቡድኖች አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በፍትህ እምነት መንግስት በዜጐች ንቁ ተሳትፎ ላይ እና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሙሉ በሙሉ የማሳተፍ፣ የማማከር እና የወሳኝነት ሚና እንዲጫወቱ አፋጣኝ እርምጃዎችን መውሰድ እስካልቻለ ድረስ ብቻውን ተነጥሎ አንዳችም ነገር መስራት አይችልም፡፡ ወጣቶች የሚደራጁበት፣ የሚወያዩበት፣ የሚከራከሩበት፣ ስልጠና እና ድጋፍ የሚያገኙበት፣ ከፖለቲካ ወገንተኝነት የነፃና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት የሚሳተፉ ማህበራት፣ ፖሊሲ አመንጪ ቡድኖች ይኖሩ ዘንድ መንግስት ቀጥተኛ ፍቃደኝነቱን ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡ ፍትህ ይህ ሁሉ የሚሆነው መንግስት ከግትረኛነት እና ከጠቅላይነት ባህሪው ተላቆ በህገ-መንግስቱ ላይ የሰፈሩት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ኃላፊነቱን ሲወጣ ብቻ ነው የሚል አቋም አላት፡፡

አስተያየት

# በመስተዋት ቤት ውስጥ ነዋሪ፣ ቀድሞ ድንጋይ ወርዋሪ፣ ሳሳሁልህ ከበደ ማን ናቸው?



**አዮስ ጫሚሶ**
የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር

ወ/ር ሳሳሁልህ ከበደ ከመስታወት ባነሰ ነገር በተሰራ ነገር ውስጥ መኖራቸውን እያወቁ ሌሎችን እየጠሩ እንዲህ ናቸው፣ ይህ አደረጉ፣ እንዲህ ነበርኩ፣ ወይም ከነበሩት ውስጥ ነኝ ወዘተ... እያሉ ለ8 ወራት አምጠው የፃፉትን አይቼ ምላሽ በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡

በመሰረቱ አንድ የፖለቲካ ድርጅት (ፓርቲ) የሚመሰረተው ለዜጐች መነሻውም የስልጣን ጥያቄ መሆኑም የሚስተባበል አይደለም፡፡ ወደዚህ ግብ ለመድረስና ለስልጣን ለመብቃት አባላት ያስፈልጉታል፡፡ አባላቱም የፓርቲውን ፕሮግራምና ህገ ደንብ አስፈፃሚዎች እንዲሆኑ ፓርቲው በያዘው ርዕዮተ ዓለም የታጠቁ፣ ከፍተኛ የዲሲፕሊንና የአርአያነት ተግባር ባለቤት መሆን ይገባቸዋል፡፡ የፓርቲው ውስጠ ዴሞክራሲና ዲሲፕሊን ተገዥዎች እንዲሆኑም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የፓርቲው የዴሞክራሲ መርሆዎች፣ (ለምሳሌ የዕዝ ሰንሰለትና የአሰራር ተዋረድ በአባላቱ ዘንድ ሌላውና ጠንካራ መርህ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡ የፓርቲው አባላት የፓርቲው የአመለካከትና የፕሮግራሙ አተገባበር ውህድ ናቸው ተብሎም ከመታመኑም በላይ፣ ታማኝነታቸውና የማስፈፀም ኃላፊነታቸውም ለፕሮግራሙ፣ በዚያውም ፓርቲው ለሚመራው መንግስት ፕሮግራሞች ይሆናል፡፡

በእነዚህ ሂደቶች ታዲያ አባል ከአባሉ የርዕዮተ ዓለም ውህድ ከመሆናቸው የተነሳ አይጠራጠሩም፣ አሳልፎም አይሰጣጡም፣ አይመራጃጁም፣ በሀሰትም አይወነጃጀሉም፣ በተቃራኒው ችግር ከተከሰተም በሂስና በግለሂስ የመተራረም መድርክ አላቸው፡፡ በዚሁ ተጠቅመው ራሳቸውን እያጠናከሩ በአብሮነት ይጓዛሉ፡፡ እንዲጓዙም ይፈለጋል፡፡ ፍፁምነት ከሰው ልጅ ባይጠበቅም በአብዛኛው፣ ቢቻል ሁሌም ለቆሙለት ዓላማ ፍጹማን መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም፣ የራሺያው የኮሚኒስት ፓርቲ አመራር የነበረ ሊዮን ትሮቲስኪ ዓይነት ለፓርቲውና ለህዝቡ ታማኝ ያልሆነ አይገኝም ተብሎ አይገመትም፡፡ በኢኮኖሚ፣ በእውቀትና በርዮተ ዓለም ኋላ በቀሩ ሀገራት የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎችና አንጃዎች በአብዛኛው ጊዜ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና የሞራል ብቃት ስለሚያንሳቸው ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚፈልጉት በህጋዊ ምርጫ ሳይሆን በአውዳሚ የትጥቅ ትግል፣ በህዝብ ደም መፋሰስ በአንባጓሮና በግርግር ሲሆን ይስተዋላል፡፡ ይህ ተግባር ከመነሻውም የሀሳብ ልዕልናን የሚጨፈልቅ በአፈሙዝ ትምክህት የሚነሳ በድምሩም ውጤቱ ሕጋዊነትን፣ ሕገመንግስታዊነትንና ዴሞክራሲያዊነትን ከመጉዳቱም ባሻገር ህዝቡ በትክክል የሚመራውን ወኪሉን ሳይለይ በአቋራጭ የስልጣን ባለቤት በመሆን በቋመጡት ኃይሎች በኃይል ስልጣን ላይ መውጣትንና ህብረተሰቡን አያገባህም፣ እኔ አውቅልሃለሁ በማለት የሚደመደም አደገኛ፣ በአሁኗ ዓለምም የማይታሰብ ቢታሰብም ውጤት አልባ እየሆነ ነው፡፡

ስለዚህ በአንድ ፓርቲ ውስጥ የዴሞክራሲ መስረፅ እጅግ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል የአባላት ዲሲፕሊንና የእርስ በርስ ውህድነት ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አባል አባሉን አሳልፎ የሚሰጥ ከሆነ፣ እንደ ወንጀለኛ በሐሰት እንዲጠየቅ የሚያደርግ፣ ሀሰተኛ ማስረጃና ምስክር ሆኖ የሚቀርብ ከሆነ፤ በሁሉ ቻይ ጌታ እግዚአብሔር ዘንድ ኩነኔ፣ ከህዝብ ታላቁ ባህርም መተፋትን፣ ውግዘትንና በጊዜ ፍርድ ተጠያቂነትን የሚያስከትል የህሊና ውርደትና የፖለቲካ ውስልትና ነው፡፡

ባለፈው መጋቢት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. በታተመው ፍትህ ጋዜጣ ላይ ወ/ር ሳሳሁልህ ከበደ እኔን ምርጫ ቦርድን አስመልክቶ ለመሞነጫጨር በሞከረው እርባና ቢስ፣ በተቃርኖ የታጨቀ ጽሑፍ እርሱ ቅንጅትን ያቋቋመው በ1997 ምርጫ ምክንያት በተፈጠረው ሁኔታ የታሰሩን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራርና አባላትን ለማስፈታት እንደሆነ አድርጎ ሳያፍር ገልጿል፡፡

እኚህ ሰው ማን ናቸው? በመሰረቱ ወ/ር ሳሳሁልህ እንዳሉት ዓይነት የሚቋቋም ፓርቲ ይኖራልን? አይኖርም፡፡ የለምም፡፡ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚቋቋመው ለህዝብ የተሻለ አማራጭ በማቅረብ በሰላማዊ ትግል ስልጣን ለመያዝ ስለሆነ በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ለገለፁት ዓላማ የሚቋቋምም ሆነ ያቋቋሙት ፓርቲ ሊኖር አይችልም፡፡ የጠቃቀሷቸው ነጥቦችም በሙሉ ነጭ ውሸት፣ ፍሬከርስኪ የጥላቻ ክምሮች ናቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች በውኑ ዴሞክራሲያዊው ዓለም ሳይኖሩ እና ይህ ነው በሚባል የንድፈ ሀሳብ ወይስ ስነ-አመክንዮ መንገድ ሄደው ሳያውቁ ፀሐፊዎች እንደሚያደርጉት ሆኖ መቅረቡን ሊያውቁበት ይችላሉ፡፡ ወይም ትወና ቢጤ ያምራቸዋል፡፡ እኚህ ‹‹ፀሐፊም›› እንዲህ ናቸው፡፡ ራሳቸውም በቂ ምስክር እንደሆኑት በማንኛውም ፓርቲ ውስጥ እንደሚገባው ሳይሳተፉ የራስን ጥቅም ብቻ በማለም የተነሱና እኛ ዘንድ የነበሩ የከረሙ ናቸው፡፡

በመጨረሻም በፍትህ አካል የተያዘ ጉዳይ ሆኖብኝ እንጂ ለምርመራ አካሉ የቀረቡትን 18 የወንጀል ድርጊቶች አፈፃፀምና መቼት ከተገቢ የማስረጃ ትንታኔ ጋር ለአንባቢ ፍንትው አድርገን ልናሳይ እንችል ነበር፡፡ ለማንኛውም የወንጀሉ ጉዳይ በሚያዘው አካል ተይዟል፡፡ ህዝቡን በአጠቃላይና የፍትህ አንባቢያን በተለይ ለማወናበድ ለቅንጅት አመራርና ለአባላቱ ተቆርቋሪ በመምሰል ዘራፍ! እኔ ወ/ር ሳሳሁልህ፣ የከበደ አጋ ልጅ!! ዘራፍ! ዘራፍ! ያሉት ሰው ለራሳቸውም የማይዋጥ ነጭ ውሸት ነውና የፃፉት የዘራፍ ምላሱ አፎት ካለው ወደ አፎቱ ቢገባና የጊዜን ፍርድ ቢጠብቅ፡፡

ለማጠቃለል፣ ሳሳሁልህ በጋዜጣው ላይ ይህን ያህል ገንዘብ ወጪ አድርጎ ተጠቅሟል ያለውን በተመለከተ፣ ከነጭ ውሸትም በታች ተራ ምስክርነት መሆኑን እንዲያሳይ፤ የተበላው ገንዘብ ጠያቂው፣ ቼክ የተሰራለት፣ ፈርሞ ወሳጁ፣ ወስዶም በሐሰተኛ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ደረሰኝ ከፈልኩ ባይ፣ ወታደሩ ስለመሆኑ፣ የፓርቲውን ማህተም አትሞ ለሐሰተኛ ማስረጃ ሽፋን ሰጥቶ መገኘቱ በመጨረሻም ለማህተሙ መታገድና ቀሪ ሆኖ ውድቅ መደረግ ምክንያት የሆነው፣ (ፓረቲው አዲስ ማህተም አስቀርፆ ስራ ላይ ማዋሉ፣ ለክቡራን አንባቢዎችና ለሁሉም በዚህ አጋጣሚ ይታወቅ) ማን እንደሆነ እንዲታወቅ ምንም በህግ የተያዘ ቢሆንም ለዝግጅት ክፍሉ መረጃነት ሰነዶቹ ተያይዞ ተልኳል፡፡

ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተር
ሰውዓለም ታዬ

አምደኞች
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ
አናንያ ሶሪ

ግራፊክስ ዲዛይን
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡- አራዳ
ቀበሌ፡- 17
የቤት፡- 984

# የህዝብ እና የተቃዋሚ ፓርቲዎች መንታ መንገድ



ተመስገን ደሳለኝ

…የመኢአድ ም/ሊቀመንበር ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ የመኢአድ ሊቀመንበር በሆኑት ኢንጂነር ኃይሉ ሻወል በተከሰሱበት ክስ ሁለት አመት ከስድስት ወር ተፈርዶባቸው ከርቸሌ ገቡ፤ መኢአድ እንደአንባሻ ተከፋፈለ፤ የማይለያዩት ኃይሉ ሻውል እና ማሙሸት አማረ ተለያዩ፡፡ አንድነት ፓርቲ ብርቱካን ሚደቅሳ ትፈታ ይል የነበረውን ጥያቄ አንዱአለም አራጌ ይፈታ በሚል ቀየረው፤ ብርቱካንን በማስብ ይበራ የነበረውንም ሻማ አንዷአለምን በማሰብ ይበራ ዘንድ ወሰነ፤ ብርቱካን ሚደቅሳ ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ልታጠና ዋሽንግተን ሄደች፣ ስዬ አብርሃ ለትምህርት ወደአሜሪካ ሄዱ፤ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ጀርመናዊ ህፃናቶችን ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ሊያስተምሩ ጀርመን ገቡ፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና እና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ዘንድሮም ሊቀመንበር ናቸው፤ ዘንድሮም ምክትል ሊቀመናብርቶቻቸው አይታወቁም፡፡ ሳሳሁልህ ከበደ ስልጣን ያዙ፤ አየለ ጫሚሶ ተባረሩ፡፡ ኢዴፓ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ትልቁ ችግር የአፍሪካ የሌብራል ፓርቲ ስብሰባን ያለማካሄድ ነው በሚል ቁጭት የአፍሪካ ሌበራል ፓርቲ ስብሰባ አዲስ አበባ እንዲካሄድ አደረገ፤ ልደቱ አያሌው ከፓርላማ ሲባረሩ ትምህርት ቤት ገቡ…. ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል ‹‹አጀንዳ አልባው›› የተቃዋሚ ፓርቲ ሠፈር አክራሞት፡፡

እነሆ ዘንድሮም በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተያዘው የትግል ስልት ‹‹ኢህአዴግ አምባገነን ነው››፣ ‹‹ኢህአዴግ ምርጫ ያጭበረብራል››፣ ‹‹የፀረ-ሽብርተኝነት ህጉ አፋኝ ነው››፣ ‹‹ከኢህአዴግ አመራር በሙስና የተጨማለቀው ይበዛል››፣ ‹‹ሀገሪቱ በአውራ ፓርቲ መዳፍ ስር ወደቀች›› …ከሚል ማጋለጥ ያለፈ ሊሆን አለመቻሉንም እያየነው ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተቃዋሚዎች ትግል የተገኝ ‹‹መረጃ›› ሳይሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጠንቅቆ የሚያውቀው ተራ ወሬ ነው፡፡

በእርግጥ በግሌ በሀገሬ ያሉ ሁሉም ተቃዋሚዎች ‹‹ከጥቆማ ያለፈ›› ትግል የማድረግ ወይ ወኔው የላቸውም፤ ወይ ብርታቱ የላቸውም ብሎ ለመደምደም ይቸግረኛል፡፡ በተለይ ደግሞ የተሻለ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ የሚችሉትን አራቱን ፓርቲዎች እዚህ ውስጥ መደመሩ ለተቀማጭ ሰማይ… ይሆንብኛል፡፡ (አንድነት፣ መኢአድ፣ አረና እና ኦፌደንን ማለቴ ነው) ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ እንዳናጨበጭብላቸው የምርጫ ቦርድን የምዝገባ ሰርተፍኬት ታቅፎ ከመቀመጥ የዘለለ ስራ ሲሰሩ አይታዩም፡፡

በነገራችን ላይ ደጋግሜ እንደፃፍኩት ምክንያታቸው ምንም ይሁን ምን የተቃውሞውን ጎራ ለመምራት ወደ አደባባይ የወጡት ፖለቲከኞች በዛጎላቸው ከተሸሸጉት ‹‹ሌሎች ኢትዮጵያውያን›› የበለጠ ‹‹አክብሮት›› ይገባቸዋል፡፡ (ይሁንና ግን ሌሎች ኢትዮጵያውያኖች ማለት ምን ማለት ይሆን? እዚህ ውስጥ የሚመደቡትስ እነማን ይሆኑ? ከኢትዮጵያ ሌላ ትርፍ አገር ያላቸው ናቸው ወይስ የስርአቱ ምንደኞች?) ብቻ ከዚህ ባለፈ ክንብንባቸውን ገልጠው ፊታቸውን ያስመቱ ፖለቲከኞቻችን ለእስከአሁኑ አበርክቶታቸው ዋጋ ሊያገኙ ይገባል፡፡ በዚህ በኩል ችግር የለም፡፡ ችግር የሚኖረው ያ የአክብሮት ዋጋ በየአመቱ እየተመነዘረ ‹‹መሪ›› በሚል ስም ዛሬም በስልጣናችን እንደተቀመጥን መቀጠል አለብን ሲሉ ነው፡፡ ይሄ ወደድናቸውም ጠላናቸውም ትልቅ ችግር ፈጣሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት አጣብቂኝ ከጥቆማና ከአጋላጭ ባለፈ ‹‹አንቂና አደራጅ›› መሪ የሚፈልግበት ወሳኝ ጊዜ ላይ ነውና፡፡

እናም ማህተም እና የምርጫ ቦርድ ፈቃድ ያላቸው ፓርቲዎችን ብቻ ሳይሆን ‹‹የተሻሉ›› ሊባሉ የሚችሉት አራቱ ድርጅቶችም ቢሆኑ ለኑባሪያቸው (ህልውናቸው) መገለጫ ሊሆን የሚችል ስራ ሲሰሩ ማየት እንፈልጋለን፡፡

ከዚህ ውጭ ቀጣዩ ውድድር ወይም ፉክክር እንደቀድሞው ሁሉ በገዢው ፓርቲ እና በተቃዋሚዎች ብቻ የመሆን እድሉ ከቀን ወደ ቀን እየጠበበ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በርካታ ‹‹ተቀጣጣይ ነገሮች›› በህዝብ እና በመንግስት መካከል የከረረ ፍጥጫን እየፈጠሩ በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ በግልፅ አማርኛ ስንነጋገርበት ‹‹ዙሩ እየከረረ ነው›› የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህን ጊዜም ነው የአደባባይ ሰው ወይም መሪ ድርጅት ከወዴት ነህ? ብለን እንድንጠይቅ የምንገደደው፡፡

አሁን ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ‹‹ከሞላ ጎደል…›› ተብለው እንኳ ሊመረጡ የሚችሉ አይደሉም፡፡ እንደዋዛ ‹‹ኢህአዴግን ማውረድ ቀላል ነው›› ሲሉ ልትሰሟቸው ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ያንን ‹‹ቀላል›› መንገድ አያሳዩዋችሁም ወይም አያውቁትም፡፡ እናም ይህንን ‹‹ዋዛ ፈዛዛ›› ለማስወገድ ቀድመን መነጋገር አለብን፡፡ ለምሳሌ ረጅም የትግል ልምድ አላቸው የሚባሉትን የፕ/ር በየነ ጴጥሮስን እና የዶ/ር መረራ ጉዲናን ድርጅቶች ብናይ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች መንደር ከክበበው ገዳ የበለጠ ኮሜዲያን የበዛበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በእርግጥ በየነም ሆኑ መረራ ‹‹ፖለቲካ እና ኮረንቲ በሩቁ›› እየተባለ ለንፅፅር በሚቀርብበት ሀገር በተቃውሞ ጎራ መገኘታቸው በራሱ ዋጋ ሊያሰጣቸው እንደሚገባ ከላይ ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ያ ዋጋ ግን ዛሬም ድረስ ሊጨበጥ እና ሊዳሰስ የማይችል ፓርቲ ይዘው ‹‹መድረክ›› በሚባል የተበሳሳ ዣንጥላ ተጠልለው ‹‹ወከልነው›› በሚሉት ህዝብ ላይ እየቀለዱ እንዲኳዙ የሚያስችላቸው መሆን የለበትም፡፡ አሁንም ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እነዚህ ሁለት ሊቀመንበሮች ‹‹ድርጅት›› ይሁኑ ‹‹ግለሰቦች›› ሊለዩ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ መለስ ዜናዊ ላይ ሲሆን የሚቃወሙትን የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት እነሱ ጋ ሲደርስ ‹‹ትክክል ነው›› ይሉናል፡፡ ለዚህም ነው አንድም ቀን ጠቅላላ ጉባኤ ሲያካሄዱም ሆነ የራሳቸውን አጀንዳ ቀርፀው ሲታገሉ ያላየናቸውን ፓርቲዎቻቸውን እንደፓርቲ ልንቀበል አይገባም የምለው፡፡ አመንም አላመንም በየነ ወይም መራራ የሚባል ግለሰብ ይኖራል እንጂ የሚመሩት ፓርቲ በህይወት የለም፡፡

ሌላው ቀርቶ የመረራ ጉዲና ፓርቲ ጽ/ቤት ሀላፊ የሆነው ኦላና ሌሊሳ በአሸባሪነት ተጠርጥሮ ሲታሰር በህይወት ስለመኖሩ ከማህተም ባለፈ ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለው የዶ/ር መረራ ኦህኮ በያዘው ማህተም እንኳ ተጠቅሞ አንዳች ያደረገው ነገር የለም፡፡ እልፍ አእላፋት የኦሮሞ ልጆች እንደበግ ከትምህርት ቤት እና ከእርሻ ቦታቸው እየታነቁ ሲታሰሩ ‹‹የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ›› ድምፁን ማሰማት ያልቻለው ለምን ይሆን? ዛሬ የወለጋ እና የባሌ እናቶች የደረሱ ልጆቻቸው እየታነቁባቸው ‹‹የፍትህ ያለህ?›› ሲሉ እያየን መራራን እንደፖለቲካ ታጋይ መውሰዱ ለታሪክ ስህተት እንደሚዳርግ አትጠራጠሩ፡፡ የሀድያ ብላቴናዎች በ‹‹ችጋር›› ከቀዬአቸው መሰደድን በየነ ጴጥሮስ ከቁም ነገር እንደማይቆጥሩት ሁሉ፤ ኦሮሞ መሆን ብቻውን ‹‹አሸባሪ›› ማስባሉ ለመራራ ጉዲና ችግር አይደለም፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስደፍረው ችግሩን እንደ አንድ የመቀስቀሻ (የመታገያ) ስልት ወስደው ሲጠቀሙበት እና ሲያውገዙት አለመታየታቸውም ጭምር ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ፓርቲው ከመህተም ውጭ ህይወት አልባ በመሆኑ ይመስለኛል፡፡

…ከዚህ በኋላ ምን አልባት ራሳቸውን አጠናክረው ከ‹‹እስኮላር›› እና ‹‹ፌሎው-ሽፕ›› ማሳደድ እርቀው መውጣት ከቻሉ አንድነት፣ መኢአድ፣ አረና እና ኦፌዴን የተሻለ ተቀባይነት የሚያገኙበት እድል ከየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሰፋ ነው፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ከሚማልሉበት የውጭ ሀገር ትምህርት ዕድል ብቻ ሳይሆን እየተከተሉት ካለው የዘልማድ ‹‹ፖለቲካ ፓርቲ››ነት መላቀቅ ከቻሉ ብቻ ነው፡፡

እዚህ ጋ አንድ ነገር ግልፅ መሆን አለበት፡፡ እነዚህን ፓርቲዎችም ቢሆን የሰፋ እድል አላቸው ያልኩት በአመራሩ ጥንካሬ ተማምኜ አይደለም፡፡ ይልቁንም የዕድላቸው እጣ ፈንታ ገና ‹‹ያልተፋቀ›› የሆነው ጠንካራ የድርጅት ፍቅር ባለው አባሎቻቸው ብርቱነት ላይ ተመስርቼ ነው፡፡ በዚህ ቀመር መሰረትም አንድነት እና መኢአድ ልዩነታቸውን አጥበው በጋራ መስራት ከቻሉ ሰፊ ሊባል የሚችል ዕድል አላቸው፡፡ ምንአልባት ይህ የሚቸግራቸው ከሆነም ከሁለቱ የትኛው ልቆ ይወጣል? የሚለው አጨቃጫቂ ቢሆንም ሁለቱም ከሰሩ ከገቡበት ቅርቃር ሊወጡ የሚችሉባቸው ሽርፍራፊ ዕድሎች አላቸው፤ ከነአሰልቺና ማለቂያ የሌለው ችግሮቻቸው ማለቴ ነው፡፡ የአረናና የኦፌዴን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ ፓርቲዎች ብሄር ተኮር ከመሆናቸው አኳያ የሚነፃፀሩት በወከሉት ብሄር ውስጥ ባላቸው ተቀባይነት ነው፡፡ እናም ንፅፅሩ ኦሮሚያ ውስጥ ኦፌዴንን ከኦህዴድ፤ በትግራይ መሬት ላይ ደግሞ አረናን ከህወሓት ይሆናል ማለት ነው፡፡ እንግዲህ በሚዛን የሚቀመጠው የኦሮሚያ እና የትግራይ ህዝብ ነፃ የመወዳደሪያ መድረክ ከተመቻቸለት ለየትኛው ድርጅት የተሻለ ድጋፍ ይሰጣል የሚለው ነው፡፡ መቼም ለ21 አመታት ያህል ግብር ከመሰብሰብ እና ማዳበሪያ ከመቸርቸር የዘለለ ፋይዳ ለሌላቸው ኦህዴድ እና ህወሓት ነው የሚል ቀልደኛ ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡


ከዚህ ባሻገር በሀገራችን ፖለቲካ ላይ በየአመቱ እንደአዶ-ከበሬ የሚከሰት አንድ አደገኛ ተመላላሽ ችግር አለ፡፡ የአንጃ ፖለቲካ የሚባል፡፡ ይህ አይነቱ አደጋ ነው የፓርቲውን ውስጠ ሚስጥር የጉሊት ሸንኩርት የሚያደርገው፡፡ ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ ባሉ ተቃዋሚዎች ውስጥ የአንጃ ፖለቲካ የሚከሰተው በሶስት ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው መናፍቅነት /ጥርጣሬ/ ሲከሰት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ደግሞ ‹‹አንጋፋ›› ፖለቲከኞቻችን የተካኑ ናቸው፡፡ ልክ መለስ ‹‹በሲኒ ውስጥ ማዕበል የሚፈጥሩ›› የሚሏቸው አይነት፤ ‹‹እከሌ ወያኔ ነው›› ይሉና ጠርጥረው ያስጠረጥራሉ፤ ፈርጀው ያስፈርጃሉ፡፡ ይህንን ተከትሎም በአንጃዎች መናጥ የፓርቲው ዕጣ ፈንታ ይሆናል፡፡ ይህን ጊዜም ትላልቆቹ ፖለቲከኞች ሽሚያ ይገባሉ፤ ሽሚያው ግን ፓርቲውን ከአንጃ ወጀብ ለመታደግ አይደለም፤ ትከሻው ለ‹‹ሎሌነት›› የተመቻቸውን ለማፈስ እንጂ፡፡

ሁለተኛው ችግር የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊነት ነው፡፡ በዚህ ተቃዋሚዎች የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ከኢህአዴግ አይለዩም፡፡ ክፉ አቻዎች ናቸው፡፡ በመኢአድ ውስጥ የኢንጅነር ኃይሉ ሻወልን ሃሳብ መቃወም ዛሬ መኢድ ያለበት ደረጃ ያደርሳል፡፡ መስነጣጠቅ ማለቴ ነው፡፡ አመራሩን መገምገም ወይም የአደባባይ ስህተቱን መተቸት ‹‹መናፈቅ›› ያስብላል፡፡ እናም በሁሉም ፓርቲዎች ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ‹‹ውስጠ-ዲሞክራሲ›› የሚባል ነገር እምጥ ይግባ ስምጥ አይታወቅም፡፡ በዚህም የተነሳ ለገዥው ፓርቲ ሲሆን ‹‹ለልዑላኑ እውነት መናገር አንገት ያስቀነጥሳል›› ማኪያቬሊያዊ አስተምህሮት በተቃዋሚዎች ሰፈር ሲደርስ እንዲህ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን ‹‹አመራሩን መተቸት መናፍቅነት ነው››፤ መናፍቁ ደግሞ የራሱን አማኝ ያሰባስብና አንጃ ይፈጥራል፡፡

ሶስተኛው Personality Cult (የተክል ስብዕና አምልኮ) ለመፍጠር የሚደረገው እሽቅድምድም ነው ለአንጃ መፈጠር በር ከፋች የሚሆነው፡፡ ለምሳሌ በትግሉ ዘመን በህወሓት ውስጥ ግለሰብን ማምለክም ሆነ ለመመለክ ራስን ማመቻቸት በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ነበር፡፡ ከ1993ዓ.ም በኋላ ግን ይህ ሁኔታ ተቀይሮ በግልባጩ መለስ ዜናዊን ያለማምለክ በሞት ባያስቀጣም ከፓርቲ ጥቅማ ጥቅም በእጅጉ ያርቃል ተባለ- ባልተፃፈው የህወሓት ህግ፡፡ ይህንንም ተከትሎ አንጃ ተፈጠረ፡፡ እናም በህወሓት ውስጥ ‹‹ውድብ /ድርጅት ወስናለች›› ተረት የሆነውን ያህል በተቃዋሚዎችም ‹‹ቅድሚያ ለፓርቲው ውሳኔ›› የሚለው መርህ ተረት ሆኖአል፡፡ ለዚህ ትልቁ ማሳያ በየነ ጴጥሮስ እና መረራ ጉዲና ናቸው፡፡ ለምሳሌ የመረራ ጉዲና ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር ገብሩ ገ/ማርያም በማንኛውም መልኩ ከመራራ የሚያንስ አቅም የላቸውም፡፡ እንዲያውም በአንዳንድ ነገሮች፣ ሀሳብን አፍታቶ በማብራራት እና በመሳሰሉት የተሻሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ላለፉት አስራ ስድስት አመታት ከመረራ ውጭ ማንም ሊቀመንበር ሆኖ አያውቅም፡፡ ምንአልባትም በቀጣዩ አስራ ስድስት አመታትም ኦህኮ በዚህ መልኩ የሚቆይ ከሆነ እመኑኝ መረራንም በሊቀመንበር ወንበር ላይ እናገኛቸዋለን፡፡ ሌላው ቀርቶ በየትኛውም ሚዲያም ሆነ መድረክ ም/ል ሊቀመንበራቸውን ገብሩ ገብረማሪያም ኦህኮን ወክለው ሲናገሩ አናያቸውም፡፡ ይህ የሆነው በመለኮታዊ ስልጣን አይደለም፤ መረራ የመሰረቱት ፓርቲ የራሳቸውን ተክለ ስብዕና ብቻ ይዞ ይገነባ ዘንድ ስላመቻቹት እንጂ፡፡ እናም ልክ ኢህአዴግ ሲነሳ መለስ ዜናዊ፤ ህወሓት ሲነሳ መለስ ዜናዊ እንደሆነው ሁሉ ኦህኮም ሲነሳ ከፊት መራራ ጉዲና ናቸው፡፡ በየነ ጴጥሮስም ‹‹ጽዋ›› እየተጠጣ የሚዘከርለት መላዕክ ይመስል በፓርቲያቸው ውስጥ ራሳቸውን ‹‹አምላክ›› አድረገዋል፤ ያውም የማይከሰስ፣ የማይወቀስ፡፡ በዚህም ተደጋጋሚ ጊዜ በአንጃ ተከፋፍለው ከጦር መሳሪያ ፍልሚያ መለስ ባሉ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »


የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ “የመለስ አምልኮ” መፅሐፍ በድጋሚ ታተመ





# ታላላቅ ሐሳቦች የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

## ውድ ዶ/ር አድለር

እርስዎ ዘወትር የሚያወሷቸው ‹‹ታላላቅ ሐሳቦች›› የትኞቹ ናቸው? የሆነ ቦታ ያነበብኩት እንደመረጃ እንደሚጠቁመው ከሆነ እስከዛሬ ከካበተው የሰው ልጅ የጥበብ ታሪክ ውስጥ አንድ መቶ ታላላቅ ሐሳቦችን አንጥረው በማውጣት አሰባስበዋል። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ሊነግሩኝ ይችላሉ? ለእኛ አስተሳሰብ የተሻለ ጠቀሜታ ያላቸውስ የትኞቹ ናቸው?

ኤም.ደብሊው.

## ውድ ኤም.ደብሊው.

‹‹ታላላቅ ሐሳቦች›› በምዕራቡ ዓለም ባህል ውስጥ በታላላቅ ፀሐፍት የተነሱ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ‹‹ታላላቅ ሐሳቦች›› በሚል ርዕስ በሁለት ቅፅ የተከፋፈሉ መጽሐፍት ተዘጋጅተው ነበር። በእነዚህ ቅፆች ታላላቅ ሐሳቦችን በማሰባሰብና በማስተንተኑ ሥራ ላይ በማስተባበር ሰርቻለሁ። በቅፆቹ ውስጥ ከታላላቅ ሐሳቦች በተጨማሪ ከሆሜር እስከ ፍሮይድ ድረስ ያሉ ታላላቅ የፅሁፍ ሥራዎችም እንዲካተቱ ተደርጓል።

እኔና በእኔ ሥር የነበሩት ምሁራን 102 መሠረታዊ ሐሳቦችን አግኝተናል። መሰረታዊ ሐሳቦቹ በፊደል ቅደም ተከተል በመልአክ (Angel) ጀምሮ በዓለም (World) ይጠቃለላል። እነዚህ መሠረታዊ ሐሳቦች፣ ባለፉት ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ወይም በዓለም ሥልጣኔ ውስጥ የእሳቤና የተግባር ማዕከል ሆነው ያገለገሉ ናቸው።

አንተ ለማወቅ የፈለከው ተፅዕኖ የፈጠሩትንና በሰፊው ሥራ ላይ የዋሉትን ታላላቅ ሐሳቦች ነው። ለአንተ ምላሽ የሚሆነው አንዱ፣ ታላላቅ መጽሐፍትን ለማቅረብ ለፀሐፊዎቻቸው መነሻ የሆኑትን ሐሳቦች መዘርዘር ነው። በተደጋጋሚ ለውይይት የሚቀርቡ አምስት ታላላቅ ሐሳቦች፤ እግዚአብሔር (God)፣ ዕውቀት (Knowledge)፣ ሰው (Man)፣ ግዛት (State) እና ፍቅር (Love) ናቸው።

በሌላ መንገድ የአንተን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችለው ‹‹ማዕከላዊ›› ሐሳብን መምረጥ ነው። ማዕከላዊ ሐሳቡ እንደአስኳል ወይም በፕላኔቶች እንደተከበበች ፀሐይ በሌሎች ንዑስ ሐሳቦች ይታጠራል። እነዚህ ማዕከላዊ ሐሳቦች የሌሎች ሐሳቦች በዙሪያቸው የመሰብሰብ፣ የመጠራቀምና የመታጀብ ውጤቶች ናቸው። የሰው ልጅ ትኩረቱን ያሳረፈባቸው ነገሮች ላይ የሚያነጣጥሩ በመሆናቸውም ይታወቃሉ።

‹‹መንግሥት››ን የተመለከተውን ሐሳብ እንውሰድ። ለምሳሌ በመንግስት ዙሪያ የታጀቡ ሌሎች ብዙ ተዳባይ የመንግሥት ዓይነቶች አሉ። መሣፍንታዊ አገዛዝ (Aristocracy)፣ ዴሞክራሲያዊ፣ የዘውድ አገዛዝ (Monarchy)፣ የአምባገነን አገዛዝ (Oligarchy) እና የፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝ (Tyranny) መጥቀስ ይቻላል። ከዚሁ ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች እራሳቸውን የቻሉ ሐሳቦችም አሉ። ህገ መንግሥት፣ ዜግነት፣ ህግ፣ አብዮት እና ግዛት የተሰኙ። እነዚህ ሐሳቦች የፖለቲካ ግንዛቤንና እርምጃን የተመለከተ ማጣቀሻነት አላቸው።

ሥነ-ምግባርን ደግሞ ልብ በል። በተለያዩ ሥነ-ምግባራዊነትን ለሚያጣቅሱ ንዑስ ሐሳቦች ሁሉ ማዕከልነት አለው። ለምሳሌ ጉብዝና፣ ፍትህ፣ ጥንቃቄ፣ መጠንን ማወቅ እና ጥበብ ይጠቀሳሉ ሥነ-ምግባራዊ ንዑስ ሐሳቦች ከሥነ-ምግባር ጋር የቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። በተጨማሪም ከሌሎች አስተሳሰቦች ቅርብ የሆነ ዝምድናም አለው። እንደ መልካምና መጥፎ፣ ደስታ፣ ኃላፊነት፣ ቅጣት፣ ሐጢያት ካሉት ጋር። እነዚህ ሁሉ በአንድ ላይ ሥነ-ምግባራዊ ኃሳቦችን ይመሰርታሉ።

በተመሳሳይ አኳኋን እንዲሁ በ‹‹ሰው›› ማዕከልነት ሥነ-ልቦናዊ ቤተሰብነት ያላቸውን ሐሳቦች መመስረት እንችላለን። ምኞት፣ ስሜታዊነት፣ ልምድ፣ ባህሪይ፣ ትውስታ እና ምናባዊነት፣ አእምሮ፣ ደስታ እና ህመም፣ አመክንዮ፣ ስሜት፣ ነፍስ እና ተስፋ የመሳሰሉትን ማውሳት ይቻላል።

እንደ አብዮት፣ ቋንቋና እድገት ያሉት ሐሳቦች ደግሞ የነገሮች ሁሉ ቀደምት ለመሆን የቻሉት ባለፉት አንድ መቶ አመታት ውስጥ ነው። ዛሬ እነዚህ ሐሳቦች በዋነኛነት ለውይይት የሚቀርቡና ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ሆነዋል። ይሄ ግን ለሁልጊዜም የሚቀጥል አይሆንም። አንዳንድ ሐሳቦችን ያየን እንደሆን አሁን ካሉት ይልቅ ቀደም ሲል በነበሩት ፀሐፍት ከፍተኛ ትኩረት ሲሰጣቸው የነበሩ ናቸው። ለምሳሌ ያህል መልአክ፣ ዕጣፈንታ፣ ትንቢትና ነፍስ።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ብቻ በተሟላ መረጃነት የቀረቡ አይደሉም። ይልቃሉ። አንተ የበለጠ አስፈላጊ ናቸው ብለህ ያሰብካቸውን አንዳንድ ሐሳቦች ገድፌአለሁ። የተገደፉት ሐሳቦች ምንም እንኳን አምስት ዋና ዋና ብዬ ከጠቀስኳቸው ጉን የሚሰለፉ ባይሆንም ከተርታዎቹ ሰልፍ ውስጥ መታጣት አልነበረባቸውም። እንደዚያ ያሉ በእራሴ የማስባቸው ሐሳቦች አሉ።እንደ ውበት፣ ህያውነት፣ ምክንያት፣ ትምህርት፣ ቤተሰብ፣ ነፃነት፣ የጉልበት ሥራ፣ ቁስ አካል፣ ቦታ፣ ጊዜ፣ እውነት፣ ጦነትና ሰላም እንዲሁም ዓለም።

ታላቁ ሐሳብ የቱ መሆኑን ማሰብ ለውጥ አያመጣም። ዋናው ነገር እነዚህ ሐሳቦች ለአስተሳሰባችንም ሆነ ለምናከናውናቸው ነገሮች መሠረታዊ መሆናቸው ነው። ከተቀረው ዓለም ጋር ይሁን ከሌሎች ሰዎች ጋር ለሚኖረን ግንኙነት አወቅንም አላወቅንም የነዚህ ሐሳቦች ጣልቃ ገብነት ሰፊ ነው። ስለየትኛውም ነገር ለማሰብ ስንፈልግ፣ ወይም እርስ በእርስ ለመነጋገር ስንሞክር እነዚህን ሐሳቦች መጠቀማችን የግድ ነው። ካለእነሱ ማየት የማንችል አይነስውር፣ የትም የማንገኝ የጠፋን እንሆናለን።

# የህዝብና የተቃዋሚዎች ...

ከገፅ 5 የዞረ

ፍልሚያዎች ሲፋለሙ ማየቱ አዲስ አይደለም።

ከዚህም አልፈው በተለያዩ ጋዜጦች ላይ በመድረክ በኩል የሚተሳሰሩትን የአንድነት ም/ሊቀመንበር /በዚህ ወቅት ሊቀመንበሩን ወክለው እየሰሩ ነው/ ግርማ ሰይፉ ፓርላማ በመግባታቸው ደጋግመው ወርፈዋቸዋል። በቅርቡ አንድ የመድረክ አመራር እንደነገሩኝ በዚህ ጉዳይ ላይ የስራ አስፈፃሚ አባላት ተሰብስበው እየተወያዩ ሳለ መራራ ጉዲና ‹‹ድንጋይ እየተወራወርን ነው›› ሲሉ የመወራረፉን የእድገት ደረጃ በገደምዳሜ ገልፀዋል። ከዚህ በተረፈ መቼም የሽግግር ወቅቱን ጨምሮ ለአራት ክፍለ ጊዜ / Term/ በፓርላማው ቋሚ ተሰላፊ የነበሩት በየነ ጴጥሮስ ‹‹ፓርላማ መግባትን›› ሲቃወሙ መስማት የተቃውሞ ስብስብ መሪዎች የሞራል ደረጃቸው የት እንዳለ ያሳያል። በዚህ መልኩም በእንዲህ አይነት ፖለቲከኞች የምንሻገረው ወንዝ ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰብ ደመናን የመጨበጥ፣ ጉምን የመዝገን ያህል ይሆንብናል።

ይህንን ጽሑፍ እያዘጋጀሁ ሳለ በመሀሉ የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቢሮ ጎራ ለማለት ሞከርኩ። ፕሮግራማቸውን በደምሳሳው ለመቃኘት። ነገር ግን የአብዛኞቹ ቢሮ ዝግ ነው። እናም ሁለተኛ አማራጭን ተጠቀምኩ። ኢንተርኔትን። በመረራ ጉዲና የሚመራውን የኦህኮ ፕሮግራም አገኘሁና በእጅጉ ተገረምኩ። ያስገረመኝ ምን መሰላችሁ? ከሀገሪቱ የህዝብ ቁጥር ከፍተኛ የሆነውን ኦሮሞን የሚወክለው ኦህኮ ፕሮግራሙ በአምስት ገፅ የሚጠናቀቅ መሆኑ ነው። እንዴት ነው ነገሩ? ምን አልባት ‹‹ኢየሱስ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ነው በዚህ አለም የኖረው›› የሚል የመፀሀፍ ቃል ሰምተው ይሆን እንዲህ በአምስት ነጠላ ወረቀት የተዘጋጀ ፕሮግራም የቀረፁት? ብቻ እንጃ፡ ፡ (እንደማሳሰቢያ፡- በበየነ ጴጥሮስ እና በመረራ ጉዲና ላይ ያተኮርኩት በአሁኑ ወቅት በተቃውሞ ጎራ ያለውን ፖለቲካ በመምራት ከሁሉም የበለጠ የትግል ዕድሜ ስላስቆጠሩ ነው። በተጨማሪም የሁለቱ ሰዎች የፖለቲካ አዙሪት ሌሎችንም ይወክላል በሚል ነው)

የመውጫ በር አለ?

የወንድ በር ሳይሆን የመውጫ በር ለፈለገ አለ። በተለይ ለአንድነት፣ ለመኢአድ፣ ለኦፌዴን እና ለአረና። ለምሳሌ የፀረ መጅሊስ እንቅስቃሴ፣ የመምህራን ጥያቄ፣ የጉራፈርዳ መፈናቀል፤ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሳንሱር፣ የኑሮ ውድነት፣ በልማት ስም ኢፍትሃዊ መፈናቀል... ሌላም ሌላም ጥያቄዎችን በማጎን ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ከእንዲህ አይነት ህዝባዊ አጀንዳዎች ጎን ከመቆም ባሻገርም ሌሎች ድርጅታዊ ጥንካሬን የመፍጠሪያ ስልቶችን መንደፍ እና አድፋጭ ምሁራኖችን ወደ አደባባይ ማምጣትም ሌላው የመጠናከሪያ መንገድ ነው። activist (ተሟጋቾችን) መመልመል እና ማብቃት፤ ከዛም ሀገራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት በአለም አቀፍ መድረኮች ሳይቀር ለመሟገት የሚችሉበትን መደላድል ማመቻቸትም እንዲሁ ለድርጅት ጥንካሬ የጎላ ጠቀሜታ አለው።

በአናቱም ራሳቸውን ስልጣን ላይ እንዳለ ገዢ ፓርቲ በመውሰድ ለእያንዳንዱ ጉድለቶች የመፍትሄ ሀሳቦችን መሸጥ ፓርቲዎቹ ለመጠናከር ከሚችሉባቸው ስልቶች ዋነኛው ነው። በተለይም አማራጭ መንገዶችን ማሳየት ጠቀሜታው የላቀ ነው። ወጣቶችን ወደፊት ማምጣትም ሌላኛው ጠቃሚ ስልት ነው። በ‹‹ያ ትውልድ›› እና በ‹‹66ቱ ፖለቲካ›› የእኔን ትውልድ ‹‹አማልላለሁ›› ማለቱ ግን አስቸጋሪ ነው። እናም ፓርቲዎቹ የአመራር ቦታውን በወጣቶችም ጭምር ከአጠናከሩት ለተሻጋሪነቱ አስተማማኝ መንገድ ይፈጥርላቸዋል። በዚህ ደግሞ ቢያንስ በቀጣዩ አመት የሚደረገውን የአዲስ አበባ ምርጫን ‹‹እንደሰርቶ ማሳያ›› የሙከራ ፕሮግራም ወስደው ራሳቸውን ሊፈተሹ የሚችሉበትን አጋጣሚ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ እንግዲህ መልካም ምኞቴ ነው። ሆኖም ‹‹የፖለቲካ ምህዳር መጥበብን›› ብቻ በመግለጫ እየተቃወሙ፣ በሰላማዊ የትግል ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ አማራጮችን ‹‹አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ›› እያለፉ፣ 150 ሰው ብቻ በተሰለፈበት ሰላማዊ ሰልፍ ‹‹ብርቱካን ትፈታ›› ተብሎ የተጠየቀውን አይነት ጥያቄ ያህል እንኳ ‹‹አንዷለም ይፈታ›› በሚል መድገም አቅቶአቸው እያየን ‹‹መጪው ጊዜ ለተቃዋሚዎች ጨለማ ነው›› ለማለት ነብይ መሆንን አይጠይቅም። ከዚህ በተረፈ ህዝቡ ከፓርቲዎቹ ቀድሞ ወደአደባባይ በመውጣት፡-

‹‹ገለል ይሻልሃል

ገለል ያለው መቶልሃል›› ያለ እንደሆነ የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ የሊቢያ ወይም የሶሪያ ከመሆን አይመለስም። በሊቢያ እና በሶሪያ ህዝባዊ አመፅ በተቀሰቀሰ ጊዜ የተፈጠረው ነገር ምንድር ነው? ብሎ መጠየቁ የተሻለ ተሞክሮ እንዲኖር ያስችላል። ምንአልባትም እንዲህ የሚል መልስ ልናገኝ እንችላለንና። በእነዚህ ሀገራት ህዝባዊ ተቃውሞውን መስመር የሚያሲዝ ጠንካራ ፓርቲ ባለመኖሩ፣ ህዝቡ በጎበዝ አለቃ ተደራጅቶ ከመንግስት ጋ መፋለሙ ሀገራቱ የመፈራረስ አደጋ ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል። በቱኒዚያ እና በግብፅ ግን የታየው የዚህ ተቃራኒ ነው። ምክንያቱም በሁለቱ አገራት የነበሩ ፓርቲዎች ምንም እንኳን በጠበበ ምህዳር እና በአምባገነን ስርዓት ውስጥ ቢሆኑም ከአብዮቱ በፊት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ራሳቸውን ከማጠናከር ያልሰነፉ ስለነበር ተቃውሞ ሲቀሰቀስ ከፊት መስመር ለመገኘት አላዳገታቸውም። እናም የፈነዳውን ህዝባዊ ቁጣ ተከትሎ ሀገሬው አደባባይ መዋል ሲጀምር ፓርቲዎቹ በቀላሉ

‹‹አንበሳው ጋሜ

አይዞህ ወንድሜ››ን እየዘፈኑ አብዮቱን ከመቀላቀል ያገዳቸው አልነበረም። ይህ ደግሞ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲኖር አስችሎአል። (...በአነሰተኛና ጥቃቅን መደራጀትም ስራ ነው፣ ኮብል ስቶን ማንጠፍም ስራ ነው፣ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋምም ‹‹ኢንተር ፕሩነር ነው›› /ስራ ፈጠራ ነው/ በሚል ስለተቋቋሙ ፓርቲዎች ሌላ ቀን እመለስበታለሁ)

# ጦማረ አሚን ...

ከገፅ 11 የዞረ

በልቤም ከቅድሙ የአሁኑ ዜማ ክብደት እንዳለው ይሰማኛል።

. . . ከአስቀያሚ የጥበብ ቀሚስ ስር ውብ ና ጠንካራ ቀጫጭን የሐር ክሮች አሉና። መፍሰስ ብቻ በሆነ የሕይወት ሕግ ውስጥ. . . ፀሐይና ጨረቃን መገደብ መሞከር (መመኘት) እርሱ ተራ ስንፍና ነው። ተራ ሰነፎችም የድሮ ዜማቸውን እስከ አሁን ያደምጡታል. . . ለራሳቸው ተራ ሽንፈትም 'ትዝታ' የሚል ተራ ስያሜን ይሰጣሉ. . . በሰነፎች የሕይወት መመሪያ ውስጥ 'ወንዙ ሳይደርስ መንገድ ላይ መቆም ይችላል' መንገድ ላይ መቆም ይቻላል የሚል መመሪያ ያለ ይመስላል።

እኛ በጊዜ ውስጥ አይደለም. . . እኛ በራሳችን ጊዜዎች ነን። በማንነታችን ወቅት ውስጥ ክረምትና በጋ. . . ጸደይና መኸር አሉ. . . ይህ በተፈጥሮ ሕግ ብቻ ሳይሆን በህልውና ምንነታችን ውስጥም አለ. . . ነፋሳት እያለን. . . የክረምት ያህል ጭጋጋማና ጭቃማ የሆነ ሕይወትን ልናልፍ እንችላለን። በእሳትነታችን. . . በተፈጥሮ ሕግ ከተመሰልንበት የጸደይ ብርሃናማና አበባማነት ይልቅ. . . እንደ መሬት ልንሆን እንችላለን። በጉብዝናችን የሸበትን፣ በምርኩዛችን የጎለመስን ልንሆን እንችላለን። የሕይወት የወቅቱ ዑደት ከየትኛው እንደሚጀምር. . . ወዴት እንደሚፈስ አናውቅም. . . በሕይወትና በተፈጥሮ ፍርርቅ መካከል ልዩነት ስላለ. . .

በሕይወት ሕግ የኖርናቸው ዕለታት ገድለናቸው የመጣናቸው ሬሳ ወቅቶች ናቸው። ወደ ፊት የሚመጡት ደግሞ ለመሞት የተዘጋጁ ጊዜያት. . . 1. . . 2. . . 3. . . መስከረም. . . ሐምሌ. . . ነሐሴ በየትኛው የዜማ ዓይነት ታጅበናል።

ሙዚቃው አራራይ ወይም ፍሱሐዊ ዜማ ሊኖረው ይችላል። ዝማሬው ግዕዝ ወይም ዕዝል ይሆናል. . . እኔም እኚህ ጣምራ መሃል አራት አይኖቼ ስምንት ጆሮዎቼ ሊመለከቱና ሊያስተውሉ ሊያደምጡና ልብ ሊሉ የሚሹት 'አሁን' የሚል ሙዚቃዬን ነው. . .

'አሁን' የሚለው ሙዚቃ ምንም እንኳ ከድፍርስ ውሃ. . . ከጢስና ከጉም. . . እንዲሁም ነጠብጣቡ ከበዛ ጨቅጫቃ የዝናብ ድምጽ ቢሰራም. . . ከተፈጥሮ ሳይሆን ከሕይወት ሕግ የተቀመረ ስለሆነ. . . እርሱን ማጣጣም እፈልጋለሁ. . .

'አንቺ ብቻ' የሚለውን ሙዚቃ. . . ልቀንሰው ነው። በአማናዊና በምሳሌያዊ መሃል ልዩነት አለና. . . ሕይወት ላይ የተቀነባበረ ሙዚቃ. . . መጠኑ ይቀነሳል እንጂ ፈጽሞ መጥፋት አይችልምና ያንን ቀንሼ ይህን እያሰላሁት ነው!። ካቻምና ብስቅም. . . የካቻምና ሳቄ የአሁን ፈገግታዬን እንዲጋርደው አልሻም። እኔ የአሁን ሰው ነኝና። ሙዚቃ ደግሞ ስሜትን አይከተልም. . . ሙዚቃ ስሜትን የሚያዝ ሌላ ስሜት ነውና. . . አረጋውያን ለወጣቶች በሆነ የሙዚቃ ሃሳብ ይውረገረጋሉ. . . ወጣቶችም ኖረው ባላጠነጠኑት የሙዚቃ ሃሳብ ኮረዶቻቸውን አቅፈው ግንባራቸውን ይቋጥራሉ. . . እኔም እንዲሁ ነኝ. . .

ከድፍርስ ውሃ የተጠመቀው የሕይወት ሙዚቃ ነፍሴን አላቆሸሻትም። ከትነትና ከጉም የተጨመቀው መንቻካ ዝናባማ ሙዚቃም አልቀዘቀዘኝም. . . ሙዚቃ የግል ስሜትን ሳትከተል ስሜትን እንደምታዝ ሁሉ.... የህይወት ወቅታዊ ዑደትም እንዲያ ነውና... ሸክላው እየተሽከረከረ ነው. . .

ቅድም ሲያቀነቅን የነበረው ሙዚቀኛ አሁንም እየተጫወተ ነው። የ'አሁን' ሙዚቃ አቀናባሪም የቅድሙን ሲጫወት የነበረው ነው. . . ሸክላው መሽከርከሩን አላቆመም. . .

እየተሽከረከረ የነበረው ሸክላ እየተሽከረከረ ቢሆንም ሲጫወት የነበረው 'አሁን' የሚለውን ሙዚቃ ግን ፈጽሟል። አሁን ምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ የለም። የዘፈን ቃልና ዜማም እንዲሁ። ሸክላው ግን እየተሽከረከ ነው። ያለ ድምጽ. . . (ሽሽሽሽ. . . ድምጽ ብቻ)

ጸጥታው አሁን ያለው የጊዜ አካል ነው። ይህች ድርጊት አልባ ጊዜ የሕይወታችን 'ትድምርት' ናት። በምንም ውስጥ የሚሆን ሁኔታ። ሁኔታው ግን ምንም ነው። ያለ ሙዚቃ ድምጽ እንደሚሽከረከረው ሸክላ. . . ያለሁኔታዎች የሆኑ ሁኔታዎች አሉን። እዚህ ጸጥታ መሐል 'ሕይወት ያለተግባርና ያለድርጊት ሕይወት ናት' የሚል እሳቤ ወደ አዕምሮዬ መጣ። (ከነበረው ሃሳቤ የተጋጨሁ ይመስለኛል)።

የሆነ ነገርን አለማድረግ ወይም ምንም አለማሰብ አለመኖር አይደለም። የጊዜ ብክነትም አይደለም። ምንም አለማድረግ ከንቱነት ከሆነ ያ ከንቱነት በራሱ የህልውና አካል ነው። ሸክላው ያለ ሙዚቃ ድምጽ እንደሚሽከረከር ሁሉ. . . ያለ ተግባርም ሆኑ የሕይወት ጊዜዎች አሉን።

በሸክላው ውስጥ ያለው የጸጥታ ጊዜ በራሱ የሸክላው የሕልውና ክፍል ነው። ያለተግባር የሆኑ ጊዜዎቻችንም በሕይወታችን ውስጥ ያሉ የሕይወታችን. . . ሕይወቶች ናቸው።

ፀጥታ ቀጣዩን ድምጽ መጥሪያ ደወል ነው። ትንንሽ ዝግታዎች ረዥሙን መንገድ የመጀመር. . . ሃይል የማከማቻ መንደርደሪያዎች ናቸው። ስለዚህም ምንም አለማድረግ የሆነ ነገር የማድረግ ሂደት ነው። ምንም የተደረገ ባይኖርም ዕንኳ. . . ሊደረግ የሚታሰብ አለ።

ቀጣዩ ሙዚቃ ምን እንደሆነ ባላውቅም. . . ባልሰማውም. . . ሸክላው ግን ከጸጥታው ኋላ የሚያሰማኝ ነገር እንዳለ አውቃለሁ። ቀጣዩ ሙዚቃ ግን አሁን ከማስተውለው ባዶነትና ዝመታ ግን አይበልጥም። አሁን ያለችው አሁን በምትመጣው አሁን እስትከደን ድረስ።

በሸክላው ተምሳሌትነት የማያት የሕይወቴ ባዶ የሆነች ባዶ የጊዜ ክፍል በራሷ ድምጽ ናት። በራሷ ሁኔታ ናት። በራሷ ድርጊት ናት. . . ምክንያቱም በፊደሎች መሃል ያሉት ክፍተቶች የፊደላቱ ውበቶች ናቸውና። ለምሳሌ አንድ የተወደደ ክቡር መጽሐፍ እያነበብክ ነው ብለን እናስብ መጽሐፉ እንዲህ ይጀምራል. . .

'የሆነ የሚወደድ ክቡር መጽሐፍ እያነበብክ ነው። እያነበብክ. . . እያስተዋልክ. . . እየተገረምክ የሆነ ምዕራፍ ላይ ልትደርስ አንድ ገጽ ይቀርሃል።. . . የጀመርከውን መጽሐፍ አጋምሰህ የደረስክበትን ጨርሰህ. . . የጨረስከውን ሥትገልጥ አምስት መስመር ፅሁፍ በስተግራህ በኩል ታገኛለህ።. . . በስተቀኝ በኩል ደግሞ ምዕራፍ ሰባት ብሎ የሚጀምር ይታያል። ለመጨረስ. . . ሰባተኛውን ለመጀመር. . . አምስቱን መስመር ጀመርክ. . .'

'የዕረፍት ስሜት ሳያስፈልገው አይቀርም። በድንግዝግዝ የማየት. . . ምንምን የማስተዋል ሁኔታ ውስጥ ነው። በእጁ ከያዘው መጽሐፍ ተነጥለው ሩቅ የተጓዙ ዓይኖች. . . ያለ ፊደል የሚያስብ ማንነት. . . ምን እንደሚያስብ የማያውቀው 'እኔነት' ውስጥ ነው። በምንም ውስጥ ነቃ ወይንም ከምንምነት ነቃ. . . ወደ ተገለጠለት አስተዋለ. . . አንድ ሊያደርገው የሚገባ ነገር አለ. . . ምርጥ ሙዚቃ ምን ዓይነት ነው? የሚለውን ማሰላሰል. . .

# ከሕይወት የሚበልጥ ዓላማ የለም



በእውቀቱ ስዩም

ዓለማየሁ ገላጋይ ስለጃፓንና ስለቴዎድሮስ ክርክር አስጀምሮኝ ነበር። ባለፈው ሣምንት ጃፓንን በጓሮ በር አሰናብቶ አጤ ቴዎድሮስን ብቻ ይዞ ጠበቀኝ። ክርክሬን ዛሬ እቋጫለሁ። ባለፈው ሣምንት የተሰጠኝ ምላሽ ምንም እንኳን ከአፈጮሌነት ሙሉ በሙሉ የፀዳ ባይሆንም ወደ መከራከርያው ርዕሰ ጉዳይ ቀረብ የሚሉ ነጥቦችን ይዟል። ጥሩ ሙከራ ነው።

ዘግይቶ ክርክራችንን ለታደመ አንባቢ የኔ አቋም ‹‹ዳግማዊ ቴዎድሮስ የሞራል አርአያ ተደርገው የሚቆጠሩ አልነበሩም። ከዘመነኞቻቸው ጋራ ሲነፃፀሩ ንጉሡ በሞራል ኋላቀር ነበሩ›› የሚል ነው።

በሞባይል በደረሱኝ አንዳንድ መልእክቶች እንደተረዳሁት ሐተታዬ ያስከፋቸው ሰዎች አሉ። ግን ምን ይደረግ? ሰዎችን ሳያስከፉ እውነት መናገር፤ ሳይረጥቡ መታጠብ አይቻልም››

በዘመናችን ታሪክን የፖለቲካ ገባር የማድረግ አዝማሚያ አያለሁ። አዝማሚያው የጌቶችም የሽፍቶችም ነው። በኔ ግምት ይህ አዝማሚያ የታሪክን ንፁህ ግንዛቤ ይበክላል። ነገሮችን የማወቅ የጋለ ፍላጐት ብቻውን ታሪክን ለማጥናት በቂ ይመስለኛል።

ወደ ክርክሩ።

ዓለማየሁ ያጤ ቴዎድሮስን የሥነ ምግባር አርአያነት ለማሣየት የሚከተለውን አንቀጽ ጠቅሷል።

**‹‹…ቴዎድሮስ ኃይንት ሠፍረው ሳለ ወታደሮቻቸውን በባላገሩ ላይ ተሠሪ አገቡ። ባላገሩ እንዲቀልብ በየቤቱ ማስገባት ማለት ነው። ተሠሪ ከገቡት ወታደሮች መካከል አንዱን ባላገር ገደለው። የሟች ወገንም ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ አመለከተ። ቴዎድሮስም ወታደራቸውን ሁሉ አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን አውጣ ብለው ያዙት። ወታደሩ በመላው አድሞ ገዳዩን አላየንም እያለ በቁስ እየተገዘተ ወጣ። የሟች ገዳይ ወታደር በመጥፋቱ ቴዎድሮስ ተናደው ‘ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ ነኝ ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል’ ብለው ተነስተው ለከሳሹ ነገሩት። ከሳሹም እኔ ንጉሥ መግደል አይቻለኝም አለ። ቴዎድሮስም እንግዲያውስ ደም በከንቱ አይቀርም ብለው ለሟች ወገን የደም ገንዘብ ዋጋ ሰጥተው ሸኙት››**

ይሄን ትረካ ያቀረበው የቴዎድሮስን ‹‹የሥነ ምግባር ሥልጣኔ›› ያሳይልኛል ብሎ ነው። እስቲ የጥቅሱን ቡለን ፈታተን በብልት በብልት እንፈትሸው።

(ሀ) በጥቅሱ ውስጥ ቴዎድሮስ ‹‹ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ›› የሚል ግፈኛ ሕግ ማውጣታቸውን ይናዘዛሉ። ይህም፣ ንጉሡ ወታደሮቻቸውን በደመወዝ ያስተዳድሩ ነበር የሚለውን ፈጠራ ያስተባብላል።

(ለ) ግፈኛው ሕግ ለወታደሩ ገደብ የለሽ ሥልጣን ሰጥቶታል። ገደብ የለሽ ሥልጣን ያለገደብ ያባልጋል። እንግዳው ባለቤቱን እስከመግደል ደርሷል። ቴዎድሮስ አቤቱታው ሲቀርብላቸው የችግሩ ምንጭ ግፈኛው ሕግ መሆኑን ተረድተዋል። ይሁን እንጂ ሕጉን ማፍረስ ሲገባቸው አላደረጉትም። በአለቃ ዘነብ ትረካ መሠረት በኃይንት ይህ ክስተት ከተፈፀመ ከወር በኋላ በጨጨሆ፣ ወታደር በባላገር ቤት ጥገኛ ሕዋስ ሆኖ እንዲገባ ተፈቅዶለታል። ሕጉን ያፈረሡት ካጤ ቴዎድሮስ የመአት በትር ያመለጡት እምዬ ምኒልክ ናቸው።

(ሐ) ንጉሡ ደመኛህ እኔ ነኝ ብለው ባላገሩ እንዲገድላቸው መጋበዛቸው የይስሙላ ይሁን የምር አይታወቅም። ግን የምር ሆኖ ተጋባዡ ግብዣውን ቢቀበል ኑሮ መፍትሄ ይመጣ ነበር? አይመስለኝም። ችግሩ የሚፈታው ሕጉን ባጠቃላይ በማስወገድ እንጂ ንጉሡን በማስወገድ አልነበረም።

ባላገሩ የንጉሡን የግደለኝ ግብዣ አለመቀበሉ ‹‹በተቀባው ላይ እጅህን አታንሣ›› የሚለውን የጊዜውን ሕግ አክብሮ ነው። ታዲያ ጥቅሱ የሚያስረዳው የንጉሡን ስነ ምግባር ታላቅነት ነው ወይስ የስም የለሹን ባላገር ጨዋነት? ያለጥርጥር ሁለተኛው መልስ ነው።

ቴዎድሮስ ከባላገሩ ጋር ያላቸው የባላንጣነት ግንኙነት ሊቃውንት ከሚነግሩን ፈርቀዳጅነታቸው ጋር የሚጣጣም አይደለም። ሌላው ቀርቶ ከዘመነ መሣፍንት ትልልቅ መሪዎች ፖሊሲ ጋር ስናነፃፅረው ፖሊሲያቸው ኋላቀር ይሆንብናል። ከዘመነ መሣፍንት የኢትዮጵያ ዋና መሪዎች አንዱ የሆኑት ራስ ጉግሣ የባላገርን ንብረት በጉልበት ለሚቀማ ወታደር ከባድ ቅጣት ደንግገው ነበር። ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ የሚሉትን እንስማ፡-

**‹‹…ራስ ጉግሣ መሬት የረቢ ናት። መሬት ያለው የለም። አሁንም ዶሮ ያረደ በግ ይከፍላል። በግ ያረደ በሬ ይከፍላል። በሬ ያረደ የነፍስ ዋጋ ይከፍላል ብሎ አዋጅ ነግሮ አገሩን አለማው››** (ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ገፅ 119)

ስማቸው የማይታወቅ የቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ፀሐፊ እንደዘገቡት መይሣው ካሣ ለወታደሮች የሰጡት ትዕዛዝ ‹‹የምትበላውን ያቅምህን ብላ። ቋንጣህን ዘልዝለህ አድርቅ። የተረፈውን ላም ግን እያረድህ መሬት ቆፍረህ ቅበረው›› የሚል ነበር። ወታደሩ ከስንቁ የተረፈውን በሬና ላም መሬት ቆፍሮ የሚቀብረው ጥጃ ሆኖ እንዲበቅልለት አይደለም። ባላገሩን ድራሹን ለማጥፋት ነው።

ቫልድማየር በጊዜው እንደተመለከተው የንጉሡ ወታደሮች በቅሎአቸውንና ፈረሶቻቸው የሚያሠማሩት በመስክ ላይ ሳይሆን በገበሬው አዝመራ ላይ ነበር። ገበሬው በለቅሶ ቢለምን የሚራራለትም ሆነ የሚሰማው አልነበረም።

ዓለማየሁ፡- አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ሰዓታቸው የእንግሊዝ እሥረኞችን ሳይገድሉ ማሰናበታቸውን ይጠቅሳል።

**‹‹…አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በመጨረሻ የሽንፈት ሰዓት ላይ ሆነው ከአሽከሮቻቸው አንድ አማራጭ ቀረበላቸው አማራጩን ያቀረቡት ራስ እንግዳ ነበሩ። ‹‹ለምን ያዝናሉ? እነዚህን ነጮች መልሰን እናምጣና ገድለናቸው እንሸሽ ወይም ተዋግተን እንሙት።›› አሉ። አጤ ቴዎድሮስ ተስፋ ከመቁረጣቸው ብቻ ይሄንን አማራጭ አልተቀበሉትም። አጤው ለአላማ እንጂ ለበቀል አይገድሉም። በቁጣ ራስ እንግዳን እያዩ እንዲህ አሉ ‹‹…አንተ አህያ ባለፈው ሁለት ቀን ውስጥ የፈጀሁት ሰው አይበቃምን? እነዚህን ነጮች ገድዬ አበሻን በደም እንዳጥባት ነው የምትፈልግ?››**

ያሠመርሁት እኔ ነኝ። ያሠመርሁትም የተጠቀሰው ትረካ ከተሠመረበት ትርጓሜ ጋር ያለውን መራራቅ ለማሳየት ነው። አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ሰዓት ነጮችን ማሰናበታቸው ጥሩ አድርገዋል። ግን በሞቴ ይሄ ትረካ ‹‹አጤው ለበቀል አይገድሉም›› የሚለውን ሐሳብ ለመደገፍ የሚቀርብ ነው? አጤ ቴዎድሮስ በትረካው ውስጥ በራሳቸው አንደበት በመጨረሻ ሰዓት ብዙ ሰው መፍጀታቸውን በፀፀት እየተናዘዙለት ዓለማየሁ አይሰማም። ምን ይሻላል? ንጉሡ የእንግሊዝን መቅረብ ሲያዩ በመቅደላ ያሉትን አያሌ እሥረኞች እጅና እግር እየቆረጡ ገደል ጨምረዋቸዋል። ይሄ ጭፍጨፋ በቀል ካልሆነ ዓላማው ምንድነው?

የመጨረሻው የክርክር ነጥብ ለበቀል መግደል ክፉ ሲሆን ለዓላማ መግደል ግን ጥሩ ነው የሚል አደገኛ መልእክት ያስተላልፋል። አንድ የደም ጥማት ያለበት (ሴዲስት) ግለሰብ ጥማቱን ለማርካት የሚያስፈልገው፣ ያገር መሪ መሆንና ለወንጀሉ መሸፈኛ አንዳች አላማ መፍጠር ሲሆን ነው።

ግፍን የክብር ልብስ በማልበስ፣ ግፍን ከባሕላችን ማስወገድ አንችልም። እቅጩን ለመናገር ከሕይወት የሚሻል ዓላማ በዚህ አለም ላይ የለም። ታላቅ ዓላማ ላይ ለመድረስ የትኛውንም መንገድ መያዝ ተፈቅዷል ለሚሉ ሰዎች ያቶ ሀዲስ አለማየሁን ጥቅስ ጋብዤ ልሰናበት።

**‹‹…ክፉ መንገድ እመልካም ግብ አያደርስም። ክፉ ሥራ እንደተኮሱት ጥይት አላማውን ይገድላል። ክፉ ሥራ ሠርቶ መልካም መልካም ውጤት አገኛለሁ ማለት እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ለማምረት እንደ መመኘት ነው።››**

(የልምዣት ገፅ 217)

# ድህረ-ኢህአዴግ …

ከገፅ 9 የዞረ

ሊኖሩን እንደሚችሉ አይነገረንም። እንደ 2ኛ ክፍል ተማሪ፡- እውነት/ሐሰት ብቻ ብለህ ምረጥ እንባላለን። እኛም ይሄው ስለሚቀለን ለስንፍናችን ጥሩ ሰበብ አገኘን ማለት ነው። የጠያቂዎቻችንን ፊት እና የሃይል ሚዛን አይተን የሚያዋጣ የመሰለንን እንመርጣለን። በዚህ ረገድ የባለቤቱ ግላዊ የፖለቲካ ስህተቶች እንደተጠበቁ ሆነው ‹‹የ3ኛ አማራጭ መፍትሄን›› ሊያቀርብ የሞከረውን የኢዴፓው አቶ ልደቱ አያሌውን አማካይ መስመር ከገዢው ፓርቲ በላይ ሊያጠፉት የተነሱት የተቃውሞ ጐራ ውስጥ የተከተሙት የ60ዎቹ ትውልድ አባላት መሆናቸውን ስንገነዘብ፤ ከፖለቲካዊ ፋክክርም በላይ እንደ ህዝብ የሚንፀባረቅብንን ወደአንድ ጐራ ብቻ የመከተት ጠርዘኛ አቋማችንን እና ከመመርመር ይልቅ አሉባልታ የመቀበል ጠባያችንን ያመለክታል። አሉባልታ ደግሞ መመርመር የማይሻ የሰነፍ ሰው የመረጃ ምንጭ ነው።

ስለዚህም በእውር-ድንብር ጉዞ የተማሩ አፈ-ጮሌዎች ሲያታልሉን እንኖራለን። ሚዛን አንጠብቅም፤ አናመዛዝንም። ካንዱ ጫፍ ወደሌላኛው ስንንገዋገዋ አገራችንንም እኛንም ለአደጋ አሳልፈን እንሰጣለን። ከእኛ የተለየ ሃሳብ ያለውን በመናፍቅነት እየፈረጅን ውጉዙ-ከ-መአሪዮስ ስናደርግ የበለጠ ወደ ጽንፈኝነት እየገፋነው አቻችሎ የሚያኖረንን መሃከለኛ መንገድ እናጠፋለን።

እርስ-በርሳችንም በውሃ-ቀጠነ ምክንያት የፖለቲካ ፀጉር ስንሰነጥቅ እና ስንሻኮት በራችንን ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ-ገብነት እናመቻቻለን። እዚህ ጋር አንድ ወዳጄ ያጫወተኝን ታሪክ ልጥቀስ። እነሆ፡-

ጃርቶች በብርድ ወራት ብቻቸውን ሊኖሩ አይችሉም። በመሆኑም ከቅዝቃዜ ለማምለጥ ሲሉ እርስ-በርሳቸው ተጠጋግተው እና ክብ-ሠርተው ይሟሟቃሉ። ነገር ግን የጃርቶች እሾህ የሚዋጋ በመሆኑ ምቾትም አይሰማቸውም። እሾሁ ወጋን! ብለው ቢነጣጠሉ ደግሞ የሰው ጦር እያደነ ይጨርሳቸዋል። በመሆኑም፡- ጃርቶች በዚች ምድር ሲኖሩ ከእሾህና ከጦር መምረጥ ይኖባቸዋል። ታዲያ እኛ የሰው ልጆ የሆንን ኢትዮጵያውያን ከጃርት እናንሳለን?

በታሪካችን ውስጥ በተከሰቱ ክፉ ገጠመኞች የተነሳ እኛና/ሌሎች (We/others) በሚል የከረረ የልዩነት ድንበር ተከልለን በአሉታዊ የቅራኔ ትስስር የተያያዝነው የእምነት እና የብሔር ቡድኖች፤ ከ20 ዓመታት ወዲህ በተከሰቱ ዓለማዊ እና ሃገራዊ የፖለቲካ ክንውኖች ሳቢያ ይህን የልዩነት መስመር ያደመቅነው ይመስለኛል። የመንግስትም ሞራል-አልባ የፖለቲካ አጨዋወት በሁሉም እሴቶቻችን ላይ ለሥልጣኑ ሲል ቁማር በመቆመሩ ፍጥጫችንን አባብሶታል። በውጤቱም፡- ልዩነቶቻችን በረከቶች እንጂ መርገምቶች ሳይደረጉ በአንድ አገር ጥላ ስር የሚያስኖሩን አገራዊ የዝምድና ገመዶች እየላሉ እንደሆነ ተሰምቶኛል። ልዩነቶቻችን ላይ በማተኮር ተመሳሳይነታችንን የዘነጋነው ይመስለኛል።

መለያየት እጅግ የቀለለ የሰነፍ ሰው ስራ ነው። ማፍረስ አይከብድም፤ ትዕግስት አይጠይቅምና! ይኸው በጉራፈርዳ እንዳየነው በ24 ሰዓት ውስጥ ሁሉንም መመነቃቀር እና መንግሎ ሜዳ ላይ መጣል ይቻላል። አንድ መሆን ግን የትጉህ ሰዎች መልካም ፍሬ ነው። መገንባት ፈታኝ ነው- ጥበብ ይጠይቃልና! ህብረት በፍቅር የመዋሃድ ጉዞ ነው። ዳገት ቁልቁለት፣ አባጣ ጎርባጣ ቢኖረውም የአብሮነት ጉዞ ብቻ ከማዝገም ሺህ ጊዜ ይልቃል። ምሉዕነት ከአብሮነት፤ ጉዶሎነት ከብቸኝነት ይመጣሉና እኛ ግን የቀደመውን መልካም ነገር ብንመኝ ይበጀናል። አዎ በአብሮነት ምሉዕ መሆንን በነፃ-ፈቃዳችን ብንመርጥ ህይወታችን ይበለፅጋል። እኛ ከተዋደድን ቋንቋም፣ ብሔርም፣ ዘርም፣ ሃይማኖትም የህይወታችን ማጣፈጫ ቅመሞች ይሆናሉ። ምክንያቱም አንዳቸውም ስንኳ ከፍቅር አይበልጡምና! ፍቅር ደግሞ ከልብ እምነት እንጂ ካይምሮ ጥርጣሬ ፈልቆ አያውቅም።

ፕሮፌሰር መስፍን በ1986 ዓ.ም. ባሳተሙት ‹‹ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?›› በሚለው መጽሐፋቸው፡- ‹‹…የኢትዮጵያዊነት ችግር ኢትዮጵያ አይደለችም፤ ችግሩ የስርዓት ችግር ነው። የቤቴ መቃጠል ለትኋኑ በጀኝ እንዳለው ቂል እንዳንሆን።…›› ሲሉ ካስጠነቀቁ በኋላ በዛው ገጽ 32 ላይ ትንሽ ወረድ ብለው ደግሞ፡- ‹‹…ሆኖም የኢትዮጵያ ታሪክ ሊያስተምረን እንደሚችለው ኢትዮጵያዊነት እንደላስቲክ ነው። ሲስቡት ይሳባል፤ ሲለቅቁት ይሰበሰባል። ማለት -ይሳብና ይሳሳል እንጂ አይበጠስም።›› ብለው ነበር። ታዲያ ፕሮፍ በአዲስ ጉዳይ መጽሔቱ ቃለ-ምልልስ ላይ ለምን ይሄን ያህል ተስፋቸው ተሟጠጠ?

ምስጋና- አስጀምሮ ሳይቆረጥ ላስጨረሰኝ የብርሃንና ሰላም ጌታ!


# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

## በቅርቡ በወጣው የሊዝ አዋጅ ላይ ያተኮረ

## ‹የኢትዮጵያ መሰረታዊ የሊዝ ሕግ ሀሳቦችና የሚያስከትላቸው ችግሮች›

በሚል ርእስ

መጽሐፍ ታትሞ በገበያ ላይ ዋለ!

በመጽሐፉ አዲሱ የሊዝ አዋጅ፣

- በሕገመንግስቱ የተረጋገጠውን የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት ከህዝብ ጥቅምና መብት ጋር በተጣጣመ መልኩ-ሚዛናዊ ከማድረግ አንጻር ምን ያህል ተሳክቶለታል?
- የነባር ባለይዞታዎችን መብት በማስፋትም ሆነ በማጥበብ ምን አዲስ ነገር ይዞ መጣ?
- መሬትን በሊዝ ይዞ የሚጠቀም ሰው መብትና ግዴታዎቹ ምንድ ናቸው?
- የሊዝ አዋጁ ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሙስና ተግባራትን ይቀንሳል ወይስ ያባብሳል?
- ከሊዝ አዋጅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ስርአት ፍትሀዊ ነው ወይ?
- በአዋጁ ላይ ምን አይነት ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል?

የሚሉና ሌሎች በርካታ በህዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎችን በማንሳት ለጥያቄዎች የተብራራ ምላሽ እንዲሁም የማሻሻያ ሀሳቦችን ይዞላችሁ ቀርቧል።

በመካሻ አበራ (ኤል.ኤል.ቢ)




መጽሀፉን ገዝተው ያንብቡ!
ዋና አከፋፋይ ዓይናለም መጻሕፍት መደብር

# ግልገል ጊቤ ሶስትና የፈዘዘው ዲፕሎማሲ



በሙስነህ አያሌው

muleayalew@yahoo.com

አይካል አንጀሊ ትባላለች። የ30 ዓመት ኬንያዊት ወጣት ስትሆን ከዛሬ ሦስት አመት በፊት የግልገል ጊቤን ቁጥር ሶስት ፕሮጀክት የሚቃወም "Friends of lake Turkana" የሚል ድርጅትን በማቋቋም በአለም አቀፍ ደረጃ ግድቡ ከባቢያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን ሊያስከትል እንደሚችል አገራዊና አለም አቀፋዊ ቅስቀሳዎችን አካሂዳለች። በስተመጨረሻም በዚህ ወር ‹‹ጎልድማን ኢንቫሮመንት አዋርድ›› የተሰኘ አለም አቀፍ ሽልማት ተሸላሚ ሆናለች። ስራዋ በተቋሙ ሽልማት ከማግኘቱ በተጨማሪም ሌሎች ዘርፈ ብዙ ውጤቶች እንደሚኖሩት አመላካች ሆኗል።

ከዚህ በፊት የኬንያ የመንግስት ባለስልጣናት ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ላይ የምታካሂደውን ግድብ ከመደገፋቸውም በተጨማሪ ወደ ፊት ከግድቡ በሚገኘው ኃይል ተጠቃሚ እንደምትሆን የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸው ይታወቃል። በተጨማሪም ይህንን ግድብ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክና ሌሎች ለጋሽ አገራት በእጅጉ ሊደግፉት ቃል መግባታቸውም የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። የዚህች ወጣት ኬንያዊት ጥረት ግን ነገሮችን ሁሉ እንዲቀያየሩ አድርጓል። በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ የኬንያ ባለስልጣናት አገሪቷ ካለባት የኃይል አቅርቦት ችግር ትላቀቃለች ብለው ተስፋ ባደረጉት ግድብ ላይ ያላቸው አቋም በእጅጉ እየተቀየረ መጥቷል። ይህ የአመለካከት ለውጥ በቀጣይ በሁለቱ አገራት መካከል ሊፈጠር የሚችለውን የደህንነት ስጋት እንድንመረምር ያደርገናል። ከዚህ በተጨማሪም ግድቡን ለመደገፍ ቃል የገቡት የልማት ባንኮች በማፈግፈጋቸው ምክንያት ግድቡ ያልቃል ተብሎ ከታቀደለት ጊዜ በላይ እንደሚፈጅና ስራው እንደሚጓተት ይጠበቃል።

እነዚህ ወጣት ኬንያውያን ከሌሎች የአካባቢ መብት ተሟጋች ቡድኖች ጋር በጋራ በመሆን ያስገኙት ውጤት በቀጣይ ለመስራት ለታሰቡት ፕሮጀክቶች መተማመኛ እያሳጡን ከመምጣታቸው በተጨማሪ እንደ አገር መመለስ የነበረባቸውን ጥያቄዎች እንድንመረምር እድሉን ይሰጠናል። ተሟጋች ቡድኖች ያቀረቡትን መከራከሪያ በአንድ ወገን፣ መንግስት ሊወስዳቸው ይገባሉ የምላቸውን የመፍትሄ አማራጮች በሌላ በኩል በመውሰድ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊተኮሩ ይገባቸዋል የምላቸውን አንዳንድ ነጥቦች እጠቅሳለሁ።

በአጠቃላይ ከግልገል ጊቤ ቁጥር ሶስት ግድብ ይገኛሉ ተብለው ከሚጠበቁት ትሩፋቶች ውስጥ በዋነኝነት ተጠቃሽ ከሆኑት መካከል ቀዳሚው ከግድቡ ግንባታ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል ሲሆን፤ በተደጋጋሚ አካባቢውን እያጠቃ የሚገኘውን ጐርፍ መከላከል መቻሉ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠ ግብ ነው።

### የግድቡ ተስፋዎች

ግድቡ በዋናነት የተቋቋመው የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማመንጨት ነው። የዚህ ኤሌክትሪክ ምርት ተጠቃሚ የሚሆኑት በዋነኝነት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሶስት ጐረቤት አገራት ናቸው። ግድቡ ተጠናቆ ስራውን ሲጀምር ኢትዮጵያ ከሚገኘው አጠቃላይ የኃይል ምርት(1870 ሜጋ ዋት) ውስጥ ግማሽ ያህሉን ስትወስድ የተቀረውን ግማሹን ደግሞ ኬንያ (500 ሜጋ ዋት)፣ ሱዳን (200 ሜጋ ዋት) እና ጅቡቲ (200 ሜጋ ዋት) ያህሉን ይከፋፈላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ይህንን እንደ አንድ ጥቅም አድርገን ከወሰድን አገራችን ከሁለት ነገሮችን አንፃር መጠቀም ትችላለች የሚል እምነት አለኝ። የመጀመሪያው ጥቅም የግድቡን መጠናቀቅ ተከትሎ ከሚገኘው የኃይል አቅርቦትና ለጐረቤት አገራት ተሸጦ የሚገኘው ገንዘብ ሲሆን በአመት በአጠቃላይ ወደ 407 ሚሊዮን ዶላር ያህል እንደሚገኝ የተሰሩ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ሁለተኛውና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊቀርብ የሚችለው በጐረቤት አገራት ላይ የምናገኘው የፖለቲካ የበላይነት ትርፍ ነው። በዘመናዊ አለም ኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ጐን ለጐን ተያይዘው የሚሄዱ እውነቶች ናቸው። በኢኮኖሚ ኃያል የሆነች አገር በፖለቲካው ላይ የሚኖራት ተፅዕኖም በቀጥታ የሚታይ ነው። በተለይ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ አገራችን የበላይ ሆና ያላትን ቦታ በበላይነት አስጠብቃ ለመጓዝ ያስችላት ዘንድ የቀጠናውን አገራት በአንድም ይሁን በሌላ በኢኮኖሚ ረገድ በኢትዮጵያ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ማድረግ አዋጭ ፖሊሲ ነው። በተለይ በአሁኑ ጊዜ ለኢኮኖሚ ዋነኛ መሰረት ነው የሚባለው የኃይል አቅርቦትን በሚመለከት ሰፊ ፍላጐት ያለ ሲሆን ይህንን ለማሟላት ብሎም ሌሎች ፈላጊ አገራትን በእጅ አዙር ለአገራችን ፖለቲካ አጋር እንዲሆኑ ለማበረታታት ይቻል ዘንድ የኃይል አቅርቦት የሚኖረው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም።

ግድቡ ኃይልን ከማመንጨቱም በተጨማሪ ሊያከውናቸው ካቀዳቸው ተያያዥ ፕሮግራሞች መካከል በየአመቱ አካባቢውን እያጥለቀለቀ ያለውን የጐርፍ አደጋ መታደግ የሚለው ነው። ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በኦሞ ሸለቆ አካባቢ የሚገኙ አካባቢዎች በአንድም ይሁን በሌላ የዚህ ችግር ሰለባ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም አካባቢውን በተደጋጋሚ ከሚደርስበት የምግብ አቅርቦት እጥረት እና የንፁህ የውሃ መጠጥ ችግርንም ይቀርፋል የሚል ሰፊ እምነት አለ።

### የቱርካና ፖለቲካ

በኦሞ ወንዝ ላይ ግድብ ሊካሄድ ነው ከተባለ ጀምሮ በኬንያ የተለያዩ የአካባቢ ተሟጋቾች ቅሬታቸውን ወደ አደባባይ ማውጣት ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስት እቅዱን ይፋ ሲያደርግ የቱርካናን አካባቢ ወክሎ በኬንያ ፓርላማ የተቀመጠው ግለሰብ ‹‹በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ልናደርግ እንደምንችል ማሳወቅ ያስፈልጋል። እስከዛሬ ኢትዮጵያ በአባይ ላይ አንድም አይነት እንቅስቃሴ ለማድረግ ያልደፈረችው ግብፅን ስለምትፈራ ነው። እኛም ይህንን ልናደርግ ይገባል።›› ማለቱን እናስታውሳለን። ከዚህ ንግግር በመቀጠል የአካባቢውን ህዝብ ሰብዓዊ መብት ለመጠበቅ በሚል የተለያዩ የአካባቢ ቡድኖች ተዋቅረው ሙግታቸውን ወደ መድረክ በማምጣት በአገራችን እቅድ ላይ ሰፊ ዘመቻ በማካሄድ ቅስቀሳ አድርገዋል። እቅዳቸው በአብዛኛው ተሳክቶላቸዋል። እነዚህ የአካባቢው ተሟጋች ቡድኖች በቱርካና ኃይቅ እና በዙሪያው ላይ ባሉ የማህበረሰብ ቡድኖች ላይ ይደርሳል ያሉትን ችግር አንድ በአንድ ለአለም ለማስረዳት ጥረዋል። ዋና ዋና የሚባሉትን መከራከሪያዎቻቸውን እንይ።

የመጀመሪያው ስጋት የቱርካና ኃይቅ መጠኑ ይቀንሳል የሚለው ነው። የቱርካና ኃይቅ አሁን ካለው መጠን ግድቡ ተሰርቶ ሲጠናቀቅ ከሁለት እስከ አስር ሜትር የሚጠጋ ቅናሽ እንደሚያሳይ የጠቆሙ ሲሆን ይህም ህይወታቸውን በኃይቁ ዙሪያ ባደረጉ 500,000 የሚሆኑ ነዋሪዎች ላይ ውጤቱ አሉታዊ ይሆናል የሚል መከራከሪያ አላቸው። በተጨማሪም የውኃው መጠን መቀነስ በቀጥታ ውኃው በውስጡ ያለውን የጨው መጠን እንዲጨምር ስለሚያደርገው ለመጠጥነት መጠቀም አስቸጋሪ ይሆናል። አሁን ባለው መረጃ የቱርካና ኃይቅ በውስጡ በሊትር 2332 ሚሊ ግራም የሚሆን ጨው የያዘ ሲሆን ግድቡ ተገንብቶ ሲጠናቀቅ የውሃው መጠን በመቀነሱ ምክንያት የጨው መጠኑ ከነበረበት በመጨመር በሊትር 3397 ሚሊ ግራም ይሆናል የሚለው አንደኛው የአካባቢ መብት ተሟጋች መከራከሪያ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ አለምን ለማሳመን እየተጠቀሙበት ያለው መከራከሪያ ግድቡ እስኪገደብ ድረስ ያለው ክፍተት የሚያደርሰው ጉዳት ነው። አጠቃላይ ግድቡ ይይዛል ተብሎ የሚጠበቀው የውሃ መጠን ደግሞ ከ11.75-14 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ነው። ይህን ያህል መጠን ያለው ውኃ ለማቆር ቢያንስ ከሁለት እና ሶስት ክረምት ወራት ያላነሰ ጊዜን ይፈልጋል።ውኃው መጠራቀም ከጀመረ ጊዜ አንስቶ ለሶስት ተከታታይ አመታት የቱርካና ኃይቅ ያጠራቅም ከነበረው የውሃ መጠን በ50 ሴ.ሜ እንዲቀንስ ያደርገዋል። ይህ መቀነስ ቀድሞ ኃይቁ የነበረውን ጠቀሜታ በእጅጉ እንዲቀንስ ስለሚያደርገው በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳርፍ ሸንጣቸውን ገትረው ተከራክረዋል። ከዚህ በተጨማሪም ግድቡ የተገነባበት አካባቢ የተፈጥሮ ችግር አለበት የሚለው ሌላኛው መከራከሪያቸው ነው። እንደ ሪፖርቱ ትንታኔ ከሆነ ማጠራቀሚያው በውስጥ የያዘውን የውኃ መጠን በተለያዩ ምክንያቶች ከያዘው ከ50-75% የሚሆነውን ሊያጣ ይችላል ይላል። በተለይ አካባቢው ለመሬት መንሸራተት፣ ለመሬት መንቀጥቀጥ እና የድንጋዩ ባህሪ አመቺ አለመሆን ግድቡ የታቀደለትን የኃይል ማመንጨት ተግባር እንዳያከናውን እንደሚያደርገው ጠቅሰዋል። ስለዚህ ኢትዮጵያ ለራሷ ተርፎ ለጐረቤት አገራት እሰጠዋለሁ ያለችው የኃይል አቅርቦት በመረጃ በተደገፈ ጥናት ላይ የቆመ አለመሆኑን በማሳየት የተለያዩ ለጋሽ አገራትን ለማሳመን ተጠቅመውበታል።

### አካባቢያዊ ስጋቶች

በግልገል ጊቤ ሶስት ላይ የኬንያ ተሟጋቾች የሄዱበት መንገድ አዋጭ መሆኑን በተግባር አሳይተዋል። በእርግጥ የተጠቀሱት ስጋቶች ዞሮ ዞሮ የሚጠቅመውም የሚጐዳውም በሁለቱ አገራት ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ነው። በተለይ በድንበር አካባቢ። የእነዚህ ሁለት የተለያዩ ማህበረሰቦችን ጥቅም የመጠበቅም ይሁን የማስተዳደር ኃላፊነት የሁለቱ አገራት መሪዎች ነው። አሁን ባለው መረጃ የግልገል ጊቤ ፕሮጀክትን ለግጭት ቅርብ የሚያደርጉት የተለያዩ ምክንያቶች እየተፈጠሩ እንደሆነ ነው። የግልገል ጊቤ ሶስት ፕሮጀክት ከላይ ከተጠቀሱት ሰፋፊ ችግሮች ጀርባ ሌሎች ተያያዥ ጦሶችም ሊኖሩት እንደሚችሉ ቆም ብሎ መመርመር ተገቢ ነው።

የመጀመሪያው ችግር ግድቡ መገንባት ከጀመረ ከሁለት ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥናትና ውይይት እንዲደረግ በር መከፈቱ ጉዳዩን የዘገየ የሚያደርገው ሲሆን ሁለተኛው ችግር የአካባቢው ህብረተሰብ ስለግድቡ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን ነው። የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ግድብ ዙሪያ የጠራ አመለካከት መፍጠር እስካልቻለ ድረስ በተዘዋዋሪ በአገር ውስጥም ይሁን ከውጭ ግንኙነት አንፃር ሁለት ተግዳሮቶች መግጠማቸው አይቀርም።

በኦሞ ወንዝ አቅራቢያ በግድቡ ግንባታ ምክንያት ችግር ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ የሚባሉ ወደ ስምንት የሚጠጉ የብሔር ቡድኖች አሉ። (ሙርሲ፣ ቦዲ፣ ሙጉጂ፣ ካራ፣ ሐመር፣ በሻዳ፣ ኛንጋቶሞ እና ዳስነች ናቸው)። እነዚህ ብሔሮች በግድቡ ዙሪያ ባላቸው አመለካከት፤ ከመንግስት ጋር በቅርበት ተከታታይ ውይይት ስለማድረጋቸው ጥያቄ አለኝ። መንግስት ስለፈለገ ብቻ ማህበረሰቡን ከመኖሪያ ቀያቸው አፈናቅሎ የፈለገውን ልማት ማከናወን ይችላል የሚል ህገ-መንግስታዊ ድጋፍ የለውም። ግድቡ ተጠናቆ ስራ ሲጀምርምር በተጨማሪነት ለታቀደው የጥጥ እና የሸንኮራ አገዳ ልማት (444,500 ha) የነዋሪዎቹ መሬት ተፈላጊ መሆኑ አይቀሬ ነው። ይህ ደግሞ ሌላ የሰፈራን ፕሮግራም በኦሞ ወንዝ አካባቢ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች ማዘጋጀት ስለሚፈልግ ዜጐችን ማፈናቀል የመንግስት ሌላው ተግባር ይሆናል። እነዚህን ማህበረሰቦች በጉልበት ከቀያቸው ማፈናቀል አደጋ አለው። አንደኛው እርምጃቸው ሊሆን የሚችለው ጠመንጃ አንግተው መዋጋት ሲሆን ሁለተኛው በአካባቢው የሚካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ በባለቤትነት ባለመያዛቸው ምክንያት ሊያደርሱ የሚችሉት አደጋ መልሶ ልማቱን ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል።

### ቀጣዩ የኢትዮ-ኬንያ ግንኙነት

ግድቡን በሚመለከት አስቀድሞ በኬንያ እና ኢትዮጵያ መካከል ተደርሶ የነበረው መግባባት አሁን አሁን ጥያቄዎችን ማስነሳት ጀምሯል። የኬንያ ከፍተኛ ባለስልጣን (በሚኒስትርነት ማዕረግ) በግልገል ጊቤ እና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ላይ የነበራቸው አቋም በአካባቢ ተሟጋች ቡድኖች ምክንያት እየቀየሩ መጥተዋል። በኬንያ የሚኖሩ የዳሰነች እና ቱርካና ማህበረሰቦች በኃይቁ ዙሪያ በሚደርሰው አደጋ ቀጥተኛ ተጋላጭ ናቸው። በአካባቢው ላይ በውኃው ምክንያት በሚደርስ ማናቸውም ተፅዕኖ ነዋሪዎቹ የቀደመው ህይወታቸው መስመር ሊስት እንደሚችል ባለስልጣናቱ ተገንዝበዋል። ስለዚህ ከዚህ ቀደም አልፎ አልፎ የነበረው የግጦሽ መሬት ፍለጋ ግጭት በተባባሰ መልኩ ወደ ጦርነት ሊቀየር ይችላል የሚለው ሌላው ስጋት ነው። ከጐረቤት አገራት መካከል ኬንያ ለአገራችን በስጋትነት ደረጃ ያልሰፈረችው ስትሆን በቀጣይነትም በዚህ መንገድም ትቀጥላለች ብሎ ማሰብ ከባድ ይሆናል።

### ኢትዮጵያኖቹስ?

ኬንያውያኑ ለአገራቸው እና ለዜጐቻቸው የሚቆረቆሩ ወጣቶች እንዳሏቸው አይካል አንጀሊ አንድ ማሳያ ነች። ግድቡን አስመልክቶ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ "They don't want to see developed African: they want us to remain undeveloped and backward to serve their tourist as a museum" (እነርሱ ያደገች አፍሪካን ከማየት ይልቅ፣ የአገራቸው ቱሪስቶች መጥተው የሚጐበኙት ሙዝየም ሆነን እንድንቀርላቸው ይፈልጋሉ) ከማለት ውጭ ግድቡን በሚመለከት ለደረሰብን ትችት አንዳችም ኢትዮጵያን ወክሎ ወደ መድረኩ የመጣ ተሟጋች ቡድን ሊያሳዩን አልቻሉም። በመድረኩ የታየው የመንግስት ዝምታ ምንን ያመለክታል? በእርግጥ ይደርሳል የተባለው አካባቢያዊ ችግር በማህበረሰቡ ላይ የሚደርስ ከሆነ በቀጣይ ለሚመጣው ፖለቲካ አደጋ ኃላፊነቱን ማን ሊወስድ ነው? ‹‹አይ! ሌሎች ያሉት ችግር በተጨባጭ የሌለ እና መሰረተ ቢስ ነው›› ብሎ መንግስት የሚያምንም ከሆነ አንዲት ኬንያዊት ወጣት አለምን አሳምና እርዳታ እንዳናገኝ እስክታሳምፅብን ድረስ መንግስት ምን እየሰራ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች እንድንጠይቅ ያደርገናል።

የአለም አቀፉ ማህበረሰብ በግድቡ ዙሪያ ያሳየው ድጋፍ መቀዛቀዝ ምንም ችግር አላመጣም ለማለት አንደፍርም። እንደታቀደው ቢሆን ኖሮ ግድቡ በቀጣይ ዓመት ተጠናቆ ስራውን በጀመረ ነበር። አሁን ባለው መረጃ 51% ብቻ የሚሆነው ነው የተጠናቀቀው። የኬንያ አካባቢ ተሟጋች ቡድኖች በዚህ ረገድ የሰሩት ሰፊ ስራ ማሳያ አድርገን ልንወስደው እንችላለን። ይሄ ትልቅ የፖለቲካ ክስረት ነው።

አሁንም ቢሆን የተጀመረውን ግድብ በጉልበት ‹‹እንጨርሰዋለን›› ከማለት ጐን ለጐን ሌሎች የዲፕሎማሲ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጉዳዩን በኃላፊነት ወስዶ ቢያንስ አንዳንድ ተግባራት ሊሰራ ይገባዋል። የመጀመሪያው ተጨባጭ እርምጃ በአገራችን ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን በማሰባሰብ (የተማሩትን) በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ እውቀት በማሰልጠን መጠቀም የሚለው ነው። እነዚህን ወጣት እና ብቁ ዲፕሎማቶች ለሁለት የተለያዩ አላማዎች መጠቀም ይቻላል።

የመጀመሪያው አገራችን በምታካሂዳቸው ማናቸውም የልማት እንቅስቃሴዎች ዜጐች ጉዳዩን በእኔነት ስሜት እንዲያዩትና ተባባሪ እንዲሆኑ የማሳመንና ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን እንዲፈጥሩ ማበረታታት። እነዚህን ወጣቶች የሚደግፍ ሌላ የምሁራን ቡድን በኃሳብ ማመንጨት ተግባር ላይ (Think thank) እንዲሰማሩ በማድረግ ወጣቶቹን በልምድና በእውቀት እንዲያግዟቸው ማበረታታት ሲሆን የእነዚህ ወጣት ዲፕሎማቶች ተልዕኮ መሆን የሚገባው በአለም አቀፍ መድረክ እየተገኙ በሌሎች አገሮች እየደረሰብን ያለውን የዲፕሎማሲ የበላይነት በሀሳብ እንዲሟገቱ ማድረግና በሀሳብ የበላይነት እንድንወስድ ማስቻል ናቸው።

ሁለተኛው መፍትሄ አቅጣጫ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደረጃ በልማት ዙሪያዎች ብቻ የሚሰሩ ቃል አቀባዮች (Spokes man) መቋቋም ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ የቃል አቀባይ ሚና በደንብ ጐልቶ የወጣው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ሲሆን የኤርትራ መንግስት በጊዜው በአለም አቀፍ መድረክ ይዞት የነበረውን የበላይነት እንዲያጣ ምክንያት ከሆኑት መካከል የኢትዮጵያ ቃል አቀባይ ቢሮ ዋነኛው ነበር። ከጦርነቱ ማብቃት በኋላ በሚኒስትር መስሪያ ቤት ደረጃ የተቋቋመ ቃል አቀባይ ቢሮ ከመኖሩ በስተቀር በወሳኝ አገራዊ ፕሮጀክቶች ዙሪያ ዲፕሎማሲያዊ ተግባራትን የሚከውን የቃል አቀባይ ቢሮዎች የሉም። ስለዚህ በተለይ ከጐረቤት አገራት ጋር በሚያነካኩን ማናቸውም ፕሮጀክቶች ዙሪያ ስራው ከግብ እስኪደርስ ድረስ እየተከታተሉ መረጃዎችን የሚያቀርቡ፣ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሚሟገቱ የተለየዩ የቃል አቀባይ ቢሮዎች ያስፈልጉናል።

እነዚህ ቡድኖች ስራቸውን በአግባቡ ይወጡ ዘንድ፤ በማህበረሰቡም ዘንድ ተዓማኒ እንዲሆኑ ከፖለቲካ ተፅዕኖ ገለልተኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ እና ኢትዮጵያ እንደ አገር ተነጣጥለው መታየት አለባቸው የሚል አመለካከት አለኝ። በአገር ጉዳይ የጋራ አቋም ማሳየት ኢህአዴግን እንደመደገፍ ብቻ መታየት የለበትም። በእንዲህ አይነት ወሳኝ ፕሮጀክቶች ላይ ተጠቃሚም ተጐጂም የምንሆነው ሁላችንም ነን። የኬንያ ማህበረሰብ በፖለቲካ አመለካከቱ ያልተከፋፈለ ማህበረሰብ አይደለም። በቅርቡ የምርጫ ታሪካቸው እንኳን ዘርን ማዕከል ባደረገ መልኩ ብዙ ዜጐቻቸውን አጥተዋል። ኬንያ እንደ አገር ስትደክም ማየት የማይሹ ወጣቶች እንዳሏት ግን ከዚህ ተሞክሮ ማየት ችላለች።**ኢትዮጵያኖቹስ?**

# ድህረ-ኢህአዴግ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት

## (የፕሮፌሰር መስፍን ባቡር የት ደርሶ ይሆን?)



አናንያ ሶሪ
anania20006@yahoo.com

ከኢህአዴግ-መንግስት በኋላ ኢትዮጵያ በሚል ስያሜ የምትጠራ የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ አገር ትኖር ይሆን? ወይስ እንደሶቪየት ሕብረት፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ አሊያም ሶማሊያ ትበታተንና መታሰቢያዋን እንኳን ማግኘት እስኪያቅት ድረስ ትጠፋለች?

በታላቅ ወንድሞቼና እህቴ ዕድሜ እንኳ የነበረችው ያቺ ኢትዮጵያ ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ ከመረብ-ማዶ ያሉትን ህዝቦቿንና አካልዋን በይፋ አጥታለች:: ሰፊ የነበረችው ታላቅ ሀገር ጠባለች:: ብዙ የነበርነው ህዝቦቿም ወንድም እና እህቶቻችን ከቁጥር ጉድለውብን ዛሬ አንሰናል:: ዓለም ወደ አንድ-ነት በሚነጉድበት በዚህ ጊዜ እኛ ግን ከዚህም በላይ እንዳንከፋፈልና እንዳንነጣጠል የሚሰጉ እኔን ጨምሮ በርካታ ናቸው:: ነገም እንለያይ ይሆን? ግን ለምን?

በህዳር ወር 1996 ዓ.ም. በሂልተን ሆቴል የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማሕበር አዘጋጅቶት በነበረው 'ርእይ 2020' በተሰኘ የምሁራን ስብሰባ ላይ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ባቀረቡት ፅሑፍ፡- ኢትዮጵያ በያዘችው አቅጣጫ ከቀጠለች የት ልትደርስ እንደምትችል ሲያትቱ እንዲህ ብለው ነበረ፡-

‹‹ከተለያየ የትምህርትና የሥራ መስክ የመጡ ቢሆንም ከዚህ በፊት የተናገሩት ሁሉ በአንድ ነገር ይስማማሉ፡- አሁን በተያዘው መንገድ መቀጠል አንችልም፤ የያዝነው መንገድ ወደ ‹‹ክፉ ዕድል›› ወደ ‹‹መዓት›› ወደ ‹‹ውድቀት›› የሚያመራ መሆኑ ተገልጾአል፤ ለእኔ የአዘቅቱ መንገድ የሚታየኝ እንደሚከተለው ነው፤ በሸምበቆ አጥር የተለያዩና የሚተራመሱ ጎሳዎችን ጭኖ የሚከንፍ ባቡር ይታየኛል፤ ነጂው መትረየሱን ይዞ ፊቱን አዙሮ የተቀመጠው ወደሚነዳበት አቅጣጫ ሳይሆን ወደተሳፋሪዎቹ ነው፤ ተሳፋሪዎቹ የሚያዩት ወደፊት ነው፤ ነጂው የሚያየው ወደኋላ ነው፤ ስለዚህም ነጂው ገደሉን ስለማያይ ይበልጥ የሚያስፈራው የተሳፋሪዎች ትርምስ ነው፤ ተሳፋሪዎቹን የሚያስፈራቸው የሚታያቸው መትረየስና ገደል ነው፤ በባቡሩ ላይ ያሉ ተሳፋሪዎች ሁሉ በባቡሩ ፍጥነት ላይም ሆነ አቅጣጫው ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የላቸውም፤ የባቡሩ ነጂ ተሳፋሪዎቹ የሚያዩትን አያይም፤ እንዲነግሩትም አይፈልግም፤ የነጂውና የተሳፋሪዎቹ አስተሳሰብ ለየቅል ነው፤ አይነጋገሩም፤ ተሳፋሪዎች በዝምታ ነጂውም ባለማወቅ ወደማያየው ገደል ውስጥ ለመግባት ቆርጠዋል፤ ባቡሩን አቁም ብለው ቢጮሁ መልሱ መትረየስ መሆኑን ያውቃሉ፤ በዝምታ አብሮ ገደል መግባት ነው፤ በዚህ አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ተይዘናል፤ ከተረዳንለት ነጂውም አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ውስጥ ነው፤ ነጂውና ተሳፋሪዎች ካልተነጋገሩ ባቡሩም፤ ተሳፋሪዎችም፤ ነጂውም ከገደሉ ማምለጥ አይችሉም::

እንግዲህ መሳሪያ የያዘውም ይፈራል፤ መሳሪያ ያልያዘውም ይፈራል ማለት ነው፤ የሁለቱም ጠላት አለመተማመንና መሳሪያው ነው፤ አለመተማመንን ሳናጠፋ መሳሪያውን ማጥፋት አንችልም፤ ሳንነጋገር አለመተማመንን ማጥፋት አንችልም፤ ልባችን ከቂምና ከበቀል ካልፀዳ ተነጋግረን መግባባት አንችልም፤ ባቡሩ እውር ድንበሩን እየሄደ ገደል የሚገባው ለዚህ ነው::››

ፕሮፌሰር መስፍን ይህን ፅሁፍ ካቀረቡ ደግሞ እነሆ 8 ዓመታት ሆነው:: በሚያዚያ 2004 ዓ.ም. ከ‹‹አዲስ ጉዳይ›› መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ-መጠይቅ ደግሞ ስለነገይቱ ኢትዮጵያ መፃዒ-ዕድል ተጠይቀው፡- ‹‹…ነገ ኢትዮጵያ ትኖራለች ብለህ ነው?…›› ዓይነት አስደንጋጭ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህን አሳሳቢ ምላሽ በዘበት ቸል እንዳንለው የሚያደርገን ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ሶስት የአገዛዝ ስርዓቶችን በተመራማሪነት፣ በመምህርነት፣ በሰብዓዊ-መብት ተሟጋችነት፣ በፖለቲከኛነት፣ በመጽሐፍት ደራሲነት፣ በአባትነት፣ በአገራዊ ጉዳዮች ሂስ-አቅራቢነት በንቃት ሲሳተፉ ከኖሩ አንጋፋ ኢትዮጵያዊ የተሰነዘረ በመሆኑ ነው:: በዚያ ላይ ፕሮፍ በተለያዩ የምርምርና የህይወት ጉዳዮች ከአገሪቷ ጫፍ-እስከ-ጫፍ ተንቀሳቅሰዋል:: የኢትዮጵያውያንንም ስነ-ልቡና እና ነፍስ ከብዙዎች መሰሎቻቸው ይልቅ በጥልቅ-ግንዛቤ የተረዱ የሞራል-አባት እና የአገር-ዋርካ የሆኑ ሰው ናቸው::

በመሆኑም የእኚህን አሰላሳይ-ምሁር ተስፋ እንዲህ ያሰለሉባቸው፤ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ህልውና ተግዳሮቶች ላይ ሌሎቻችንም ብንወያይ መልካም በመሆኑ እኔም የበኩሌን ልገልፅ ወደድኩ::

ፕሮፌሰሩን ስጋት ውስጥ የከተታቸው 'በሸምበቆ አጥር የተለያዩና የሚተራመሱ ጎሳዎችን ጭኖ የሚከንፈው ባቡር' ወደገደሉ አፋፍ ደርሷል መሰል መንገራገጮቹ በዝተዋል:: በሸምበቆ አጥር የተለያዩት ጎሳዎችም ምሬታቸው ገደቡን ጥሷል:: ይህ ገደቡን የጣሰው ምሬታቸውም ባልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይነጉድ ያሰጋል:: ለዚህ ደግሞ እንደ ሰይጣን መልእክተኛ በቅርብ ሆነው 'በል! በል!' የሚሉ እፉኝቶች በሁሉም ቡድኖች መሃል ተቀምጠው መርዘኛ-ጥላቻቸውን ሲነዙ ይስተዋላል:: 'ከእኛ ወዲያ ኢትዮጵያዊ-ላሳር!' የሚሉ ጥራዝ-ነጠቅ አርበኞችም የፊውዳል ዘመን ቀረርቶዋቸውን ተያይዘውታል::

ይህን ሁሉ ትርምስ ወደቁም-ነገር ወስደን ከስሜት ውጪ በሆነ መንፈስ በአመክንዮአዊና በርዕዮተ-ዓለማዊ መስመርነት እንየው ካልን ደግሞ ሁለት ዋነኛ ቅራኔዎችን እናገኛለን:: 'ኢትዮጵያ የአምላክ ቃልኪዳን ያላት አገር ናት!' በሚለው መለኮታዊ የእምነት መሠረት ላይ ከቆሙት ጀምሮ እስከ 'ከኢትዮጵያ ቅኝ-ግዛት/ጭቆና ስንወጣ ነፃ-አገር እንሆናለን!' እንቅስቃሴዎች ድረስ እጅግ የተራራቁ እና ፅንፍ-ለፅንፍ የቆሙ (Extremely polarized) አሰላለፎች በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልክአ-ምድር ላይ ጉልተው ይስተዋላሉ::

እነዚህ አሰላለፎች የየራሳቸው ተከታዮች ቢኖሯቸውም፤ በትክክል የአብላጫውን ህዝብ ስሜት ይወክሉ አይወክሉ ግን በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም:: ይህ የሚታወቀው ነፃና ዴሞክራሲያዊ ህዝበ-ውሳኔ ተደርጐ ህዝቡ በነፃ-ፈቃዱ ፍላጐቱን ሲገልጥ ብቻ ነው:: እስከዚያው ድረስ ግን፡- በፊት በፊት ለአካባቢያዊ መሳፍንቶች ሎሌነት ማደር ግዴታው የሆነው ሰፊው ህዝብ አሁን አሁን ደግሞ ለአካባቢያዊ-ልሂቃን ሎሌነት እንዲያድር ይገደዳል:: ሁለቱም ግን አስገዳጆች ናቸው:: ከዚህ ውጭ ያለውን መሃከለኛ-መንገድ ግን በግራም ሆነ በቀኝ ያሉት ሃይሎች ክፉኛ ይቃወሙታል፤ ከየአቅጣጫቸው እርግማንና ውርጅብኛቸውንም ያዘንቡበታል:: የማይነካ እርኩስ ነገር አድርገው ይስሉትና ያስፀይፉታል::

በመሆኑም፡- ጫፍ ላይ ያሉ ጽንፈኛ የፖለቲካ አሰላለፎች (ጩኸታቸው ከፍ ያለ መሆኑም ታክሎበት) በኢትዮጵያ ዋናውን የፖለቲካ መድረክ ተቆጣጥረውታል:: ለዘብተኞች (Moderates) ቦታ አጥተዋል:: ከደቂቀ-እስጢፋኖስ ዘመን የጀመረ ልዩነትን ጨርሶ የማጥፋት አውዳሚ አካሄድ በ'ያ ትውልድ' የግራ-ዘመም ፖለቲከኞች ወደላቀ ደረጃ ተሸጋግሮ 'መሃል-ሰፋሪ በሁለት ጥይት ይመታል!' እስከሚል ፖለቲካዊ ቀኖናነት አድጓል:: በመሆኑም፡- ኢትዮጵያ ሀገራችን እና ኢትዮጵያዊ ማንነታችን በአገር ወዳድነት Vs ከሃዲነት፣ በወግ-አጥባቂነት Vs ተራማጅነት፣ በትውፊት ጠባቂነት Vs በአእማድ አፍራሽነት መሃል በከረረ ልዩነት (Sharp Distinction) ተወጥሮ ሊበጠስ እየተገዘገዘ ነው::

ከዚህ በመለስ ያለ አማካይ መንገድ፤ እንኳን ለምርጫ ሊቀርብ ቀርቶ ሃሳቡን የሚያብራራበት ዕድል እንኳን ተነፍጐታል:: ወይ ከእኛ ጋር ነህ፤ አሊያም በእኛ ላይ ተነስተሃል! (You are either with us or against us) በሚል 'የአንዱን ምረጥ!' አንጉል ፈሊጥ ተገድበናል:: ወይ ይሄ/አሊያም ያኛው! የሚል ከሁለት የተገደቡ ምርጫዎች አንዱን ብቻ የግድ የመምረጥ የሃሳብ-ዝንፈት ወይም ስህተት (Either/or fallacy) ላይ እንድንወድቅ ይዳርገናል:: 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ ወይም ከዚያ በላይ ምርጫዎች

ወደ ገፅ 7 ዞሯል »

# የፖለቲካችን የቁልቁለት ጉዞ መቆሚያው የት ይሆን?

ዳንኤል ተፈራ

ከወራት በፊት ከመስማት በማይሞላው ጆሮአችን አንድ አስደንጋጭ ዜና ሰምተን ነበር:: ዜናውን ለየት የሚያደርገው ከዚህ በፊት ከሰማናቸው የስደት ላይ አደጋዎች የተለየ በመሆኑ ነው:: መቼስ ስደት መታወቂያችን ሆኖ የለ? ከዚህ በፊት በሱዳን፣ በኬንያ፣ በሶማሊያና ጅቡቲ እየሾለኩ ከሀገራቸው የሚሸሹት ኢትዮጵያውያን ምክንያታቸው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወይም ፖለቲካ ከተባለው ወላፈን ለማምለጥ ነው::

እናም በፊት እንሰማው የነበረው የስደት አደጋ በአስፈሪው የሰሃራ በርሃ ደርቆ መቅረት ወይም በባህር እየተጣሉ የአሳነባሪ እራት መሆን ነበር:: በየጊዜው ‹‹ቁጥራቸው እንደዚህ የሚገመት ኢትዮጵያውያን ወደ የመን ስታመራ የነበረች ጀልባ ሰምጣ በጠቅላላ አለቁ›› ሲባል ሰምተናል:: ስለለመድነው ምንም አይመስለንም:: የተለመደችውን ከንፈራችንን መጥጠን ዝም እንላለን:: እነዚህ ዜናዎች ከአፈና አምልጠው ጆሮአችን የሚደርሱ ናቸው:: እምጥ ይግቡ ስምጥ ሳይታወቅ የሞታቸው ዜና ተዳፍኖ የሚቀሩት የትየለሌ እንደሆኑ ለመገመት አይከብድም::

ከወራት በፊት የሰማነው ዜናም አፈትልኮ ጆሮአችን ደረሰ:: ቁሳቁስ በሚታጨቅበት ባዶ ኮንቴነር ውስጥ ታጭቀው ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ለመውጣት በቆረጡ ወጣቶች የተሞላው ኮንቴነር ከበረሃው ወላፈን ጋር ተደምሮ የበርካቶችን ህይወት በላ:: መተኪያ የሌላት ክቡር ህይወት ላይ ፈርዶ ከኢትዮጵያ ለመውጣት መሞከር ያለብንን ግዙፍ ችግር ክብደት ፍንትው አድርጐ ያሳያል::

ጥያቄው መሆን ያለበት ኢትዮጵያውያን በቀጭን ክር ተንጠልጥለው ከሀገር የሚወጡት ለምንድን ነው? የሚለው ነው:: ለምን እንደ ሸንኩርት በኮንቴነር ተጭነው ለመውጣት ሞከሩ? ከዚህ የተሻለስ እዚያ ምን አለ? መንግስትስ የስደቱን መንስኤ ለምን አላጠናም የሚሉ ሸንጥና ወርድ ያላቸውን ጥያቄዎችን መደርደር ይቻላል::

ኢትዮጵያውያን ነፍሳቸውን ሸጠው ከሀገር የሚወጡት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ነው:: የተሻለ ነፃነት ስላማራቸው ነው:: ገዢው ፓርቲ ‹‹አዲሲቱ ኢትዮጵያ›› እያለ እንደሚያወራው አይነት አዲስ ነገር ያለ አይመስለም:: የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካው መበላሸትም ተማረው ሀገር ላይ የሌለውን ነፃነት በባዕዳን ሀገር ለማግኘት ሸተው በሞያሌ በኩል የሚወጡም ብዙ ናቸው::

ከላይ ያነሳሁትን የስደት ዋና ምክንያት ስንፈትሽ የምናገኘው መቆሚያው የት እንደሆነ የማይታወቀውን የፖለቲካችንን የቁልቁለት ጉዞ ነው:: የተስተካከለና ህዝባዊ መሰረት የሌለው እንዲሁም በግለሰቦች የሚመራ ፖለቲካ ባለበት ሀገር የግለሰቦችን ስልጣን ለመጠበቅ ሲባል ብቻ የህዝቦች ነፃነት እንደ ሸማ ተጠቅልሎ ይወሰዳል:: ነፃነቱ የተወሰደበት ህዝብ አሳቢነቱንና አምራችነቱን ያጣል:: ስለዚህ በተበላሸ ወይም በአፋኝ ፖለቲካ ውስጥ የሚኖር ህዝብ በኢኮኖሚውም የዳበረ አይሆንም:: ኢኮኖሚው ሲጐሳቀል ደግሞ ማህበራዊ ህይወትም እየላላና እየተወላከፈ ይሄዳል ማለት ነው:: ሀገርን ለቆ እግር በመራና ሞት ባለበትም ቢሆን ለመውጣት መሞከር ከዚህ በኋላ ይመጣል::

‹‹የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ›› እንደሚባለው ከላይ ለተነሱት ችግሮች ማሰሪያው ወይም ቁልፍ የተስተካከለ ፖለቲካ በመመስረት ላይ የወደቀ ይሆናል:: ለዛሬውም በስሱም ቢሆን የፖለቲካችን የቁልቁለት ጉዞ መንስኤና መቆሚያው የት እንደሚሆን እናያለን::

የተበላሸ የፖለቲካ መስመር የት እንደሚያደርስ በቀደሙት መንግስቶቻችን ያየን ቢሆንም አስከፊነቱን ለመገንዘብ ግን ሱማሊያን መጥቀስ ይቻላል:: ቁልቁል እየወረደ ያለን ፖለቲካ ተመልክቶ መቆሚያውን እያሰቡ መቆዘም ወይም መቃዠት ተገቢ ነው::

ጐረቤታችን የቀድሞዋ ‹‹ታላቋ ሶማሊያ›› የአምባገነኑ ዚያድባሬ አስተሳሰብ ውጤት ናት:: ከአቅም በላይ መንጠራራትም ከአቅም በታች መሸምቀቅም አደገኛ ነው:: እናም አምባገነንነታቸውን በጀብደኝነት እያሹ እንደ ዚያድባሬ መድረሻው በማይታወቅ ቅዠት ውስጥ መውደቅና በቅዠት ውስጥ ሀገርን መምራት ሀገርን ይዞ ከመውደቅ ባለፈ የሚፈይደው ቁም ነገር የለም:: ዛሬ መንግስት አልባ (Failed state) በመባል የምናውቃት ጐረቤታችን ሶማሊያ መቆሚያ በሌለው የፖለቲካ ቁልቁለት ወርዳ፣ ወርዳ የተሸነቀረች ወይም ቅርቃር ውስጥ የገባች ሀገር ሆናለች:: ሱማሊያን እጇን ይዞ ከገባችበት ቅርቃር ለማውጣት ሙከራ ተደርጎም አልተሳካም::

የዚህ ፅሁፍ አላማም ፖለቲካችን ቁልቁል ወርዶ፣ ወርዶ መውጣት ከማንችልበት ቅርቃር ውስጥ ከመግባታችን በፊት የፖለቲካው መታመም ምክንያቶችን ለመጠቋቆም ነው:: መቼም ‹‹ኢህአዴግ አምባገነን መንግስት ነው፣ ዴሞክራሲያዊ አይደለም›› ብሎ እንደመፃፍ አሰልቺ ነገር የለም:: በቃ እውነት ነዋ! አንዳንዴ ደግሞ ስለገዢው ፓርቲ ስርየሰደድ ችግሮች እያነሳን ስንፅፍ የተለየ ጥላቻ ያለን የሚመስላቸው ግለሰቦችም አይጠፉም:: ምን እናድርግ እሱም እውነት ነው:: ስለአቶ መለስም ደጋግመን ስናነሳም ‹‹አልበዛም እንዴ!›› የሚሉ አሉ:: እንዴ! አቶ መለስ እኮ መንግስት ሆነዋል:: በዛ ላይ ጠቅላይ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ ግን ቁልቁለት እየወረደ ያለ ፖለቲካ ውጤት ናቸው::

እንዴት? የሚል አብይ ጥያቄ እናንሳና እንቀጥላ! ለባለፉት 21 ዓመታት በመግዛት ላይ የሚገኘው ኢህአዴግ (አሁንም ኢህአዴግ እያሉ መፃፍ እንዴት ያሰለቻል መሰላችሁ:: ኢህአዴግ የተስተካከለ ዴሞክራሲያዊ መንግስት በሆነና መፃፍ ባቆምኩ እያልሁ እመኛለሁ:: ሊስተካከል አልቻለም እንጂ) በኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ቁጭ ያደረገው የፖለቲካ መስመሩ አደናጋሪም፣ አነጋጋሪም ነው:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ መንግስትና አውራ ፓርቲ ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት ጋር እየተጣረሱ፤ እንዲሁም እነ አቶ መለስ አንድ እግራቸውን ምዕራባውያን ላይ ሌላ እግራቸውን ደግሞ ምስራቅ ላይ አቁመው ይችን ሀገር ከግራና ከቀኝ እየጎተቱ የእኛ የሆነውን ሳናገኝ ዥዋዥዌ እየሰራን ይሄው አለን:: ይሄን ግራ የገባው ርዕዮትና በግራና በቀኝ መካከል ቆሞ መጐተት አንድ አላችሁልኝ?

ደግ:: ሁለት እንበላ! ሁለተኛው በአንደኛው ላይ የተቀመጠውን ተከትሎ የሚመጣው በመሪ ነው የምንመራው ወይስ በርዕዮት (Ideology) ነው? የሚል ነው:: እንደምናየው በመሪ የምንመራ መሰለኝ:: በአቶ መለስ ብቻ ማለት ነው:: ይሄንን ማለትም (የርዕሰ መንግስትነት ሀልዮት) የፖለቲካችን የቁልቁለት ጉዞ ማሳያ ማረግ ይቻላል:: አሁን ሀገራችን የምትመራው በኢህአዴግ ሳይሆን በአቶ መለስ ነው የሚሉ ልሂቃን አሉ:: ከውስጥ አዋቂዎች እንደሰማነው የሕግ አውጭነቱን ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውና ከሶስቱ የፌደራሊዝም ክንፎች አንዱ የሆነው ፓርላማ ብዙ ጊዜ ኮረም አልሞላ እያለ ስብሰባ ይስተጓጐላል አሉ:: አቶ መለስ ፓርላማ ሲቀርቡ ግን ግጥም ብሎ ይሞላል:: ይሄ ለፓርላማ አባላቱ እንኳ ከሀገራዊ ጉዳዮች በላይ የአቶ መለስ ጉዳይ ይገዝፍባቸዋል ማለት ነው:: አቶ መለስ በተለይ ከ1997 ዓ.ም በኋላ ምትክ የሌላቸው፣ ብቸኛና ሁሉን አዋቂ ተደርገው ተስለዋል:: ይሄን ለማጠናከር መንግስታቸውን በታማኝነት በሚያገለግሉ ባለስልጣናት ተከቧል:: ይሄንን የመሰለ ገንኖ በብቸኝነት መውጣት ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ‹‹የመለስ አምልኮ›› ይለዋል:: መለስ እንዴት አምላኪዎቻቸውን እንደፈጠሩና ወደ መመለክ ደረጃ እንደወጡ ይተርክልናል:: ስለዚህ በኢህአዴግ የፖለቲካ መስመር ውስጥ ሀገሪቷ የመሪ ሀገር እንድትሆን ተፈርዶባታል:: (በነገራችን ላይ እንደ ክፉ ዕጣ ኢትዮጵያ ከመሪ ሀገርነት ወጥታ አታውቅም:: ኢህአዴግ ደርግን አስወግዶ ስልጣኑን በሙሉ ሲቆጣጠር ተስፋ ከተደረጉት ጉዳዮች አንዱ ‹‹ሀገሪቱን በግለሰብ ከመመራት ያወጣታል›› የሚል ነበር:: በነበር ቀረ እንጂ! ታዲያ የፖለቲካችንን የቁልቁለት ጉዞ ሁለት አልን አይደል!

እንሰልስ:: ሦስተኛው የሀሳብ የበላይነት መጥፋት ነው:: አሁን አሁን በፖለቲካችን ውስጥ አስፈሪነቱ እየገዘፈ የመጣው ጉዳይ በክርክር አምኖ በሀሳብ የበላይነት ማሸነፍ የማይታሰብ መሆኑ ነው:: በኢትዮጵያ የምታሸንፈው ግሩም ሀሳብ አፍላቂ ስለሆንክ አይደለም:: አሸናፊነት በፕሮፓጋንዳ የበላይነትና በጉልበት ብቻ ነው:: ራሱን ኢህአዴግንና አመራሩን እንቅልፍ የነሱት ‹‹ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና›› የሚባሉት መገለጫዎች የተፈጠሩት የሀሳብ የበላይነት መሸነፍና የጉልበትን ማሸነፍ ተከትሎ ነው:: በቃ ጉልበት ካለህ ሁሉንም ትወስዳለህ:: ሲዘርፍ እያየህ አትናገርም:: ጉልበት አለችዋ! ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት እንዲጠፉ ደግሞ የሀሳብ የበላይነት ማሸነፍ አለበት::

የኢህአዴግ መንግስት በሀሳብ የበላይነትና በክርክር የሚያምን መንግስት አይደለም የሚሉ ወቀሳዎች ሲሰነዘሩበት እንሰማለን:: ለዚህ ወቀሳ ምሳሌ ማድረግ የሚቻለው ነፃ-ሚዲያዎችን ነው:: ነፃ-ሚዲያዎችን አይወዳቸውም:: ባለመውደድ ብቻ ቢያበቃም እሰየው ነበር ግን የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅና አሁን ደግሞ በማተሚያ ቤት በኩል ሳንሱር ለማድረግ መሞከር የሀሳብ የበላይነትን ያለመቀበል ውጤቶች ናቸው:: ሀሳብን በነፃነት መግለፅ አለመቻልና የሀሳብ የበላይነትን ያለማክበር የፖለቲካችን የቁልቁለት ጉዞ ማሳያ ነው::

ለመፃፍ የመረጥኩት ርዕስ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ያነሳኋቸው ሃሳቦች ከበርሜል ውስጥ በማንኪያ የመቆንጠር ያህል ነው:: የቆነጠርኩትን ላጠቃልለው:: ከላይ የቆነጠርኳቸው የፖለቲካችን ቁልቁለት ማሳያዎች ማሳረጊያ የሚሆነው አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መመስረት አለመቻል በሚለው ይሆናል::

የነ አቶ መለስ መንግስት በመቻቻል፣ በመተሳሰብና በአንድነት ላይ የቆመ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር አልቻለም:: የተበታተነ፣ በብሔሩ ውስጥ የሚወሸቅና ርስ በርስ በመጠራጠር የሚተያይ ማህበረሰብ በመፍጠር ግን ተሳክቶላቸዋል:: ስለዚህ ፖለቲካቸው በመንግስት ወዳድነት እንጅ በሀገር ወዳድነት ላይ ያልተመሰረተ የሀገር ፍቅርን በመንግስት ፍቅር በመጠረዝ የተሞሉ ያጠቃው ነው:: ስለዚህ ምንም አይነት ርምጃ የሚወስደው ለስልጣን ሲባል ይሆናል ማለት ነው:: እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች ተደምረው የፖለቲካው ቁልቁል ጉዞ መቆሚያው የት ይሆን? ያሰኙናል::

የማቆሚያው ታኮ በመንግስት እጅ ነው:: እሱም ማዳመጥና መተግበር ናቸው:: ያኔ በኮንቴነር ታሽገው በሰቆቃ ከሀገር ለመውጣት የሚሞክሩ ኢትዮጵያውያን ስቃይም ያበቃል:: የፖለቲካችን መጨረሻም አያስጨንቀንም::

በጌታቸው ታምራት (LLB)

## የፍትህ ዓምድ



በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

# የሠራተኛ ማህበራት ተግባር ምን ድረስ ነው? ፩

የበሰሉ የሰራተኛ ማህበራት የሉም ማህበራቱ ካሉም በዳቦ አደር አመራሮች የተሞሉ ስልሆነ በቀላሉ በአሰሪዎች ሎቢ ይደረጋሉ፣ አንዳንድ አሰሪዎች በአደባባይ በህግ የተቀመጠውን መብት አያከብሩም፣ በመንግስት በኩል ጉዳዩን ተከታትሎ ህግን ከማስከበርና ሰራተኞች መብታቸው ሳይነካ ሰርተው የሚገቡበትን መንገድ ለማመቻቸት ያለው ተነሳሽነት ደካማ ነው ወይም ሰምቶ እንዳልሰማ ይታለፋል፣ የግል ድርጅት ባለቤቶች ሰራተኛው መብቱን ለማስከበር በማህበራት ለመደራጀት ሲሞክር ‹‹ድርጅቱን ልታፈርስ ነው›› በሚል አንዳንድ ሰራተኞች ላይ የስራ ጫና ያበዛሉ፣ ዕድገት እንዲያልፋቸው ያደርጋሉ፣ በተለያዩ ጫናዎች ስራውን ያስለቅቃቸዋል ሌሎች ሠራተኞችም ይህን አይተው መቀጣጫ ያደርጓቸዋል፡፡ ስለዚህ በቀጣይ ተመሳሳይ ስራዎችን አይሰሩም የሚል አስተሳሰብ ተንሰራፍቷል... እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮች በአሁኑ ሰዓት በአሰሪ እና በሰራተኞች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሻክር የሚያደርጉ ችግሮች ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነት መሰል ችግሮች በምዕራቡ ዓለም በተለይም በአሜሪካን ትላንት የነበሩ ችግሮች ሲሆኑ አሁን ግን በፍትሐብሔር ብቻ ሳይሆን በወንጀልም የሚያስቀጡ ጥፋቶች ናቸው፡፡ እንግዲህ በፈረንጆቹ ሀገር ትላንት የነበሩን ችግሮች እኛ አሁን እየተቸገርናቸው ከሆነ እኛ በእነሱ ቀመር ዛሬ ላይ ሆነን ትላንትን እየኖርን እንጂ ዛሬን በህግ በተቀመጠ አካሄድ ለመኖር አልቻልንም ወይንም ነገን መጠበቅ የግድ ይሆንብናል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች በተናጠልም ሆነ በቡድን በአንድ ወይም በሌላ ሰራተኛ ላይ የሚከሰቱ ሲሆኑ ሰራተኛው ችግሮቹን ለመቀነስ ከተቻለ ለማጥፋት በተናጠል ከሚያደርገው ክርክርና ትግል ይበልጥ በማህበራት በመደራጀት የሚያደርገው ተሳትፎ ለሰራተኛው መብቱ መከበር ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ከመሆኑ ሌላ በህገወጥ መንገድ ለመክበር የሚጥሩ ባለሀብቶችን በመግታት ለሀገራችን ዕድገት የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ ባለፈው ሳምንት የሰራተኛ ወይንም የአሰሪ ማህበራትን ለማቋቋም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 377/1996 ለሁለቱም አካላት የሰጠውን የመደራጀት መብት በአዋጅ አንቀፆች እያስደገፍን አይተን ነበር፡፡ ዛሬም ከዚሁ ከሰራተኞች ማህበራት ጋር በተያያዘ የሰራተኛ ማህበራት ምን ምን ዓይነት ተግባራትን መከወን እንደሚችሉ አዋጅ የሰጣቸውን መብትና የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ተዛማጅ ድንጋጌዎችን በማንሳት እናያለን፡፡

በማህበራት ከመደራጀት ጋር በተያያዘ የሀገሪቱ የበላይ ህግ /ህገ-መንግስቱ/ ያስቀመጠውን ድንጋጌ በቅድሚያ እንይ፡፡ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እንዲህ ይላል ‹‹የፋብሪካና የአገልግሎት ሰራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሰራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሰራተኞች፣ ከተወሰነ ኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የስራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግስት ሰራተኞች የስራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት የሰራተኛ ማህበራትና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡›› የሰራተኛው መብት ግልፅ በሆነ ቋንቋ በህገ-መንግስቱ የተቀመጠ ቢሆንም መብቱን በቅጡ ለመጠቀም ከሰራተኛው በኩል ያለው ተነሳሽነት እና ለመደራጀት ልበ ሙሉነት አለመኖር የመደራጀት መብት በህግ ያልተቀመጠ እስኪመስል ድረስ የነቁ የሰራተኛ ማህበራትን ማየት አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ህገ-መንግስቱ በመቀጠል በአንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ላይ ከተገለፀው አንቀጽ ሰፋ ያለ መብት ለሰራተኛው ይሰጣል ‹‹በንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት የሰራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው››

እ.ኤ.አ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በታላቋ ብሪታኒያ እንደተጀመረ የሚነገርለት በማህበራት በመደራጀት መብትን በጋራ መጠየቅ ወይም የህብረት ድርድር /Collective bargaining/ ሰራተኛው ከአሰሪው ጋር በክፍያ፣ በስራ ሰዓት፣ የስራ መብዛትን ወይም ጫናን በተመለከተ፣ እንዲሁም በህግ በተፈቀደ ሰብዓዊ እና ሌሎች መብቶች ዙሪያ የመደራደር መብት አለው፡፡ ይህ መብት የሰራተኛ ማህበራትን ከሚያስፈልጉበት አበይት ጥቅሞች አንዱ እና ዋናው ሲሆን ለአሰሪው ሲባል በመርህ ደረጃም ሆነ በተግባር ሊሻር የማይችል ጉዳይ ነው፡፡ በእኛም አገር የህብረት ድርድር በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 42 የተፈቀደ ነው፡፡ ሰራተኛው ከህብረት ድርድር ሌላ በስራው አካባቢ የተመቸ የስራ ሁኔታ ከሌለ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ስራን የማቆም መብት በህገ-መንግስቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይሁንና የስራ ማቆም ጋር ሳንደርስ ከአሰሪዎች ጋር ያለው የህብረት ስምምነት ህጉን መሰረት አድርጎ ቢጓዝ በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን ያለውን የጉልበት ብዝበዛ፣ ህገ-ወጥ መክበርና የሰብዓዊ መብት ጥሰት መቀነስ ይቻል ነበር፡፡ ሆኖም የሰራተኛ ማህበራት አለመጠናከር፣ የሰራተኞች ለመብታቸው ልበ ሙሉ አለመሆን፣ ተወክለውም ይሁን ሳይወከሉ የሰራተኛ ማህበራት አመራር የሆኑ ግለሰቦች ራስ ወዳድነት በተያያዥም የኢሠሪዎች ፊውዳላዊ ስግብግብነት የማህበራቱ ሚና ወደፊት እንዳይራመድና ሰራተኞች፣ አሰሪዎችና ሀገር ከህብረት ድርድሩ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ ሳንካ ሆኗል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ህጐችም የህብረት ድርድርን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ህገ-ወጥ አካሄድ ሳይሆን በመብት ደረጃ በህገ-መንግስቱም ሆነ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በትልቁ የተፃፈ ሃቅ ነው፡፡ አዋጅ 377/1996 በአንቀፅ 115 ንዑስ አንቀፅ 1 ይህን ጉዳይ እንዲህ ይገልፀዋል፡፡ ‹‹ማናቸውም ማህበር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፤ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የስራ ሁኔታዎችና ተግባሮች መፈፀም፤ እንዲሁም የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም መጠበቅ በተለይም በህብረት ድርድር ወይም በስራ ክርክር ጊዜ አባሎቻቸው ሲጠይቋቸው ወይም ሲወክሏአቸው ለድርድር ወይም ለክርክር አግባብ ባለው አካል ዘንድ ወክሎ መቅረብ...›› ታዲያ ይህ መብት በግልፅ ተቀምጦ እያሉ ለመጠቀም ሰራተኛው ለምን ይፈራል? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ በቅድሚያ ሰራተኛው ይህን መብት በቅጡ እንዳይጠቀም የሚያደርጉት በአሰሪዎች የሚጫንባቸው ውስብስብ ቢሮክራሲ እና መብቱን ለመጠየቅ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በስራው ቦታው የሚዐደርስበት እንግልት እንዲሁም የስራ ማጣት አደጋ ሲሆን መብቱን ለማስከበር ፍርድ ቤት እስኪወስንለት የሚያጋጥመው የኑሮ ውጣ ውረድ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ የአብዛኛው ሰራተኛ ገቢ ከዕለት ጉርስ ስለማያልፍና የኑሮ ውድነትም እየጨመረ ስለሚሄድ ሰራተኛው የማስቀመጥ ባህል አላዳበረም፡፡ የዋጋ ግሽበቱም ይህን እንዲያደርግ አያስችሉትም፡፡ ስለዚህ ሳይበላ ከማደር በህግ የተቀመጠ መብቱ እየተጣሰም ቢሆን በልቶ ለማደር ሲል በአሰሪዎቹ ጫና እየተደረገበት ጫናውን ተሸክሞ ይሰራል፡፡ ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ የህግ ጥሰት በሀገር ላይ ያለው አደጋ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ እንዲሁም ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ በአዋጅ ኃላፊነት የተሰጠው የመንግስት አካል ስላለ ክትትል በማድረግ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል፡፡ በርግጥ የተደራጀ ሰራተኛ የሚጠይቀው ነገር እየበዛ ሲመጣ በማናቸውም መልኩ ላለ አምባገነናዊ አስተዳደር አስቸጋሪ ነው ታዲያ የብዙሃኑ ዜጋ ጉዳይ ከሆነ ምን ሊደረግ ይችላል? ምንም፡፡

ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ የሰራተኛውን መብት በማፈን እንዳይደራጅ የሚያደርጉ አሰሪዎች ከፍትሀብሔር ሌላ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑበት መንገድ በህግ ሊቀመጥ ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ በህገ-መንግስቱ በመርህ ደረጃ የተቀመጠ ሃሳብ በመሆኑ በማናቸውም መልኩ ሊከበር ይገባዋል፡፡ መብታቸው የገባቸው ከዳቦ ሌላ አሻግረው ማየት የሚችሉ የማህበር አመራሮችን ሰራተኛው ማፍራት ከቻለ ሰራተኛውን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ የሚጠቀሙበትንና አነስተኛ ክፍያ እየከፈሉ ጉልበትና ጊዜውን የሚመዘብሩትን ህገ-ወጥ አሰሪዎች መቆጣጠር ይቻላል፡፡ የህብረት ድርድር እያደረገ በመጣ ቁጥር አሰሪዎች ለማህበራት እውቅና እየሰጡ ስለሚመጡ ህጋዊ ማዕቀፍ በደንብ እየገባቸው ይመጣል፡፡ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የሚገኘው የሀብት ማጋበስ ስለሚቀንስ በዜጐች መካከል ያለው የሀብት ልዩነት እየጠበበ ይመጣል፡፡ ብዙሃን የሞቱለት ዓላማም ፍሬ ማፍራት ይጀምራል፡፡ ካልሆነ ግን ስም ብቻ ምን ዋጋ አለው? ቸር እንሰንብት፡፡

# ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትና ፡ሰሞነኛው መንገጫገጭ፡

ዓለማየሁ ሰይፉ

"የቻይና መሪዎች በህግ የበላይነት ሳይሆን በህግ መምራት ይፈልጋሉ" ይህ በአንድ ወቅት የቻይናው የህግ ፕሮፌሰር ሊ ሹጉዋንግ በመንግስታቸው ላይ የሰነዘሩት ትችት ነበር፡፡ በሁለቱ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ በህግ የበላይነት መምራት ህጉ ቀዳሚ በመሆኑ ስልጣናቸውን አላግባብ በሚጠቀሙት ላይ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ በህግ መምራት ግን ህጉ ለመንግስት እንደ መሳሪያ ከማገልገል ያለፈ ትርጉም የለውም፡፡ የህግ የበላይነት ባለበት ሃገር ሺህ ህግ፤ ሺ መመሪያ መደንገግ አያስፈልግም፡፡ ስልት እየቀያየሩ የዜጎችን ሰብአዊ መብት ማፈን ብዙ አያራምድም በምክር ቤት ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጣው ህግና መመሪያ አልበቃ ብሎ የንግድ ድርጅቶችን አሰራር እስከ መጠቀም ድረስ መፍራት አያስፈልግም፡፡

በሰብአዊ መብት መዝገበ ቃላት እጅግ ትልቅ መስዋዕትነት ከተከፈለባቸው ጥያቄዎች መካከል አንደኛውና ዋነኛው ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነት ነው፡፡ በሃገራችን ይህ መብት ህገ መንግስታዊ እውቅና ካገኘም በኃላ አሁንም ዋጋ እያስከፈለ ያለ ጥያቄ ነው፡፡ ይህ መብት ልክ ትምህርት የማግኘትና የመማር መብት ሌሎች መብቶችን አውቆ ለመጠቀም እንደሚያገለግለው ሁሉ ከራሱ ከመብቱ ወይም ሃሳብን በነፃነት ከመግለፅ ባለፈ ሌሎች መብቶችንም ለማረጋገጥ እንዲሁም ለመጠየቅ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ መብት በስተጀርባ ተዘርዝረው የማያልቁ አያሌ የሰው ልጅ ነፃና ክቡር ፍጡር መሆኑን የሚገልፁ የመንግስትና መንግስታዊ አስተዳደር ተጠያቂነትን የሚያጠይቁ ወዘተ አሴቶችን የያዘ የመብቶች ሁሉ የማዕዘን ድንጋይ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል መብት ነው፡፡

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 29 ስር በግልፅ እንደተደነገገው ሀሳብን ለመግለፅ የሃሳቡ ባለቤት ምርጫ እንጂ ምንም አይነት የተቀመጠ የሃሳብ መግለጫ ዘዴ የለም፡፡ በንግግር በፅሁፍ በፕሬስ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ምርጫው የመብቱ ባለቤት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 29/3/ሀ/ "ቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው፡፡" ብሎ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ እጅግ ጠቃሚው ቃል በማንኛውም መልኩ የሚለው ሲሆን የሰሞኑን መንገጫገጭ የፈጠረው የማተሚያ ቤቶች ውል ይህን የሃገሪቱ ህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ድንጋጌ ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው፡፡ የመንግስት አካላት በዚህ ጉዳይ ላይ ዝም ማለታቸው ሳያንስ ስለ ጉዳዩ በተጠየቁ ጊዜም "ይሄ የብርሃንና ሰላም ድርጅት ያወጣው ህገ ደንብ ነው እኛ በዚህ ላይ የለንበትም!፤" ማለት የህገ መንግስቱን አንቀፅ 13/1/ ድንጋጌ መዘንጋት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌደራልና የክልል የመንግስት አካላት ህገ መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው ያስገድዳል፡፡ በአንቀፅ 9/1/ "ማንኛውም ህግ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ-መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡" የሚለውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚጥስ ውል ሲዘጋጅ አያገባንም ማለት ህገ መንግስቱን አለማስፈፀም ነው ወይም የህገ መንግስቱን ድንጋጌ አንቀፅ 13/1/ መጣስ ነው፡፡ ይህ የድርጅቱ ውል ሚዲያው ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህን አስመልክቶ የኢትዮጵያ መንግስትን የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች አጠባበቅ የተመለከተው የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ኮሚቴ በስምምነቱ አንቀፅ19 መሰረት መንግስት ሚዲያዎች ከተፅዕኖ ነፃ መሆናቸውን እንዲያረጋግጥ የሚል ምክርና ተግሳፅ ለግሷል፡፡ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 13/2/ መሰረት በኢትዮጵያ የፀደቁ ስምምነቶች ሁሉ የሃገሪቱ ህግ አካል ናቸው፡፡ ህገ-መንግስቱንና ህግን ማስፈፀም ሲባል የእነዚህን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ድንጋጌዎችንም እንደሚመለከት ባለስልጣኖቻችን ቢያገናዝቡ ቢያንስ ቢያንስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚደርስባቸው ወቀሳና ውግዘትም ለመዳን ይረዳ ነበር፡፡ ለዜጎች ግን ህጎች ናቸውና ከነዚህ ስምምነቶች የመነጩ ድንጋጌዎችን ማጣቀስና መብትን መጠየቅ ይቻላል፡፡

ህግ በማውጣትና ህጉን እንደ መግዣ መሳሪያ መጠቀም የአምባገነን መንግስታት ባህሪይ ነው፡፡ የአሁኑ የማተሚያ ቤቶች ውል ደግሞ ዝቅ ብሎ መመከት መሆኑ ነው፡፡ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ውል አንቀፅ 10.1 አታሚው ድርጅት በአሳታሚው እንዲታተምለት የቀረበው ፅሁፍ ህግን ይጥሳል ብሎ ካመነበት የቀረበለትን ፅሁፍ ያለማተም መብት አለው፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የትኛው የመንግስት አካል ሆኖ ነው ለህትመት የቀረበው ፅሁፍ ህግን ይጥሳል የሚል ዳኝነት የሚሰጠው? ይህ ከሆነ የፍትህ ሚኒስቴር ምን ይስራ? ፍርድ ቤቶችስ ለምን አስፈለጉን? በፍርድ ሂደት እንኳን አቃቤ ህግ አንድ ህግ እንደተጣሰና ወንጀል መፈፀሙን መቶ በመቶ ለፍርድ ቤት ማስረዳት መቻል አለበት፡፡ የህግ የበላይነት አለ ከተባለ ህግ አስፈፃሚ ህግ አውጪ እና ህግ ተርጓሚ አካላት ያሉት መንግስታዊ ስርዓት ተዋቅሯል፡፡ ብርሃንና ሰላምን ጨምሮ ሌላው በዚህ ስርዓት ውስጥ ተሸከርካሪ ነው፡፡ እንደዚህ ከሆነማ ከዚህ በፊት በሚፅፉአቸው ፅሁፎችና ህትመቶች የተከሰሱ የታሰሩ የተበየነባቸው ጋዜጠኞች የፍርድ ሂደት በብርሃንና ሰላም ገላጋይ ውል የፍትህ ስርዓቱን ስራ ሊያስፈታ ነው ማለት ነው፡፡

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ተብሎ ከኃላፊነት ጋር በህግ ከተደነገገ በኃላ በማንኛውም መልኩ አስቀድሞ ክልከላ ማድረግ ከሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ መብቶች ሁሉ ግዴታንና ኃላፊነትን እንደሚጥሉት ሁሉ ሃሳብን በነጻነት መግለፅም የተቀመጠለት መስፈርት አለ፡፡ ለዚህ ደግሞ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 29/6/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት በህግ ሲገደብ አስተሳሰባዊ ይዘቱና ይዘቱ ሊያስከትል በሚችለው ለውጥ ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደማይገባም ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ ስለዚህ እንኳን የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ውል ይቅርና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚፀድቅ አዋጅ እንኳን አስተሳሰባዊ ይዘትና ይዘቱ በሚያስከትለው ለውጥ ላይ ገደብ መጣል አይችልም፡፡ መብቶቹ የሚገደቡባቸው የህግ መሰረቶችም ሆኑ እነዚህን ገደቦች መጣስ የሚያስከትላቸው ውጤቶች በህግ ተደንግገዋል፡፡

ይህ የዓለምን ህዝብ ሁሉ ብዙ ዋጋ ያስከፈለ በሃገራችን ደግሞ እውቅ ጋዜጠኞችን የፖለቲካ ተንታኞችን የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ለእስር ሌሎችን ለስደት እየዳረገ የሚገኘው ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የሚገደብባቸው ምክንያቶች እንዲሁ ብርሃንና ሰላም ፅሁፉ ህግን ይጥሳል የሚል እምነት ስለያዘ ሳይሆን የገደቡ አስፈላጊነት በቂ የሆነ ምክንያታዊ ዓላማ ባለው ህግ ሲደነገግ ብቻ ነው፡፡ ህግ ብቻ ሳይሆን ህጉ ምክንያታዊ መሆን ይኖርበታል ህጉም ምክንያታዊ ሆኖ ዓላማ ሊኖረው ይገባል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስትም ሆነ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የሚገደብባቸው ምክንያቶች በጥንቃቄ የተቀረፁና ገደቡን በመተላለፍ ህግ ተጥሷል ወይም አልተጣሰም የሚለውን ለመወሰን ሃሳቡ የተገለፀበት መንገድ የሃሳቡ ዓላማ ይህን ሃሳብ ከህጉ አንፃር መተርጎም የሚያስችል ገለልተኛ እና የተጣመረ እውቀት ይጠይቃል፡፡ ይህን ጉዳይ አንድ አታሚ ድርጅት እንደፈለገ ያድርገው ብሎ መፍቀድ ለህግ የበላይነት እና ለሰብአዊ መብት ጥበቃ ያለውን ዝቅተኛ የሆነ ትኩረት ያመለክታል፡፡ ከላይ የገለፅ ነው ምክንያታዊና ዓላማ ያለው ህጋዊ ገደብ በህገ መንግስታችን አንቀፅ 29/6 እንዲሁም በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነት አንቀፅ 19/3/ ስር ያሉትን መመዘኛዎች ያሟላ መሆን መቻል አለበት፡፡ አንድ ለህትመት የቀረበ ፅሁፍ በህግ መንግስቱ አንቀፅ 29/6/ የተደነገጉትን ገደቦች ማለትም የወጣቶችን ደህንነት አደጋ ውስጥ የሚከት የሰውን ክብርና መልካም ስም ያልጠበቀ የጦርነት ቅስቀሳ ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚነካ የአደባባይ መግለጫ መሆኑን አንድ አታሚ ድርጅት አንብቦ ውሳኔ እንዲሰጥ መፍቀድ ወይም ዝም ማለት ይህን ግዙፍ የሰብአዊ መብት ፅንሰ ሃሳብ ተራ ማድረግ ለመንግስት አሳፋሪ ለሁላችንም ግን ውርደት ነው፡፡ ይህ ተራ ነገር አይደለም ህመምና ፍቅር ጥላቻና እርቅ አንድነትና ልዩነት መቻቻልና መከባበር ሃገርና ሰው ጦርነትና ሰላም ሌላም ሌላም መልካምነቱና ጎጂነቱ በመርህና በምክንያት የሚገለፅበት የሰብአዊ መብት ትልቁ መዝገበ ቃል ነው፡፡ እውነት ማፈላለጊያ ነው፡፡ የራስን በራስ ማስተዳደር ቅድመ መገለጫ ነው የስብዕናና እውቀት ማጎልበቻ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሰብአዊ መብቶች አሉ፡፡

ስለዚህ መንግስት የሲቪልና ፖሊቲካ መብቶች አጠባበቁን አስመልክቶ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰብአዊ መብት ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርትው ላይ ለመግለፅ እንደ ተሞከረው በተለያዩ መንገዶች በፕሬስና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ላይ በራሱ በመንግስት አስፈፃሚዎች እንዲሁም በተለያዩ ድርጅቶች የሚደረገውን ጫና በማስቆም ለህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ተገዢነቱን ማሳየት አለበት፡፡

ህገ-መንግስቱና በህገ-መንግስቱ ለዜጎች የተሰጡ የሰብአዊ መብቶች ሲጣሱ ጣልቃ ገብተው ሪፖርት ለማውጣት ድርጊቱን ለማውገዝ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለመጠቆም የተቋቋሙ የዴሞክራሲ ተቋሞቻችንም በዚህ ጉዳይ ላይ ዝምታቸውን መስበር ግዴታና ኃላፊነትን መወጣት ነው፡፡

# ጦማረ አሚን



ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

ሁላችንም የግላችን የሆነ Sound Track አለን:: ያSound Track ያለፈ ጊዜያችን የአሁን ማንነታችን ነው:: አሁንን የሚረብሽ Sound Track አለ:: ድሮ ተቀነባብሮ እስካሁን ድረስ የሚደመጥ:: በግድ:: ከቀጭን የሸንበቆ አንደበት የሚፈስ ማሕዘኒ ቅላፄ ያለው የጊዜን ሕግ ሽሮ ከትላንት እስካሁን ያለን ማንነት አለን. . . በዚሁ ድብልቅነት ደግሞ አሁን የራስዋን ዜማ ከቀጫጭን የክራር ገመዶች በምንነት እየመዘዘች ነው. . . ዕዝኖቻችን ግን ሁለቱንም በዕኩል የድምጽ ከፍታ ማዳመጥ አይችሉም አንደኛው ከፍ ይላልና. . .

ከአሁን ቅድም. . . ከዛሬ ትላንት. . . ከአምና ካቻምና የተሻለ ቢሆንም. . . መልካምና ውብ የነበሩት ያለፉት ጊዜዎቻችን ግን ከአሁን የበለጡ ሊሆኑ አይችሉም (አሁን መልካም ባይሆንም እንኳ)::

የቅድሙን ውብ ሙዚቃ ተጫውተው ድምጻዊ. . . አሁንም እየተጫወተ ነው. . . ሥንተኛ Track ላይ እንዳለ ባላውቅም. . . ሽክላው ግን እየተሽከረከረ ነው. . . በመጀመሪያውና በሰባተኛው ሙዚቃ መካከል ግን የዜማ የሙዚቃና የሐሳብ ልዩነት በፍጹማዊነት አለ. . . ሕይወት ከሚሽከረከረው የሙዚቃ ሽክላ ልዩ አይደለችም. . . ሽክላው ሐዘንተኛ ሐሳብ ያላቸውን ሙዚቃዎች ተሸክሟል. . . ማሕዘኒ ዜማ ግን በውበት ሲሰራ ውብ ነው::

መቼም ሕይወት ላይ የሚያናድድ ነገር አይጠፋም አይደል?. . . ትናንሽ የሽክላ ጭረቶች የሙዚቃውን ጣዕም ይረብሹታል. . . ከሙዚቃው ሐዘንተኛ መንፈስ ይልቅ ባላዋቂ ጥፍር የተቧጨሩ የሽክላው ጆርባዎች. . . ዜማውን ያበላሹታል. . . አንድ ወዳጄ. . . ውብ እኔነቱን ብዙ ምርጥ ዜማዎቹን በማንነቱ ላይ እንደተሸከመ ራሱን በራሱ ለመስበር ሲሞክር ሞክሮም ተሰባብሮ. . . ሥብርባሪው ተለቅሞና ታሽጎ ወደ ዘለዓለም ፀጥታው ሲጓዝ ተመልክቻለሁ. . . በዚህም ከታላላቆች መስበር የታናናሾች ጭረት እንዲጎዳ አስተውያለሁ. . .

እንግዲህ አሁንን ለመኖር ያለፈን ተራኪ የሆነው የSound Track ድምጽ መቀነስ አለበት:: ትረካውንና ማጀቢያ ሙዚቃውን ዕኩል ለማዳመጥ የተፈጥሮ ሕግ አይደለምና:: መድረክ ላይ የቆሙት ሁለት ተዋናዮች በተመሳሳይ ደቂቃ ዕኩል ቢናገሩ አንድም ቃለ ምልልሱ የንዴት ጩኸት መሆን አለበት አልያም ስህተት ነው::

መደንበርና መበርገግ የሚመስል በግራና በቀኝ የሚደበደብ ጎርናና እና ስስ የድራም ድምጽ ያጀበው ማንነት አለ. . . የተቀጠቀጠ ጆርባው እስኪጠና ድረስ የትላንቱን የድራም ዱላ እና. . . ድብደባውን በማሰብ 'እንደምን ያለ ተራ ሙዚቃ ነበር?' ብሎ ተራውን ሙዚቃ እስከዛሬ ድረስ የሚያደምጥ. . . መሽከርከር የማይችል ቢሽከረከርም ማንነቱ ላይ አንድ አይነት ዜማ አንድ አይነት ቅንብር አንድ አይነት ሐሳብ የሆነ. . . ሥልቹ ዘፈን ዘፈኑ. . . ዘፈኑ ትላንት ነው:: ሠውዬው ግን አሁን:: ይህ የዚህ ሰው Sound Track ነው:: በሕይወት ብረቱ ክንድ የተመታ ማንነት::

አሁንና ቅድም፣ ዛሬና ትላንት፣. . . ዕለትና አምና. . . እኩል አይደሉም:: የአሁን ማንነታችን ግን በአምና ሙዚቃ የታጀበ ነው:: ዕዝኖቻችን ባረጀና በነተበ ፍቅር በተረሳም የትዝታ ዜማ የታጨቁ ናቸው. . . (የተረሳ ትዝታ). . . ስላለፈ ማንነት አሁንን ማጣፈጫ ቅመም እንጂ ያለፈን ማስታወስ አይደለም. . . ብዙዎቻችን ግን ባለፈ ትውስት ፈንጠዚያ ውስጥ ስለምንዋልል ከአሁን ፈገግታችን ይልቅ የአምና ኩርፊያችን. . . ከዛሬ ሳቃችን በላይ የካቻምና ዕንባችን የቅፅበት እኛነታችን ጋርደውታል መጋረጃው ግን መገለጥ ያለበት ከውስጡ ያለውን ለመመልከት ዓልያም የእኔነትን መቅደስ ለማፅዳት መሆን አለበት. . .

በገዛ አመለካከታችን (አስተውሎት) ራሳችን በራሳችን ላይ ያደረስነው በጣቶቻችን የሕይወታችን አጃቢ ሙዚቃ አለን:: በሰዎች ለስላሳ ጣቶች እንዴት እንደተነኩ ሳናውቅ ተነክተው ተዳስሰው ና ተጭነው የሚጮሁ ፒያኖ የሚመስሉ. . . ማንነቶችም አሉን (እኒህ ድምፆች ትላንት የተደረሱ የዛሬ ማንነቶቻችን ናቸው) ቢሆንም ሕይወት ሕልሞቻችንን ወደ ቅዠት ብትለውጥብንም እኛ ትላንት የተገኘን ነን እንጂ ዛሬ የተወለድን አይደለንም ከተወለዱ በኋላ ሕይወትን ከልደት ቀን ጀምሮ መቁጠር ዕድሜን ከሕልውና የመቀየጥ ሥህተት ነውና:: ስለዚህ የዛሬውን ለአሁን ተወው 'ንጂ ትላንትን ከዛሬ ጋር አትደባልቀው::

አዳዲስ ሙዚቃዎችን እያደመጥኩ ነው. . . ሽክላው እኒህን ሁሉ ሙዚቃዎች መሸከሙ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚያሰማኝ አናዳጅ ሙዚቃዎች ውበት ግን እያስገረመኝ ነው:: እጅግ በጣም የማረኩኝን ሙዚቃዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርጌ እያዳመጥኳቸው ነው. . .

አልፎ አልፎ ከጎዳና ወደ ጆሮዬ የሚደርሱ መንገደኛ ድምጾችን እሰማለሁ. . . አሁን ላይ ያለ የእኔነቴ ሃሳብ በሚሰሙት ድምጾች አልተረበሸም. . . ድምጾቹን ቢሰማም ለማዳመጥ የዕዝኑ መሳከው ክፍት አልነበሩምና ይህ ማለት ግን ድምጾችን ከመኖርና ከመስማት አያግዳቸውም እኚህ ድምጾች በሕይወታችን ላይ አልፎ አልፎ እንደሚከሰቱ ጭረቶች ሊሆኑ ይችላሉ. . . አልፎ አልፎ ጭረት ቢኖርም የሽክላውን ሙዚቃ ሊያውከው ይችላል:: ቁስለቱ የዳነ ጠባሳም ከሚመረቅዘው ልዩ ነው. . .

እኔ ብዙ አይነት Sound Track ያለኝ የአሁን ሰው ነኝ:: የትኛዋንም ቅጽበት ሕይወት እንድትሞላ የማደርገው ትላንትና አስሮ ሊገንዘኝ የሚሻውን አጃቢ ሙዚቃ የጩኸቱን መጠን በመቀነስ ነው:: በሕይወት ሰሌዳ ላይ ጽፈነው ያመጣነው ሙዚቃ የድምጽ ሃይል ሊቀንስ እንጂ. . . መጥፋት አይችልምና::

ትዝታ (ወደ ኋላ መፍሰስ) ትላንትን ዛሬ ላይ ከመመኘት የሚመጣ ነገር ነው:: ዛሬ ላይ አብረውን ያሉትን ሰዎች ወደ ኋላ አናስባቸውም. . . ትላንት የተዉንን (የተዉናቸውን) ሰዎች ግን ዛሬ ላይ ልናስባቸውና ልንመኛቸው. . . ወደ ኋላ እንፈሳለን ከወንዙ ወደ ምንጩ. . . ከደረስንበት ወደ ተነሳንበት. . . በዛሬ ሰውነት በአሁን እግር ላይ ቆመን. . . የድምጹን መጠን ቀንሼ የማደምጠው አንድ ብቸኛ የኔ ብቻ የሆነ Jazz አለ. . . ርዕሱም 'አንቺ ብቻ' የሚል ሲሆን እርሷም እርሷ ናት:: ይህን ሙዚቃ እኔና እርሷ ካቻምና አቀናብረነው እስካሁን ድረስ የማዳምጥበት ምክንያት. . . ከዚህ ከፍ ያለ አቅም ያለው ሙዚቃ እስካሁን ለጆሮዬ ባዳ ስለሆነ ይሆናል. . . ቢሆንም ያሙዚቃ ያምራል ማለት ይህኛውን ማጣጣል አይደለም የተሻለ ነው ማለት 'ንጂ. . .

የዚህ ቅጽበት መዝሙሬ እርሷ ብትሆንም እኔ የአሁን ሰው ስለሆንኩ የትላንትና ልሰልስና. . . የረጋ ፈሳሽ ወንዝ ነበረውን ውቡን የውበት Jazz አንቺ ብቻ ለእኔ የሚለውን የድምጽ መጠን እጅግ በጣም ቀንሼዋለሁ:: የአሁን ሰው ስለሆንኩ::

ይሕን ሙዚቃ በሰማሁት ቁጥር ጊዜ በሕሊና ላይ ሃይል እንደሌለው እረዳለሁ ጊዜ ማለትም ትላንት. . . አምና. . . አልያም ካቻምና ምሰላቸው ሁኔታቸው በአይምሮ ላይ ብቃት የላቸውም እላለሁ. . . (ድፍን አምስት አመት ሆነኝ:: እርሷን ከተመለከትኳት:: ሙዚቃውንም ለሦስት ዓመት ያህል ሰርተን ከጨረስነው) እንግዲህ ይህም ሙዚቃ. . . እስካሁን ድረስ መስማት እሻ ነበር. . . ያለምንም መደባለቅና መደባለቅ::

ይህን የሁለታችንን የJazz ሙዚቃ ሰርተን እንደጨረስን ዋሸንት የነበረውን ሸምበቆ እንጨት ነው ብዬ ሰባበርኩት. . . በሳክስፎኑ አንደበት. . . አቧራ በተንኩበት. . . በአናቱም የትዝብት ጢስ ወጣ. . . እርሷ ግን 'ይህ ውብ የJazz ሙዚቃ ከነዚህ የተገኘ ነው' አለችኝ እኔ ግን የአሁን ሰው ስለሆንኩ 'በአዲስ መሳሪያ አዲስ ሙዚቃ እፈልጋለሁ' ብዬ የተኛችበት የተቃኘውን ተጫውቼ ግንባሯ ላይ! ለመጨረሻ ጊዜ. . . ግንባሯን ተሳልሜ ወጣሁ. . . እንግዲህ ከአምስት ዓመት በኋላ እርሷን ሳስብ ትዝ የሚለኝ ሙሉ ጨረቃ የሚመስል ገላዋና ግንባሯን ስስም የነበረው አይኗ አስተያየት ብቻ ነው:: ከአምስት ዓመት በኋላ እንደ ከአምስት ዓመት በፊቱ ትታየኛለች:: የጊዜ ሕግ በህሊና ላይ ሃይል የለውም:: ይህ ሁሉ ቢሆንም ከዛችኛዋ ትዝታ ይልቅ የዚህች ዝግ ያለ የጠዋት ዝናብ የመሰለ ጭቅጭቅ ያዘለ ሙዚቃ የተሻለ የድምጽ ከፍታ አለው. . . የዛችን ብሰማም የዚህችን አዳምጠዋለሁና::

እንግዲህ እርሷ (ያቺ) በማለት በእኔነት መደብ ስቆም ትላንት?. . . ከትላንት ወድያ አምና ካቻምና. . . ካምስት ዓመት በፊት ብቻ ናት:: አሁንና ይህ ቅጽበት ግን እኔ ነኝ:: እኔ ፍጻሜው ምን አይነት እንደሆነ ባላውቅም የነገን ሙዚቃ ዛሬ እያቀናበርኩኝ ነው:: ልዩነቱ ቀዳሚዋ ሽክላ ከጨረቃና ርጋታ ካለው ሃይቅ ስትሰራ. . . ሁለተኛዋ ግን ከጉም ከጢስና ከጎርፍ የተቃኘች ናት::

ሽክላው እየተሽከረከረ ነው. . . ስለጨረቃና ስለረጉ ሐይቆች ያቀነቅን የነበረው ሙዚቀኛ አሁን ደግሞ ከጉምና ከጢስ ከጎርፍና ከድፍርስ ውሃ ስለምትመሳሰል እንስት እየጮኸ ነው::

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# አጫጭር ዜናዎች

## ሲፒጄ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ያቀረበው ውል ቅድመ-ምርመራ ነው ሲል ተቃወመ

የጋዜጠኞች መብት ተቆርቋሪ ተቋሙ ሲፒጄ ከትናንት በስቲያ ባወጣው መግለጫ ከሁለት ሳምንት በፊት በመንግስታዊ ተቋሙ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አማካኝነት ለግል አሳታሚዎች የቀረበውን ውል ቅድመ ምርመራ ነው ሲል ተቃውሞውን ገልጿል:: የተቋሙ የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ቶም ሮዴስ ውሉን ‹‹ቅድመ-ምርመራን ህጋዊነት ማልበስ ነው›› ከማለቱ ባለፈ እንዳይተገበር ጠይቋል::

እንደ ሲፒጄ መግለጫ የሪፖርተር ጋዜጣ ባለቤት አቶ አማረ አረጋዊ የማተሚያ ቤቱ አካሄድ ቅድመ-ምርመራን የሚከለክለውን በህገ-መንግስቱ የሰሰፈረውን አንቀፅ ሃያ ዘጠኝ፤ የፎቹን ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር ታምራት ገ/ጊዮርጊስ እርሱን ጨምሮ ሌሎቹ የግል አሳታሚዎች ውሉ ለማተሚያ ቤቱ የሚሰጠውን ህግን የሚፃረሩ የሚመስሉ ዕሁፎችን የመዳኘት መብት እንደማይቀበሉት ተናግሯል::

## የ78 ዓመቱ አርሶ አደር በማዳበሪያ እዳ ራሳቸውን አጠፉ

በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ ሮቢት 03 ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር የኋላሸት መኮንን የተባሉ የ78 ዓመት አዛውንት በማዳበሪያ እዳ ራሳቸውን ሰቅለው ገደሉ::

አርሷ አደሩ በብድር እንዲወስዱ የተደረጉትን ማዳበሪያ ክፍያ እንዲፈፅሙ ካልሆነ ይታሰራሉ የሚል ማስፈራሪያ በቀበሌው ባለስልጣናት ስለደረሰባቸው ሚያዚያ 26/2004 ዓ.ም. ጊቢያቸው ውስጥ በሚገኝ ዛፍ ላይ ራሳቸውን ሰቅለው የተገኙ መሆኑን የለፍትህ ምንጮች ገልፀዋል::

በአካባቢው የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎችና የልማት ሰራዊት ነን የሚሉት የገዢው ፓርቲ ተጠሪዎች አፈሩ ሳይጠና ከውጪ የመጣውን ማዳበሪያ አርሶ አደሮቹ በግዳጅ ከመንግስት እንዲወስዱ ያስገድዷቸዋል ሲሉ ምንጮቻችን ጨምረው ተናግረዋል::

በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ ሮቢት 03 ቀበሌ ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ሽፈራው ጓንጉል ስለ ጉዳዩ እንዲያብራሩ በፍትህ ጋዜጣ ተጠይቀው ሲመልሱ ‹‹ውሸት ነው:: ሰውዬው ራሳቸውን ያጠፉት ከሚስታቸው ጋር አለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት ነው እንጂ በማዳበሪያ ምክንያት አይደለም›› ሲሉ ለፍትህ ገልፀዋል::

## የፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ 13ኛ የሙት ዓመት ሰኞ ታስቦ ይውላል

እውቁ የቀዶ ጥገና ስፔሻሊስትና የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት መስራች ፕሬዚዳንት የነበሩት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ 13ኛ የሙት ዓመት ሰኞ ግንቦት 6/2004 ዓ.ም. በባለወልድ ቤተክርስቲያን ታስቦ እንደሚውል የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት /በአህድ/ ለፍትሕ በላከው ደብዳቤ ገለፀ::

ፓርቲው በላከው ደብዳቤ ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ በከፋ ሁኔታ በደቡብ ክልል እየተፈናቀሉ ያሉ የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች እንዲቆሙ የሚመለከተው አካል ሁሉ ልብ ሊለው እንደሚገባ በድጋሚ ድርጅታዊ አቋሙን ገልጿል::

## ልዑል መኮንን ት/ቤት 50ኛ አመቱን ነገ ያከብራል

የቀድሞ ልዑል መኮንን የአሁኑ አዲስ ከተማ መሰናዶ ት/ቤት የተመሰረተበትን 50ኛ አመት የወርቅ እዮቤልዩ በዓል ነገ ሊያከብር ነው::

ት/ቤቱ ያስተማራቸው 2700,000 በላይ ተማሪዎች በሀገሪቱ በተለያዩ የስራ ሀላፊነቶች ተሰማርተው ይገኛሉ:: እነዚህ የት/ቤቱ ተማሪዎች የነበሩ ግንቦት 4/2004 በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ተገኝተው ትዝታቸውን አንስተው በመጨዋወት እና ስለቀጣዩ የት/ቤቱ ሁኔታ በመመካከር እንደሚያከብሩ ት/ቤቱ በተለይ ለፍትሕ በላከው ደብዳቤ ገልጿል::

## በአምስት ዓመት ህፃን ላይ የግብረሰዶም ወንጀል የፈፀመው ግለሰብ ተፈረደበት

በአምስት ዓመት ህፃን ልጅ ላይ የግብረሰዶም ወንጀል መፈፀሙ በማስረጃ የተረጋገጠበት ሳሙኤል ታደሠ የተባለው ተከሳሽ የፌዴራል መደበኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 7ኛ ወንጀል ችሎት በ24/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወሰነ::

ተከሳሹ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 631/1(ለ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከእርሱ ጋር አንድ አይነት ፆታ ባለውና ለአካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ የግብረሰዶም ወንጀል ለመፈፀም በ15/05/2004 ዓ.ም. አስቦ እንደነበረ የክስ ዝርዝሩ ያስረዳል::

በተጠቀሰው ዕለት በግምት ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ሲሆን በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ‹‹ዶልፊን ሆቴል›› አካባቢ ተከሳሹ ህፃኑን ወደ ቤቱ በመውሰድ የግብረሰዶም ድርጊት የፈፀመበት መሆኑን ፍ/ቤቱ በማስረጃ ማረጋገጡን ገልጿል::

በመሆኑም ፍ/ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት በዋለው ችሎት ‹‹ተከሳሽን ያርማል፣ ሌሎችንም ያስጠነቅቃል›› ባለው በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ እና ለአምስት ዓመት ከሕዝባዊ መብቱ እንዲሻር ወስኗል::

## ባለዕራይ ወጣቶች ማህበር ውይይት አደረገ

ባለዕራይ ወጣቶች ማህበር በአመቻች ኮሚቴ ከተመሰረተ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የማህበሩ አመራር እና አባላት በ8/08/2004 ዓ.ም. በፓኖራማ ሆቴል ውይይት ማድርጉን ማህበሩ ለፍትህ በላከው ደብዳቤ ገለፀ::

ማህበሩ ባደረገው ውይይት ላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ቀርቦ የማህበሩም ዋንኛ አላማ ኢትዮጵያዊ አንድነት በመገንባት ላይ ማተኮር እንዳለበት እንዲሁም በሀገሪቱ ከሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በጋራ አጀንዳ ዙሪያ ለሚደረገው ውይይት ተወካዮችን መምረጥ የሚሉት አጀንዳዎች ለውይይት መቅረባቸውን ደብዳቤው ያብራራል::

የማህበሩ አባላት በማህበሩ አመራሮች ላይ በተናጠል ተፅዕኖ እያደረጉ እና እየሰፈሩ ያሉትን አካላት ተፅዕኖ ለመቋቋም ያላቸውን ቁርጠኝነት በመግለጽ ማህበሩ የጀመረው የአባላት ምልመላ አጠናክሮ ባጭር ጊዜ ውስጥ በአስሩም ክፍለ ከተሞች የማህበሩ ምስረታ ይፋ እንዲሆን ውሳኔ መተላለፉንም ማወቅ ደብዳቤው ጨምሮ ገልጿል::

## ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ዓለም አቀፍ ሽልማት ተሸለመች

ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ራሳቸውን ለአደጋ በማጋለጥ በአስቸጋሪ አካባቢዎች መስራት ለቻሉ ጋዜጠኞች የሚሰጠውን ሽልማት ማግኘቷን የአለም አቀፉ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን /IWMF/ ባለፈው ሳምንት አሳወቀ:: የሃገሯን ገዥ ስርዓት በመተቸቷ ለእስር እንደተዳረገች የሚገልፀው የተቋሙ ዘገባ በሀገሪቱ ውስጥ በብቸኛ ሴት የፖለቲካ ተንታኝነት በፍትህ ጋዜጣ በዓምደኝነት ስትሰራ መቆየቷን በመጥቀስ ከአዘርባጃን እና ከፍልስጤም ከተመረጡ ሁለት ሴት ጋዜጠኞች ጋር የ2012 ሽልማት ተሸላሚ ሆናለች:: የሽልማቱ ይፋዊ ስነስርዓትም እ.ኤ.አ በኦክቶበር 24 እና 29 በኒውዮርክ እና በሎስ አንጀለስ ከተሞች እንደሚካሄድ ታውቋል:: ጋዜጠኛ ርዕዮት በሽብርተኝነት ክስ ተጠርጥራ ስትከራከር ከቆየች በኋላ ፍርድ ቤቱ ‹‹ጥፋተኛ ነች›› ሲል የ14 ዓመት ብይን በመስጠቱ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንደምትገኝ ይታወቃል::

# የፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም አዎንታዊና አሉታዊ ትምህርቶች

## ኢ/ር ታደሰ ኃ/ሥላሴ

በፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም የተፃፈው ‹‹አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ›› መጽሐፍ ደግሜ ደጋግሜ ያነበብኩት ሲሆን በፀሐፊውና በመጽሐፉ የሰፈሩት አንዳንድ ሀሳቦች ላይ ያሉኝን አስተያየቶች ከዚህ ቀጥሎ ለጋዜጣው አንባቢዎች አቀርባለሁ፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን በሥራ ዓለም ከተሰማሩበት ዘመን ጀምሮ በሠሩት ሥራ በሁላችንም ኑሮ ላይ ተጽእኖ ፈጣሪ ናቸው፡፡ ተራ ሰው አይደሉም፡፡ እንዲያውም ከንጉሠ ነገሥቱም- ከኮሎኔል መንግሥቱም፣ ከአበበ ቢቂላም- ከጥላሁን ገሠሠም በላይ በኢትዮጵያ ወጣቶች ህይወት ላይ ከባድ ጫና ያሳረፉ ምሁር ናቸው፡፡ አራት ኪሎንና ፕሮፌሰር መስፍንን የማያውቅ የተማረ ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት አልደፍርም፡፡ የሰውነት ተክላቸው ለእኔ ጥርጣሬ ያመቻል፡፡ እሳይ የጻፍኩትን የምትቀበሉኝ (የምንተማመን) ከሆነ የሚከተለውን ልትቀበሉ ግዴታ ይሆንባችኋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ላለፉት 50 ዓመታት የተጓዝንበት፣ የኖርንበት፣ አሁንም ያለንበት የእድገት ሁኔታችን የፕሮፌሰር መስፍን የሥራ ውጤት ነው፡፡ የእሳቸው ምርታማነት የሚለካው በኢትዮጵያ እድገት ነው-በሳይንስ ትምህርት Work done is zero የሚባል ሁኔታ አለ ስለዚህ የፕሮፌሰር ሥራ ውጤቱ ዜሮ ነው ወይስ የተወሰነ ምርት አምጥቷል? በሳቸው ቋንቋ ኢትዮጵያውያን ቁልቁለትን እያገባደድን? ወይስ ዳገቱን ተያይዘናል? የሚለውን ጥያቄ መገምገምና መልስ ማግኘት ይኖርብናል፡፡ ተገቢም ይመስለኛል፡፡

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ ሲከፈት ከንጉሡ የተሰጠን መመሪያ ስድስት ኪሎ ራስ መኮንን ህንፃ መግቢያ ላይ ተጽፎ ይገኛል ቃሉም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡ ‹‹ኩሉ አመክሩ ወዘሠናይ አጽንዑ›› ትርጉሙም ሁሉን መርምሩ መልካም መልካሙን ገብዩ፤ በዚህ መመሪያ በመነሳት የፕ/ር መስፍንን ‹‹አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ›› መጽሐፍንና በ50 ዓመታት ያመረቱትን በማጤን ጽሑፌን በሶስት ንዑስ ክፍሎች አዘጋጅቻለሁ፡፡

ሀ. የፕሮፌሰር አዎንታዊ ሥራዎቻቸው

1. በሰው ልጆች እኩልነት ያምናሉ! በተፈጥሮ ሰው ሆነን በመፈጠራችን ሁላችንም በህግ ፊት እኩል ነን ብለው ያመናሉ፡፡ ገዥና ተገዥ በትውልድ ሳይሆን በትምህርት፣ በሥራ ውጤት፣ እንዲሆን ያወጁ ሽንጣቸውን ገትረው ያስተማሩ ምሁር ናቸው፡፡ ከገዥ መደብ ያልተወለዱ ሁሉ ይህን አቋማቸውን በጣም ይወዱላቸዋል፡፡

2. ደፋር ናቸው- የሚያምኑበትን በድፍረት፣ በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ከመናገር ወደኋላ አይሉም፡፡ መንግሥቱ ኃይለማርያም እዚህ መጣ-እዚህ ደረሰ ሲሉን መግቢያ መውጫ የሚጠፋን ሰዎች ብዙ ነበርን፡፡ ኢትዮጵያ ካላት ምሁራኖች ሁሉ እኔ እስከማውቀው ድረስ ፕሮፌሰር መስፍን እና ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ብቻ ኮሎኔል መንግሥቱን ፊት ለፊት ገጥመው እንደኮሶ የሚመሩ እውነታዎችን እንዲጋት ያደረጉ ሁለቱ ሰዎች ብቻ በአገራችን ተገኝተዋል፡፡

3. ፕሮፌሰር በዚሁ በአዲሱ መጽሐፋቸው ጦርነት ለሰው ልጆች ምን ያህል ጠንቅ መሆኑን በሰፊው አብራርተውልናል፡፡ የሰው ልጆች ተነጋግረው ችግሮቻቸውን በሰለጠነ መንገድ መፍታት ሲገባቸው እጅግ ከባድ አውዳሚ የጦር መሳሪያ እያመረቱ መተላለቃቸው በትንሹም ቢሆን የአውሬነት ጠባያቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ ፕሮፌሰሩ በያዝነው ምዕተ አመት ይህን ልማድ ከምድራችን እንድናጠፋ በብርቱ መክረውናል፡፡ ኢህአዴግንም የጦር መሳሪያን ሁሉ ወደ አካፋ፣ ዶማና ማረሻ እለውጣለሁ ያለውን መፈክር መልሶ እንዲታጠቀው ምክራቸውን ለግሰውታል፡፡

4. ፕሮፌሰር መስፍን በዚህ አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ በሚለው መጽሐፋቸው ከማንም ምሁር በበለጠ የኢትዮጵያን ጂኦግራፊ ተንትነዋል፡፡ አገራችን በዚህ ቦታ በመገኘቷ እስከዛሬ ያለፈችበትን አስቸጋሪ ጉዞ ወደፊትም ሊገጥማት የሚችለውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ቀውሶችን በመዘርዘር ከሚያጋጥምዎት ችግሮችም የመፍትሄ ሀሳቦችን በጥልቀት በመተንተን አቅርበዋል፡፡

ለ. የፕሮፌሰር አሉታዊ ትምህርቶች

1. የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም በአገራችን ስር እንዲሰድ ካደረጉት ምሁራኖች አንዱ ናቸው፡፡ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም የሰው ልጆች እኩል ሆነው ራቁታቸውን የተወለዱ በመሆናቸው በኑሮአቸውም እኩል አንድ ዓይነት ሁሉም አብሮ ድሀ ወይም ሁሉም አብሮ ሀብታም ይሁኑ ሲል፣ በግል የማሰብን ነፃነት ሙሉ በሙሉ ከልክሎ ሥልጣን ላይ በተቆናጠጡት መሪዎች ሀሳብ ብቻ እንዲገዛ ማለትም እኛ በምናስብልህ ብቻ ተራመድ የሚል ፍልስፍና የያዘ ነው፡፡ የሰው ልጅ ተፈጥሮንም የካደ ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ የዚህ እምነት የመጀመሪያው ፈጣሪዎች ሶስት ሰዎች ሲሆኑ ሁሉም ጆሮ የላቸውም ተብለው ይታማሉ፡፡

በተጨባጭ የምናየውም ሶሻሊዝም የሰው ልጆችን ከድህነት የማያወጣ የጭቆና አስተሳሰብ ሲሆን የካፒታሊዝም ግን የሀብታምነትና የህግ የበላይነት፣ የሰው ልጆች ተደስተው፣ ስቀው፣ ተዝናንተው፣ የሚኖሩበት መሆኑን ነው፡፡ እውነት ለጊዜው ትደበቅ እንደሆነ እንጂ ጠፍታ አትቀርም፣ ፕ/ር መስፍን ከእነ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ከመሳሰሉት ምሁራኖች ጋር በመቆም በአገራችን የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም አራማጅ ናቸው፡፡

ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ለሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም አራማጆች ጥብቅና በመቆም ህይወታቸውን አራዝመዋል፣ ከሌሎች የሚለዩት የአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ ካልተመለሰ በማለት ብዙ ደክመዋል! ከነዚህ ከሁለት ሥራዎቻቸው ኢትዮጵያውያን ምን ያህል እንደተጠቀምን ልንገመግማቸው ይገባል እንጂ በዝምታ ማለፍ አይገባንም፡፡ ፕ/ር መስፍን በዚሁ ርዕዮተ ዓለም በመመራት መሬት ላራሹ የሚለውን መፈክር በማስተጋባታቸው በዚህ መፈክር ምክንያት ረሃብ ከአገራችን እንዳይጠፋ አድርገዋል፡፡ በዚሁ በአዲሱ መጽሐፋቸው ከገጽ 155 እስከ 163 ስለረሃብ በአገራችን ተንሰራፍቶ መገኘት ያቀረቡዋቸውን ሀሳቦች በጥሞና ልናጤናቸው ይገባል፡፡ እኔ አልቀበላቸውም፡፡ አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ መሰለኝ! የራሳቸውን ስህተት ለመደበቅ ያደረጉት ሙከራ ነው!

2. የገዥነት መብት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው ብለው የሚያመልኩትን የሰለሞንና የንግሥት ሳባን ዘሮችን ከስልጣን አስወግደዋል፡፡ ማስወገዳቸው ባለከፋ ነበር! ጥያቄው በምን ተኳቸው ነውና? በሬ ሆይ ሳርሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ ቀረህ እንደሚባለው ተረት!

3. ሰው በላሽ የሆነውን የደርግ አገዛዝ በንጉሣዊ አገዛዝ ምትክ በላያችን ላይ ጭነዋል፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ ወይስ የደርግ አገዛዝ፤ የቱ ጠቀመን? የሚለውን በሰከነ መንፈስ እንወያይበት!

4. የደርግ አገዛዝም ከሳቸው አስተሳሰብ አፈንግጦ ሲራመድ (የሾለ ብዕራቸውን በመጠቀም) ውስጡ ሆነው፣ ተገርስሶ እንዲወድቅና በኢህአዴግ እንዲተካ ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል፡፡

5. የኢህአዴግ መንግሥት በእርስዎ ትምህርት አልመራም እምቢ ሲላቸው የሰብዓዊ መብት ጉባኤ አቋቁመው ሙግት ገጥመዋቸዋል፡፡ ከኢህአዴግ ጋር በፈጠሩት ውዥንብር ለሁለት ዓመታት እስር ቤት መማቀቃቸውን አንርሳ!

6. ቅንጅት የሚባለውን የተቃዋሚ ድርጅት በማቋቋም በሳቸው የውስጥ አመራር እንዲንቀሳቀስ ሲሞክሩ ዳገት መውጣት ሲሆንባቸው ትተው ወጥተዋል፡፡ በዚህ ልፋታቸው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ አባት የሚል የማዕረግ ስም (ከፕሮፌሰርነት በላይ ይመስለኛል) ሰጥታቸዋለች፡፡ ይህ ማዕረግ ለሶቭየቱ ሚካኤል ጎርባቾቭም የተሰጠ ነው፡፡ የኢትዮጵያም ምሁር ከጎርባቾቭ እኩል መሆናቸው ስንገነዘብ ሊያስደስተን ይገባ ይሆናል፡፡

7. የፕ/ር የ50 ዓመታት የትምህርት ውጤት የኢትዮጵያ ልጆች ኢህአፓ የሚባል የፖለቲካ ድርጅት አቋቁመው ለኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆኑ፣ ለራሳቸውም ሳይሆኑ እንደጉም በነው አልቀዋል፡፡ ነጭ ሽብር ቀይ ሽብር በማለት የኢትዮጵያ ወታደሮችና ወጣቶች እርስ በእርሳቸው ሲተላለቁ ከማየት በላይ ለኢትዮጵያውያን የበለጠ አሳፋሪና አስከፊ ውርደት አልነበረም፡፡ የሚገርመው ወጣቶቹም ወታደሮቹም የፕሮፌሰሩ ተማሪዎች የነበሩ መሆናቸው ነው!

8. በተጨማሪ የፕሮፌሰር አድናቂ የሆኑት የትግራይ ወጣቶች ደደቢት በረሃ በመግባት ተደራጅተው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ለ17 ዓመታት ደርግን በጠመንጃ ትግል ገጥመው የደርግንም ሠራዊት ፍርክስክሱን በማውጣት በአሁኑ ጊዜ በንጉሡ ነገስቱ ወንበር ተቀምጠው ኢትዮጵያን እየመሩ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወጣቶች ይመሩበት የነበረው ርዕዮተ ዓለም አክራሪ ሶሻሊዝም ሲሆን ይህንንም ርዕዮተ ዓለም አዲስ አበባ ለመግባት ሱሉልታ ሜዳ ሲደርሱ አውልቀው በነጭ ካፒታሊዝም መተካታቸውን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በጻፉት መጽሐፍ ላይ አስነብበውናል፡፡ ሆኖም ለውጡን የኢህአዴግ አመራሮች፣ ለኢህአዴግ አባሎችም ሆነ ለፕሮፌሰር መስፍን በይፋ አልነገሩም፣ አላስፈቀዱም፣ የኢህአዴግ አባሎችን እና የአስተማሪያቸውን የፕሮፌሰር መስፍንን ቁጣ ፈርተው ይመስለኛል፡፡

9. ፕ/ር መስፍን በዚህ በአዲሱ መጽሐፋቸው የአፍሪካ ቀንድ ሲሉ የቆጠሯቸው የአገሮች ስም ዝርዝር ውስጥ ኡጋንዳንና ግብጽን ቢጨምሩ ለነዚሁ ለአፍሪካ ቀንድ አገሮች የችግሮቻቸው መፍቻ ብለው ያቀረቡት ሀሳብ ክብደት ይኖረው ነበር፡፡ የአባይን (ናይልን) ወንዝ ሁኔታ ከቀሩት ሁለት አገሮች ውጭ አከፋፍላለሁ ብሎ ማሰብ ጉም እንደመጨጥ ይሆናልና!

10. ፕ/ር መስፍን በአዲሱ መጻፋቸው የሀረር ክፍለ ሀገር ብለው የጠሩትን 2/3ኛው ለእርሻ የማይሆን በርሃ ነው ብለውናል፡፡ እኔ ባየሁበት የሀረር 2/3ኛው አፈሩ ቀይ ሲሆን ከባሌና ከጋራሙለታ ተራሮች በዝናብ ታጥቦ መጥቶ በሰፊ ሜዳው ላይ የተከማቸ ስለሆነ ለእርሻ እጅግ ተስማሚ ሲሆን አንድ ቢሊዮን የሚሆነውን የአለም ህዝብ ሊመግብ የሚችል ሀገር ነው፡፡ በቆራሄ ሜዳ ላይ የሚፈነጥዙት ግመሎች በሰውነታቸው ትልቅነት ከዝሆን የሚያንሱ አይደለም፡፡ የሐረር ክፍለሀገር ችግሩ በቂ ውሃና የሚያለማው ነዋሪዎች ወይም ሰፋሪዎች አለማግኘቱ ነው!

11. ፕሮፌሰሩ አሁንም በዚህ መጽሐፋቸው ሱማሌዎች የሚኖሩበት አካባቢ በሙሉና ኡጋዴንም ጭምር የነሱ የራሳቸው የሱማሌዎች መሆኑን በማመናቸው በእጅጉ ተሳልቀውባቸዋል! ፕሮፌሰሩ ኡጋዴን በደጋው አገር ለሚገኙት የነፍጠኞቹ የአማሮች አገር ነው ብለው ሊያሳምኑን ይሞክራሉ፡፡

አሁንም በዚሁ መጽሐፋቸው የፈረንሳዩም፣ የእንግሊዙም፣ የኢጣሊያኑም፣ የኢትዮጵያም ሱማሌዎች አራቱም ተባብረን አንድ የሱማሌ ሪፖብሊክ እንፍጠር በማለታቸው ብዙ ይኮንኖአቸዋል፡፡ ፕሮፌሰሩ ለአንድ ቀን ለሊት ሱማሌ ሆነው ተወልደው ቢሆን አሁን የያዙትን አስተሳሰብ መቶ በመቶ እንደሚለወጡ እርግጠኛ ነኝ፡፡ መተባበርና መዋሀድ እንዴት ይኮነናል፡፡ ሱማሌዎች እንደልባቸው እንደሚኖሩበት ሐረር ከተማ ድረስ ያለውን አካባቢ ወይም ክልል በግድም በውድም ካላገኙ መቼም ጊዜ ቢሆን ጦር ማንሳታቸው አይቀርም፡፡ ኢትዮጵያውያንም ይህን አገር ለሱማሌ አንለቅም ብለን ሁልጊዜ መዋጋታችን አይቀርም፡፡ ለሁለታችንም ሁኔታው ከባድ ነው! ምን ይሻላል? ወጣቶች በጦርነት ከማለቅ ዘዴ ፈልጉለት!

12. ፕ/ር መስፍን አሁንም በዚሁ መጽሐፋቸው የኡጋዴን በርሃ ሰፊ ስለሆነ የደጋውን መሀል አገር ለመውረር በባህር በኩል የሚመጣን ጠላት ውጦ ስለሚያስቀርልን የኢትዮጵያ አካል ሆኖ መቅረት አለበት በማለት በጥሞና ይሰብካሉ፡፡ የአለም ህዝብ ይህን አስተሳሰብ አይቀበላቸውም! እኔም አልደግፋቸውም፡፡

13. ፕ/ር መስፍን በዚሁ መጽሐፋቸው እሳቸው የዴሞክራሲ አባት ተብለው በወ/ት ብርቱካን የተወሰዱበትን ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝና ጠባቂ የሆነውን አሜሪካ ክፉኛ ወቅሰውታል፡፡ አሜሪካኖች በራሳቸው አገር ዴሞክራሲን ለምን ተከተላችሁ በማለት ሽብርተኝነት የአልቃይዳን ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች ሊገድሏቸው ስለሞከሩ አሜሪካኖች አልቃይዳን በገባበት ጉድጓድ እያሳደዱ ማጥፋታቸው እንደትልቅ ሀጢአት በፕሮፌሰር መስፍን ተቆጥሮባቸዋል፡፡

ቢንላደን (የአልቃይዳን እምነት መሪ) ቢሆንለት ኖሮ ሶስት መቶ ሺህ ንፁህ ሲቪል አሜሪካኖችን በአንድ ጊዜ በመግደል የአላህ ቅዱስ መልእክተኛ መሆኑን ሊያውጅ ሞክሮ ሶስት ሺህ ብቻ መግደል ችሏል፡፡ ታዲያ አሜሪካኖች አንዱን ጉንጫቸውን የመታውን ሁለተኛውን ጉንጭ እንዲመታ አዙራችሁ ስጡት የሚለውን የፕሮፌሰርን ትምህርት ያልተቀበሉ እንደሆነ ይህ ሁሉ ወቀሳ ይገባቸዋልን?

ሐ. በእኔ በኩል ለውይይት የማቀርባቸው ሀሳቦች

ፕ/ር መስፍን በአዲሱ መጽሐፋቸው ትልቅ ሀሳብ ለወጣቱ አቅርበዋል፡፡ ይህ ሀሳብ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ውህደት ይፍጠሩ የሚል ነው፡፡ ይህ ሀሳብ በጣም የሚደገፍ ሲሆን ከረሃብና ከድህነት ለመውጣት በኢኮኖሚም እጅግ የበለጸገ አገር ለመሆን ፍቱን መድሀኒት ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ይህን የውህደት አስተሳሰብ ጥቅሙንና ጉዳቱን ብትንትን አድርገን እንድንወያይበት በአንክሮ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥሞና ገምግሙልኝ!!

1. የኢትዮጵያ መሀል አገር ተራራማ በመሆኑ በሰማይ የሚሮጠውን ደመና በመያዝ ወደ ውሃ- ወደ ዝናብ ይለወጣል፡፡ እነዚህ ተራራማ ቦታዎች ለእርሻ አይሆኑም፡፡ ጥቅማቸው ለቱሪስቶች መስህብ እና ዝናብን ከመፍጠር አኳያ ነው፡፡

2. የኢትዮጵያ ተራራማ መሀል አገርን የከበቡት የሱማሌ፣ የሱዳን፣ የግብጽ፣ የኤርትራም፣ የኬንያም ካለዚህ ውሃ መኖር አይችሉም፡፡ በውሃ ጥም ያልቃሉ፡፡ በመሬት ላይ ያለው ሃቅ ይህ ነው፡፡ ውሃ ጥቅሙ ለምግብ፣ ለመብራት ኃይል፣ ለመንገድም ነው፡፡ ኢትዮጵያ ይህን ጥቅም ልታጋራቸው ይገባል፡፡

3. በመሀል ተራራማ ቦታ ላይ የሚኖሩት ሰዎችም ከከበቧቸው ከሱማሌ፣ ከኤርትራ፣ ከሱዳን (ሰሜኑም ሆነ ደቡብ) ከኬንያና ከግብጽ ሰዎች ተነጥለው መኖርም አይችሉም፡፡ ጀግኖች አባቶቻችን መሀል አገሩን አናስደፍርም፤ ተነጥለን እንኖራለን ብለው በአጥንታቸው በደማቸው ጠብቀው እስከዛሬ ያቆዩን አገር ውጤት ዴሞክራሲ፣ ፍትህ የሌለበት እና በረሃብና በጥም እንድናልቅ ነው ያደረጉን! በወሎ፣ በትግራይ፣ በሰሜን ሸዋ በረሃብ ያለቀውን ኢትዮጵያዊ ማናችንም አንረሳውም!

4. ከመሀል ተራራማ አገር የሚመነጩት ወንዞች ተጠቃለው (አባይ የሚል ስም ይዘው) ወደ ግብጽ የሚፈሱትን ገድበን አቅጣጫቸውን አስለውጠን ወደ ኡጋዴን እንዲፈሱ ማድረግ አለብን፡፡ ይህ ይቻላል፡፡ ይህን ብናደርግ የአፋርና የኡጋዴን ሰፋፊ ሜዳዎች ብቻ ሳይሆን ለቻይናዎችም ለህንዶችም በቂ የምግብ እህል እናመርትላቸዋለን፡፡

5. የኦጋዴንን ምርት ወደ መሀል አገር ለማምጣት የባሌንና የሀረርን ተራሮች ሽንቁረን በቦይ (Tunnel) ካላመጣነው አሁን እንደተያዘው በየብስ አጓጉዘን ብናመጣው ምርታማ አንሆንም የማጓጓዣው ዋጋ በጣም ይበዛል፡፡ በየብስ 1500 ኪሎ ሜትር እና ሁለት ሺህ ሜትር መውጣትና መውረድን ከ400 ኪሎ ሜትር ታናል ከመቆፈር ጋር ወጭውና ገቢውን ማስላት ነው፡፡ ናዝሬትን ወይም አዋሽ ከተማን ከጎዴ በታናል ብናያይዝ ኢኮኖሚያችን ያድጋል፡፡

6. ደቡብ ሱዳን - ደቡብ ኢትዮጵያን በኬንያ አሁን ከሚሰራ ከኪሰማዩ ወደብ ጋር በቱርካና ሀይቅ በኩል በካናል ማገናኘት ለገቢና ለወጭ ሸቀጦች ማጓጓዣ ቀላሉና ርካሽ ዘዴ ነው፡፡ የሱዳንን ነዳጅ በቱቦ ከማውጣት በዚህ ካናል ቢጓጓዝ አስተማማኝ ዘዴ ይሆናል፡፡

7. ኢህአዴግ ለበርካታ ዓመታት ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ፍላጐት ካለው ይህ የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን ውህደት ሊያምንበትና ሊቀበለው ስለሚገባ ፅንሰ ሀሳቡን ከፕሮፌሰር መስፍን ተምረው፤ ፕሮፌሰሩም በትጋት አስተምረው፤ ትምህርቱንም ማለፋቸውን አረጋግጠው፤ ካልገባቸውም በተለመደው ቀይ ቀለም ዜሮ በማከናነብ ደግመው ደጋግመው እንዲያጠኑ አርገው፤ በመቀጠልም የሚቀጥሉትን የኢኮኖሚያችንን ማሻሻያ ዘዴዎች በሥራ ላይ እንዲያውሉ ማስደረግ ለውህደቱ የመጀመሪያ እርምጃ ይሆናል፡፡

8. የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚያድገው መብራትና የመብራት ኃይል በሁሉም ከተሞች የስርጭት ሥራን በግል ኢንቨስተሮች እንዲመራ ሲደረግ ነው፡፡ አንድ የኤሌክትሪክ መሐንዲስ ሁለት መኪናዎች ይዞ ጥቂት ሰራተኞችን አደራጅቶ የአንድ የከተማ ከፍተኛ የመብራት ስርጭትን ሊሰራና ሊጠብቅ ይችላል፡፡ የኤሌክትሪክ ፍሰት አይቋረጥ አይባልም፡፡ ሆኖም በአጭር ጊዜ በትንሽ ዋጋ ብዙ ብልሽት ከመድረሱ በፊት ተጠግኖ አገልግሎት መቀጠሉ ለአገር እድገት ወሳኝ ነው፡፡ ይህን ሥራ ለኢንቨስተሮች ወይም በግል ለተደራጁ የኤሌክትሪክ መሐንዲሶች አወዳድሮ ጨረታውን ላሸነፈው ቢሰጥ ሁላችንም ተጠቃሚ እንሆናለን፡፡

9. የጤና ተቋማትን በተመለከተም ቢሆን በመንግስት አካላት ከሚተዳደሩ ይልቅ ጉዳዩ በግል ሀኪሞች ቢያዙ የሚያረካ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም፡፡ ያሉን ሆስፒታሎች ሁሉ በግል ሀኪሞች ተደራጅተው እንዲሰሩባቸው ይደረግ! ህዝቡ ጎበዝ ባለሞያና አነስተኛ ክፍያ የሚያስከፍለውን ሀኪም ራሱ እየመረጠ ሄዶ ይታከማል፡፡ በዚህ መሰረት ቢሰራ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከመሞት ይተርፋሉ፡፡ በአሜሪካ ኦባማ የገጠመው ችግር ሀኪማችሁን እኔ ልምረጥላችሁ በማለቱ ነው! ኦባማ የፕሮፌሰር ግርፍ መሆን አለመሆኑን እያጣራሁ ነው! የሶሻሊስት አስተሳሰብ ይዞ የአሜሪካን ህዝብ እያስቸገረ ነው! እሳቸው በመጽሐፋቸው አሜሪካኖች እየተማሩባቸውመሆኑን አስነብበውናል፡፡

10. የትምህርትም ጉዳይም ቢሆን ወጭ ለሁሉም ማዳረስ አይቻልም፡፡ ተማሪዎችንም ሆኑ አስተማሪዎች ምርታማ የሚሆኑት በግላቸው ተወዳድረው ሲሰሩና ሲማሩ ነው፡፡ ይህ አሰራር መንግስታችን ባልበሰሉ የወጣት ጭንቅላት ከመመራት በበሰሉ የፓርላማ አባላት እንድንመራ ከማስቻሉም በላይ እያንዳንዱ መምህር እንደ ምርቱ ብዛትና ጥራት ደመወዝ ሊከፈለው ያስችላል፣ መንግሥትም ከተማሪዎችና ከመምህራን ንትርክ ይወጣል! ወጭውንም ይቀንስለታል፡፡ ሌላውን ሀላፊነቱም በብቃት እንዲወጣ ሸክሙ ይቀልለታል፡፡ ባጭሩ በምንሰራው ሁሉ ልማታዊና ምርታማ እንሆናለን፡፡

11. የባንክ አገልግሎት፣ የባንክ ባለቤትነት ከመንግሥት ውጭ መሆን አለበት፣ የባንክ ባለቤት መንግሥት ከሆነ በቸገረው ቁጥር ከባንክ በቀላሉ መበደሩ አይቀርም! የመውሰጃው መንገድ ተዘርዝሮ አያልቅም! ባንኮች በራሳቸው ገቢ ከተዳደሩ ሳይወዱ ምርታማና ቀለጣፋ ይሆናሉ!! እኔ በምገለገልበት ቁራ አካባቢ የኦሮሚያ ባንክ በአንድ ክፍል ውስጥ የምትሠራ አለች! ትልልቆቹ የንግድ ባንክም ሁለቱ አሉ! ገንዘብ ወደ መንዲ ከተማ ለማስተላለፍ ከትልልቆቹ ከንግድ ባንክ አውጥተን ለትንሿ ለኦሮሚያ ባንክ የምንሰጥበት ሁኔታ አለ ምክንያቱም፣ ትንሿ የኦሮሚያ ባንክ ቢበዛ በግማሽ ቀን የምታስተላልፍልንን፣ ትልልቆቹ የንግድ ባንኮች በሶስት ቀናት አያደርሱልንም፣ ሰበባቸው ተቆጥሮ አያልቅም፡፡ የስልኩ መስመር ሳይቀር ለትልልቆቹ ባንክ ይለግማል፡፡ አይሰራላቸውም! የባንክ ሥራ አለምንም አድሎ ለመንግሥትም ለግሎችም በእኩል ቢተው የጎልያድና የዳዊት ታሪክ በአጭር ጊዜ በአገራችን ይደገማል፡፡ ትንንሾቹ ትልልቆቹን ገፍትረው እንደሚጥሏቸው አትጠራጠሩ! ሁለቱም ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ አንዱ ቀልጣፋ ሌላው ዘገምተኛ! አንዱ የመንግሥት ሌላው የግል!

12. በቴሌ ሥራ አገራችን እንኳንስ ከአለም ከአፍሪካ ቀንድ አገሮች ጭራ የሆነችው ሥራው በመንግሥት ስለተያዘ እንጂ የቴሌ ሰራተኞች ሰነፍ ፍጡር ሆነው አይደለም፣ የፕሮፌሰር የሶሻሊዝም ትምህርት በደንብ ስለገባቸው፣ ብልጥም ስለሆኑ፣ ሳይሰሩ ስለሚበሉ ነው፡፡ በመንግስትም በኩል የቴሌ ሥራ ወተት እንደምትሰጥ ላም ጠዋትና ማታ ገንዘብ የምታስታቅፍ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው! ሃቁ ግን ለመንግስት ብዙ ገንዘብ ሊገኝበት የሚችለው ሥራው በግል ኢንቨስተሮች ቢሠራና መንግስትም በውለታው መሰረት ድርሻውን መሰብሰብ ሲችል ነው፣ መንግስትና ኢንቨስተር ቢቀናጅ የኢትዮጵያ ህዝብ የበለጠ ይጠቀማል፡፡

13. የኑሮ ውድነት ከሁለት አሀዝ ወደ አንድ ወርዶ አገራችንም በኑሮ ውድነት ከአለም አንደኛ ከመሆን ይልቅ መሀከል ደረጃ ልትሆን የምትችለው መሬት ብሎም የእርሻ መሬትን ገበሬው ሲሸጥ ሲለውጥ ብቻ ይመስለኛል፡፡ የኢህአዴግ አባላት ይህ አስተሳሰብ በእነሱ መቃብር ላይ እንጂ በጭራሽ መታሰብ እንደሌለበት አውጀዋልና ቢያንስ 6 ሚሊዮን ያህል የኢህአዴግ አባላት ከሚሞቱብን ይህን ምኞት እናቆየውና ሌላ ዘዴ ፕሮፌሰር እንዲያስተምሩልን እንማጸናቸው! እኔ ያገኘሁት ዘዴ አክሲዮኖች የሚሻሻሉበት አሰራርና ማህበር በመፍጠር ከመንግስት በሊዝ ሰፋፊ መሬት ወስደን ወደ እርሻ እንግባ! የማረስ ሀሳብን ከለወጥን (ካልፈለግን) አክሲዮናችንን በመሸጥ ከማህበሩ ልንወጣ እንችላለን፡፡ ይህ ዘዴ ምናልባት በምግብ እህል ራሳችንን እንድንችል ይረዳናል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው መንግስት ለአክሲዮን ግዢና ሽያጭ ገበያ መመሪያና ህግ ሲያወጣልን ብቻ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የአክሲዮን ግብይት የሚከናወንበት ሁኔታ በኢትዮጵያ እንደሌለ የታወቀ ነው፡፡

በመዝጊያም ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም የኢትዮጵያ ህዝብን ሊክሱ ይገባል፡፡ ብዙ በድለውናል፡፡ በህልማችን ማርና ቅቤ እያጠጡን ሲያጓጉን ኖረዋል፡፡ በንግግራቸውና በትምህርታቸው ዴሞክራሲ፣ ፍትህ፣ በኢኮኖሚ የበለፀገች ኢትዮጵያ እንድትፈጠር ይፈልጋሉ ይመኙልናል፡፡ በሌላ በኩል ይህን ዴሞክራሲ ይህን ፍትህ የኢኮኖሚ ብልጽግና እንዳንጎናጸፍ እንቅፋት (ጋሬጣ) ሆነውብናል፡፡ በእውነት ለእውነት ረጋ ብላችሁ አስቡት፤ እውነቱ ኮሶም ቢሆን ተግተን ከበሽታችን መፈወስ አለብን፡፡

የፕሮሬሰርን እድሜ ከጤና ጋር ያርዝምልን!

አለም አቀፍ

# ህግ እንደ መሳሪያ? “የአፍሪካኖች” እጣ ፋንታ.....?

ማንኛውም የህግና የፖለቲካ ክርክር በተነሳ ቁጥር “መቼት ሳይመርጡ” በጠቅላላው ህግን የፖለቲካ ቡድን ጥቅም ማስከበሪያ መሳሪያ አድርገው የሚተረጉሙ የህግ ባለሙያን ደግሞ ጋሪ እንደሚጎትት ፈረስ ወደ ፊት እንጂ ግራና ቀኙን ማየት እንደማይችል ባለሙያ ወይም ታዛዥ ሮቦት አድርገው የሚያስቡ አንዳንድ ግለሰቦች ይህንን ፅሁፍ ለመፃፍ መነሻዎቼ ናቸው፡፡ ይህ ፅሁፍ “ህግ” የቡድን ጥቅም ማስፈፀሚያ መሳሪያ አይሆንም በማለት የሚሞግት አይደለም ይልቁንስ “ህግ” መቼና በምን አይነት ስርአት ውስጥ የፖለቲካ ቡድን ጥቅም ማስፈፀሚያ መሳሪያ ይሆናል የሚለውን ለማየት እንጂ፡፡ በአንድ ሀገር ያለው የህገመንግስት ስርአት፤ የፖለቲካ ስርአት አደረጃጀት እንዲሁም የፍርድ ቤቶች የህግ ስልጣን እና ተጨባጭ ተግባር ለህግ ባለሙያዎች ሚና እና ማንኛውም ክዋኔ ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡

“ህግ” በፍላጎት ተፅእኖ ስር ያልወደቀ አመክንዮ ነው ‹‹Law is a reason unaffected by desire›› ብሎ ነበር አርስቶትል፡፡ ህገ-ፍልስፍና (Jurisprudence) ህግ ምንድን ነው? ለሚለው እና መሰል ጥያቄዎች የተለያዩ ፍልስፍናዊ አመለካከትና ትርጓሜ ቢሰጠንም ለዚህ ፅሁፍ አላማ በስፋት አለ በሚባለው ህገ-መንግስታዊ ዲሞክራሲ ስርአት ህግ ማለት ምንድን ነው የሚለውን እንመልከት፡፡ “ህግ” በሰፊው ስንተረጉመው የፖለቲካና የህግ ሰነድ ከሆነው ህገ-መንግስት ይጀምርና እሱን መሰረት አድርገው የሚወጡ አዋጅዎችን፤ደንቦችን፤መመሪያዎቹን የሚያጠቃልል የማህበረሰብን ጥቅም ለማስከበር የሚወጣ የመግባቢያ ሰነድ ነው ልንል እንችላለን፡፡ በህገ-መንግስታዊ ስርአት ህጎች የራሳቸው የሆነ ደረጃ አላቸው፡፡ ህገ-መንግስት የማህበረሰቡን ትክክለኛና ያልተበረዘ ይሁኝታ ለስርአቱ መሰረት በሚሆኑ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ላይ ሰብሰብ አድርጎ የሚያወጣ ሰነድ ነው ተብሎ ስለሚታመን ከሁሉም የበላይ ህግ ነው፡፡ ስለዚህ ህገመንግስቱን የሚቃረኑ ማናቸውም ህግጋት (አዋጅ፤ደንብ፤መመሪያ) የባለስልጣኖች ውሳኔ እና ሌሎችም ዋጋ አልባ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ የማህበረሰቡ የምሃላ ቃል (swear words of a nation) ህገ መንግስቱ በማንኛውም ሁኔታ ከተበከለ (ትክክለኛ የህዝቡን ፍላጎት በቅንነት በተገቢው መንገድ ካላስቀመጠ) ይህንኑ መሰረት አድርገው የሚወጡ ፍሬዎቹም (ህግጋት፤የባለስልጣን ውሳኔዎች እና ሌሎችም) የመመረዝ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም ስርአቱን ጠቅላላ የመመረዝ ጉዳት ማምጣቱ አይቀሬ ነው፡፡

**ህገ-መንግስት እንደ “ቅዱስ መፃህፍት”**

በህገ መንግስት የሚተዳደር ሀገር ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ይልቁንስ ህገ መንግስት ያላቸው ሃገራት ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ላይሆኑ እንደሚችሉና ሁሉም ህገ መንግስቶች ለህዝብ ጥቅም ያልቆሙ እንደሆኑ መገንዘብ ይህንን ፅሁፍ ለመረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ህገ መንግስት የህዝብን ፍላጎት መግለጫ፤ የሰላም የልማት እና የዲሞክራሲ ማስፈኛ መሰረት እንደሚሆን ሁሉ የግል ወይንም የቡድን ጥቅም ማስከበሪያ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ አፍሪካዊ መሆን በተግባር የተደገፈ እውቀት ለመገብየት የተሻለ አጋጣሚ ነው፡፡

የህገ መንግስት ስርአቶች ዲሞክራሲያዊ ናቸው ለማለት የህገ መንግስቱ ስርአት ግንባታ ሂደት “ትክክለኛነት” ትልቅና የማይተካ ሚና አለው፡፡ በህገ መንግስት ማርቀቅና ማፅደቅ ሂደት የሚከሰቱ የህገ መንግስት መሰረታዊ የሆኑ “ስህተቶች” የሃገሪቱን መሰረት አሸዋ ላይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የበላይ ህግ እያልን አታሞ የምንደልቅለት ህገ መንግስትና እሱን ተከትለው የሚወጡ ህግጋት እና ውሳኔዎች የእንቧይ ካብ ከመሆን አያመልጡም፡፡ እንዲህ ያለው መሰረታዊ ችግር የተፈጠረው ታልሞና ታስቦበት ካልሆነና የፖለቲካ ምሰሶ የሆነው ቅንነትን የያዘ ከሆነ እራሱ ሰነዱ በሚያዘጋጀው የማሻሻያ ስርአት ስለሚስተካከል የችግሩ ዘለቄታ እምብዛም ነው፡፡ ይሁን እንጂ በእቅድ የግል አሊያም የቡድን ርካሽ ጥቅም ለማጋበስ ተብሎ የህገ መንግስት ግንባታ ሂደት ከተበላሸ ህገ መንግስት ተብሎ ስም የሚያገኘው ሰነድ ፍትሀዊነት የጎደለው የተንኮል ሰነድ እንጂ እንዴት ህግ ሊሆን ይችላል? በእንደዚህ አይነት ሂደት የተገነባን የተንኮል ሰነድ እንደ ቅዱስ መፃህፍት ማምለክስ ለስርአቱ ይሁኝታ አሊያም ህጋዊነት (Legitimacy) መስጠትስ አይሆንምን?

**እኔ ከሞትኩ......?**

የህዝባቸውን የአጭርና የረዥም ጊዜ የጥቅም ሁኔታ ለማስከበርና ሃገሪቱ የዛሬ ትውልድ ብቻ ሳትሆን የነገዎቹም እንድትሆን በህገ መንግስት ስርአት ግንባታ ሂደተ የሚሳተፉ የወቅቱ ተደማጮችና ባለሙያዎቻቸው የዛሬና የነገን የግልና የቡድን የፖለቲካ ጥቅም ስሌት ውስጥ ሳያስገቡ በጊዜው የተሻለ ተቀባይነት ያለውን የህዝብ ሃሳብ መሰብሰቢያ ፍልስፍና ተጠቅመው ህዝቡ “ያልተበረዘና” ከማንኛውም ጫና ነፃ የሆነ ሃሳቡን እንዲገልፅ በማድረግ የሃገሪቱን መሰረት ሊፈርስ በማይችል ትልቅና ጠንካራ መሰረት ላይ ይገነባሉ፡፡ እንዲህ ያሉት ተደማጮችና ለጊዜው መንበረ ስልጣኑን የሚይዙት አካላት (በምንም ይምጡ በምን) እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ከሚሉት አይነት ሳይሆኑ እነሱ ትተውት የሚሄዱት ሀገር ባለተራው ትውልድ ሲመጣ ከዜሮ እንዳይጀምር አልያም በስልጣኑ አልባሌ ተግባር እንዳይፈፀም የህዝብ ፍላጎቶችን በቅንነት በአግባቡና በተገቢው ሁኔታ ሳይሸራርፉና ሳይጨማምሩ በማስቀመጥ የሃገሪቱን ስርአት በጠንካራ መሰረት ላይ በመጣል ስማቸውን ህያው ያደርጋሉ፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ነገሮችን ለማከናወን ቀን ከሌት የሚጥሩ ለህዝባቸው ያደሩ ግለሰቦችና ቡድኖች እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒው (በምንም ይምጡ በምን) የያዙትን ስልጣን እንዴት እንደሚያራዝሙት፤ በፈለጉት መንገድ “ህግ” እያወጡ ህዝቡን በህግ ስም እያሸማቀቁ እና ስህተቶቻቸውን ፍትሀዊነት በጎደለው ህግ ስም እያከናወኑ ባጠቃላይ ሙሉ ጊዜአቸውን ጥንቃቄ የተሞላበት የተንኮል ጥናት የሚያከናውኑ ባለጊዜዎችም ቢሆኑ አልታጡም ፡፡እነዚህ አደራ በል ስግብግብ ባለጊዜዎች ይህንን እቅዳቸውን ለማሳካት በህገ መንግስት የማርቀቅና የማፅደቅ ሂደት ሁለት አይነት የተለመዱ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ አንደኛው በሚፈልጉት መንገድ ሰነዱን በማዘጋጀት ለህዝብ አቅርቦ ህዝቡም ግድፈት ያለበትን ፍላጎቱ እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የፍቃድ ግድፈት በተለያየ መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ከእነዚህም መካከል በተንኮል የማይረባና ሃሰተኛ ፕሮፖጋንዳ በመንዛት ፍላጎታቸውን ያንፀባረቁበትን አንቀፅ ትኩረት እንዳያገኝ በማድረግ፤ነፃ የሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች በህገ መንግስት ማርቀቅና ማፅደቅ ሂደት ያላቸውን አስተያየት በአግባቡና ነፃ በሆነ መንገድ እንዳይገልፁ በመግታት፤ጫና ያሳድራሉ የሚባሉ ግለሰቦችና ቡድኖችን በሃይል በማስፈራራት ወይም በመደለል ገንቢ ሚናቸውን እንዳይጫወቱ በማድረግ፤በማሳሳት እና በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ተንኮሎች ግድፈት ሊፈፀም ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ የህዝብን ፍላጎት (public will) በፕሮፖጋንዳና በማስታወቂያ ለመቀየር ትልቅ ዘመቻ ያካሂዳሉ፡፡ ሁለተኛው ሰነዱን ጭራሽ ለህዝብ ሳያቀርቡ በሀሰት ፕሮፖጋንዳ የህዝብ ይሁኝታ ያገኘ በማስመሰል እራሳቸው ማፅደቅ ነው፡፡ በሁለቱም መንገዶች የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን የፕሮፖጋንዳ ሚና ማብዛትና የግል ሚዲያን ማጥፋት ለያዙት የማስቀየስ ተግባር ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ ለምን ቢባል ፕሮፖጋንዳና ማስቀየስ ተስፋ በሌለበት ተስፈኛ ህዝብ በመፍጠር በስነ-አመክንዩ (logic) ሳይሆን በስሜት የሚነዳ ማህበረሰብን የመፍጠር እድሉ ከፍተኛ ነውና፡፡

**ህገ-መንግስታዊ ተንኮል?**

Legitimacy of wrongs

የህዝብ ይሁኝታ (legitimacy) ሳይኖራቸው መንበረ ስልጣኑን ከያዙ በኋላ የግልና የፖለቲካ ቡድን ጥቅም የሚያስፈፅሙ ኢ-ፍትሃዊ ህጎችን እንደፍላጎታቸው የሚያወጡበት ሁኔታ ማመቻቸት፤ ህዝቡ ስርአቱን መሰረት አድርጎ የሚጠይቅበትን ሁኔታ ዝግ ማድረግ ወይም ዉጤታማ የማይሆንበትን ተግባራዊ ሂደት መፍጠር፤ በህግ አዉጪ፣ በህግ አስፈፃሚና በህግ ተርጓሚ ወይም በዳኝነት ስርአት መካከል የሚኖረውን የምጥጥንና የቁጥጥር (Check and Balance) ሂደት እርስ በእርሱ እንዲሆን በማድረግ አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ አይነት ስርአት መዘርጋት፤ህገ መንግስታዊ ሊሆኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች በዕቅድ (Deliberately) በመዝለልና ህገ-መንግስታዊ ሊሆኑ የማይገባቸውን ለአማራጭ የፖለቲካ ሙከራ ክፍት መሆን የሚገባቸው የፖሊሲና የፖለቲካ ጉዳዮችን ህገ-መንግስታዊ በማድረግ አማራጭ አስተሳሰቦችን እንዳይመጡ በመዝጋት፤ ይህንን ስርአት የሚዘረጉት የተንኮል ኢንጅነሮች ነብይ አይደሉምና ሁሉን ነገር ቀድመው መገመትና መተንበይ ስለማይችሉ አንዳንድ በጊዜ ሂደት የሚከሰቱ ክስተቶችን በፈለጉት መንገድ ለመግራት ያወጡትን የተንኮል ሰነድ (ህገ-መንግስት) ተቃርነውም ቢሆን ህግ ማውጣታቸው ስለማይቀርና ይህንንም ተከትሎ የሚመጣ ጥያቄ እንደሚኖር ስለሚገምቱ የህገ-መንግስት ትርጉሙን ስራ በፖለቲካ መንገድ እንዲያልፍ ማድረግ፤ በአንድ በኩላ የዳኝነት ስርአቱን ነፃነት ዲስኩር በመንዛት በሌላ በኩል ደግሞ ፍትህ የማያውቁ የፍትህ አካላትን እራሳቸው ወደ ዳኝነት አካል የሚያመጡበትን ወይም የሚመርጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤ከሃገራዊ ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለሃገርና ለህዝብ የሚበጅ ትክክለኛና አማራጭ ሳይሆን ለፖርቲያቸው የሚያደላ የምርጫ ዘዴ (Electoral System) ለራሳቸው የሚያመዝነውን የሃገሪቱ የምርጫ ዘዴ በማድረግ፤መብቶችን በጠቅላላው መርህ (General Principles) ላይ በገፍ የሰጡ በማስመሰል ሰፋ ያለ ልዩ ሁኔታ (Exceptions) በማስቀመጥ ልዩ ሁኔታዊ እንደ መሰረታዊ መርህ በተደጋጋሚ በመጠቀምና በሰፊው በመተርጎም የበታች ህጎችን በዚህ መሰረት በማውጣት ህግን እንደ ጦር ሜዳ መሳሪያ ይጠቀሙበታል፡፡ ይህ ሁሉ ሰነድ ተቀምሮም ላወጡት መላም እራሳቸው ታማኝ አይደሉም እናም ህገመንግስት ያለ ህገመንግስታዊነት (Constitution without Constitutionalism) ያለበት ስርአትን ያራምዳሉ፡፡

**ዕውቀት፤ቅንነት፤ ፅናት፤ ፍቅር...**

የማይወዱት ሃገርና ህዝብ መምራት፤ምን ማለት እንጅ ምን መስራት እንዳለባቸው የማያገናዝቡ መሪዎችን ይፈጥራል፡፡ የሃገሪቱን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ ከማሳካት ይልቅ ጊዜያዊ የፖለቲካ ሞገዶችን እየተከተሉ ህዝብ መስማት ይፈልጋል ብለው የሚገምቱትን በመተረክ፤ በማስተረክ እና በማስቀየስ ጊዜያትን ማስቆጠር ትልቅ አላማቸው ይሆናል፡፡ ለነገሩ መሰረታዊ የትክክለኛ ብቁ መሪ ባህሪይት የሆኑትን ዕውቀት፤ ቅንነት፤ ፅናት፤ ፍቅር፤....የማያሟሉ ግለሰቦችና ቡድኖች እንዴት ሃገር ይመራሉ? “የሚመራውን” ህዝብ ችግር የማይቆረቁረው፤ስልጣኑን ለውንብድና የሚያመቻች፤ እውቀት የሌለው፤ አሊያም እውቀት ኖሮት ተንኮልን የህይወቱ መንገድ ያደረገ መሪ እንዴት ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሊገነባ ይችላል? የአሜሪካ ፕሬዘዳንት የነበሩት John Fitzgerald Kennedy ስለዲሞክራሲ እንዲህ ብለው ነበር፡-

‹‹ዲሞክራሲያዊ ስርየት አስቸጋሪ የአስተዳደር ዘዬ ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከፍተኛ የስብዕና ልቀት ማሳያ የሆኑትን ራስን- መግራት፣ ለአጠቃላዩ ማህበረሰባዊ ጥቅም መገዛትን እና ዕውቀትን ይሻል፡፡››

Hotshot Lawyers.....?

ኢ-ፍትሃዊ ህጎች (Unjust Law) እንደልብ በሚወጡበት፤ከህገ-መንግስት (ጉድለቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) የሚቃረኑ ህጎችን የዳኝነት ስርአቱ ውድቅ ማድረግ በማይችልበት፤ የህገ-መንግስት ትርጉም ሙሉ በሙሉ በፖለቲካ ውሳኔ በሚያልፍበት ስርአት የህግ ተርጓሚ ሚና እስከምን ድረስ ሊሆን ይችላል? በእንደዚህ ጉራማይሌ ስርአት ውስጥ የሚገኙ የህግ ባለሙያዎች የጋሪ ፈረስ፤ ሮቦት፤ ወይንስ Hotshot Litigant Lawyers?

**ኧረ መላ መላ......?**

የማይለወጥ አስተሳሰብና ስርአት ባነገበ ግለሰብና ቡድን የሚመራ ሃገር፤ ማህበራዊ እሴቶቻቸዉና ስርአቱ ተስፋ ቢስና ጨለምተኛ አመለካከት እንዲያነግቡ ባደረጋቸው ተቃዋሚዎች የተሞላች ሃገር እመኑኝ ገና ለውጥ አልጀመረችም፡፡ ሌላ ዜሮ ያስፈልጋታል፡፡ (If discord and antipathy in the opposition and immutability in the ruling party is a fact; the real process for change still is not commenced.) እውነተኛ መሪ እንዴት ማምጣት ይቻላል? በሰላማዊ ትግል፤ በጦርነት፤ ወይንስ በሌላ አማራጭ? ጥቂቶች በከፈሉት መስዋትነት ተጠቃሚ መሆን በዚህ ዘመን የሚቻል አይመስለኝም፡፡ በጥቂቶች መስዋትነት የሚመጣ አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ አይከሰትም ለምን ቢባል ይህም የመስዋትነቱን ሂሳብ በግልና በቡድን ጥቅም ለማወራረድ ይፈልጋልና፡፡ ይህም አሁን እንዳለንበት በማንፈልገውና በአፍሪካ ባለው አይነት የጨቋኝና የተጨቋኝ አዙሪት ያስገባናል በአፍሪካ ለውጥ ለማምጣት በስልጣን ላይ ያሉት ግለሰቦችና ቡድኖች የተሻለ እድል አላቸው፡፡ መጥፎ ማህበራዊ እሴቶቻችንን ለመቀየር፤ የዲሞክራሲ መሰረት የሚሆኑትን የህዝብ ተሳትፎ፤ ህገ-መንግስታዊነት፤እና ሌሎችም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የኔነትና የእንብላው ደዌን ማስወገድ ከቻሉ ስልጣን ላይ ያሉ መሪዎች ለዲሞክራሲ መሰረት መጣል ይችላሉ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የአፍሪካዉያን ዘላለማዊ እጣ ፍንታ ጭቆና መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

# የእርዳታ እና የችጋር

... ከገፅ 2 የዞረ

መብትን መጨፍለቅ አልፎም የመሬት በግል ይዞታ አለመሆንን በምክንያትነት አስቀምጠዋል፡፡ ከእርሳቸው ውጪ የአማርቲያ ሴንን እና የአሌክስ ዲ ዋልን ተመጋጋቢ ሙግቶች በኢትዮጵያ አውድ ለማየት የሞከሩት አሌክሳንደር ቫዳል በአሁኒቷ ኢትዮጵያ ችጋር ተጨባጭ አደጋ መሆኑን በመጥቀስ ለዚህም የሀገሪቱን የዴሞክራሲ ዕግዳት በምክንያትነት አንስተዋል፡፡ ከብዙዎቹ የፖለቲካው ተከታታይ ምሁራን ድምዳሜ በተጨማሪ ከጥቂት ዓመታት በፊት ይፋ የተደረገው የለንደኑ የፍሪደም ሀውስ ጥናት የቫዳልን መከራከሪያ የሚደግፉ ይመስላል፡፡ እንደ ተቋሙ ዘገባ ኢትዮጵያ ከ1997 ዓ.ም. ወዲህ ከነበራት ‹‹ከፊል ነፃ›› መደብ ወደ ‹‹ነፃ ወዳልሆኑ›› ሀገራት ተርታ ገብታለች፡፡ የፖለቲካ እና የሲቪል መብቶችን መከበርን በሚያካትተው በዚህ ምደባ ኢትዮጵያ ኤርትራን ወደ መሰሉ ፍፁም አምባገነን መንግስታት ጋር ለመፈረጅ ሁለት እርከኖች ብቻ ቀርተዋት ተቋሙ አምስት ነጥብ በመስጠት ‹‹ለምርጫ ፖለቲካ የማትሆን›› ሲል ሰይሟታል፡፡ የኦስሎ ዩኒቨርስቲው መምህር አሌክሳንደር ቫዳል “Understanding famine in Ethiopia: poverty, politics and Human rights” በሚለው ፅሁፋቸው ይህንን እና ሌሎች የዴሞክራሲያዊ ሂደቱን መጨናገፍ የሚነግሩ ሁነቶችን በመጥቀስ ‹‹ኢህአዴግ ችጋርን ቀዳሚ መንግስታዊ አጀንዳው ለማድረግ የሚቻለው አይመስልም›› ሲሉ ደምድመዋል፡፡ ዶ/ር ቫዳል ለዚህ ድምዳሚያቸው የመሬት ስሪቱን እና የእርሻ ግብዓት አቅርቦትን በተጨማሪነት ያነሳሉ፡፡ በመሬት ስሪቱ ላይ በቫድልም ሆነ በሌሎች ምሁራን የሚቀርበው ትችት ግልፅ ፖለቲካዊ ጭብጦችን ይይዛል፡፡ መሬት የመንግስት መሆኑ ገዢው ፓርቲ በአርሶ አደሩ ላይ ግዙፍ የበላይነት እንዲኖረው አስችሎታል፡፡ ይህ የፓርቲው ሁለንተናዊ ተቆጣጣሪነት ስርዓቱን የሚቃወሙትን ከመሬታቸው ለማፈናቀል ሲያስችለው ገበሬውን በጥልቅ ያለመረጋጋት መንፈስ ውስጥ ይከተዋል፡፡ ይህም በተራዛሚ ችጋርን ይከስታል ይላሉ ቫዳል ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው፡፡ እንደ ቫዳል ሙግት ከዚህ የመሬት ፖሊሲ በተጨማሪ ለእርሻ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች በኢህአዴግ ተቆጣጣሪነት በሚመሩት የንግድ ድርጅቶች /parastatals/ የበላይነት መያዙ ሁለተኛው ችጋር አባባሽ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናታዊ ስራ ያቀረቡት ዮናስ ቀፀላ የተባሉ ፀሐፊ ለማሳያነት የአማራ ክልልን ያነሳሉ፡፡ ፀሐፊው “Post-1991 Agricultural policies with Reference to the Role of national Extension intervention program in addressing the problem of food security” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው በአማራ ክልል በብአዴን ባለቤትነት የተያዘው አምባሰል ትሬዲንግ እና በአማራ ክልል በብአዴን ባለቤትነት የተያዘው አምባሰል ትሬዲንግ እና ሌላው የገዢው ፓርቲ የንግድ ድርጅት ‹‹የእርሻ ግብይት አቅራቢ ኢንተርፕራይዝ /AISE/ የተባለው ተቋም ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት እና በክልሉ በማከፋፈል እያንዳንዳቸው 97% እና 99.3 % የገበያ ድርሻ መያዛቸውን ያወሳሉ፡፡ ዶ/ር ቫዳል በበኩላቸው ከእነዚህ ሁለት ሁነቶች በተጨማሪ ገዢው ፓርቲ ካሰፈነው አምባገነናዊ የፖለቲካ ስርዓት አንፃር የፀረ-ችግር ውል መፈረምን አስቸጋሪ ማድረጉ ምንም ያህል የውጪ ዕርዳታ ቢኖር ችጋርን ከሀገሪቷ ለማጥፋት እንዳይቻል ተጨማሪ ተግዳሮቶች ሆነዋል ሲሉ ለ16ኛው የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ ባቀረቡት ፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

# ወይ ሀገሬ

... ከገፅ 3 የዞረ

ወይ ሀገሬ!

ኢትዮጵያውያን ከፋሽስት ኢጣሊያ የሚሹት ምን ነበር? የቤት ግንባታ? የመንገድ ሥራ? የድልድይ ማቆም? የተማሪ ቤት? የኤሌክትሪክና የመታከሚያ ቤቶች ማቋቋም?... አልነበረም! የተጣሰው ድንበር ወደነበረበት እንዲመለስ፣ የወደቀው ባንዲራ እንዲነሳ፣ የፈረሰው መንግሥት እንዲቋቋም ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ከግምት ባይገቡ ከኢጣሊያ የተሻለ ‹‹ልማታዊ መንግሥት›› ከየት ሊገኝ? በአምስት አመት የገነባው 70 ዓመት አላግደረደረንም?

በሀገር ሥም፣ ሀገር ላይ ስለተሰራ ሀገርን ይወክላል ማለት እንዳልሆነ አንጡራው ኢትዮጵያዊ ያኔም ተረድቶታል፡፡ ይራበን፣ ይጥማን፣ እንታረዝ... ይሄ ችግራችን ሀገር ቅልቅል፣ ባንዲራ ቅይጥና ሉአላዊነት ድብልቅ ከሆነ እንታገሳለን፡፡ ሀገር የጠገቡት ዜጐቿ ብቻ ነች የሚል ድምዳሜ የለንም፡፡ የተራቡትም ነች፡፡ መጥገቢያ ብቻ ሳትሆን መራቢያና መጠሚያ መሆኗ አይጠፋንም፡፡ የድሎት ገነት ትሁን አይወጣንም፡፡ በሀገር መኩራት ጠግቦ ከመብላት፣ እረክቶ ከመጠጣት፣ አማርጦ ከመልበስና መጠለያ ካለማጣት ይመነጫል የሚል ድምዳሜ ቢኖረን ገና ድሮ፣ በአያቶቻችንና በቅድመ አያቶቻችን ጊዜ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ባለቀላቸው ነበር፡፡

ወይ ሀገሬ!

‹‹ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል›› በሀገር ጉዳይ አይሰራም፡፡ ብቻውን የበላ ብቻውን ለሀገር ሲሞት በታሪካችን አልታየም፡፡ የጨቆነው ዘምቶ የተጨቆነው አልቀረም፡፡ የገዛው ከልቡ ተዋግቶ የተገዛው ሲለግም አልተሰማም፡፡ የበደለውና የተበደለው፣ የተራበውና ያስራበው፣ የገደለውና የሞተው... የእርቅ ማዕዳቸው ሀገርን ያማከለ ነው፡፡ ታዲያ ምነው ዛሬ?

ደረታችንላይየሚንቀዋለሉግንባታዎች፣ ከልባችን ያልደረሱ አዳዲስ ተቋሞች፣ ቀልባችንን ያልሳቡ የልማት እቅዶች አሉ፡፡ መንገዶች፣ ፋብሪካዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ የዩኒቨርስቲ ማስፋፊያዎች፣ የኤሌክትሪክ ማመንጪያዎች፣... ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ውስጥ ድጋፍ የተነፈገው፣ እምነት ያልተጣለበት ሁለተኛው ልማታዊ መንግሥት መሆኑ ነው፡፡ ለምን? እንደፋሽስት ኢጣሊያ የድንበር፣ የባንዲራ፣ የነፃነት...ጥያቄ ስላለበት? በከፊል አዎ!

አንጡራው ኢትዮጵያዊ ዘንግቶ የማይዘነጋቸው፣ ድኖም የማይሽር ቁስለት ያተረፈባቸው የዚህ መንግሥት ድርጊቶች አሉ፡፡ በተለይ ኤርትራን በተመለከተ፡፡ ኢትዮጵያን ይዞ የማስደብደብ ተግባር ተፈጽሟል፡፡ ይሄ ተግባር ከባዕዱ ኢጣሊያ እኩል የሚያስቆጥር የጠላት ድርጊት ቢሆን አያንስም፡፡ የተሳሳተው ይስተካከል፣ የጠፋው ይታረም አይደለም፡፡ ያ-ሁለተኛ ነገር ነው፡፡ ተሳስተናል፣ አጥፍተናል ማንን ገደለ? ከሀገር ባሻገር የመንፈስ፣ የክብር፣ የህሊና፣ የሰው መሆን... ድንበር ተጥሷል፡፡ ያንን ቁጭት ይዞ መገንባት፣ ያንን ጥቃት አርግዞ ማልማት፣ ያንን መደፈር እያብሰለሰሉ ድህነት ማጥፋት... የከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ... ከንቱ ነው!

ወይ ሀገሬ!!

# አካኪ ዘራፍ ገዳይ በርግጡ፤ አሽሟጣጭ ታጥቆ በረጅም ሽንጡ::

### ከፉከራ ሥነ ቃል የተወሰደ



ከታዴዎስ ታንቱ

ኢትዮጵያ! በደም የተገነባች ሀገር! በደም የተከበረች ምድር! በደም የፈረሰች መሬት! የከበርቴዎች ገነት! የሕዝብ ሲዖል! የገዢዎች ንብረት! ኢትዮጵያ! የጀግኖች ውርስ! የፈሪዎች ርስት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! ተጠግቷል! ተጠግቷል! ተጠግቷል! ቀርቧል! ደርሷል! ማጆር ጉሎኒ አውግስቶ ይገደላል! ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል ሊያድነው አይችልም! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ይባርከዋል! ምሽጉ ተከብቧል! ማምለጫ አጥቷል! ቡም! ቡም! ቡም! ድም! ድም! ድም! ቦምብ! ቦምብ! ቦምብ! ጥይት! ጥይት! ጥይት! ጉሎኒ አውግስቶ ተገድሏል! ሌሎች ጣሊያኖችም ተደምስሰዋል! ምሽጉ ወድሟል! የጀግናው ዕቅድ ወደ ተግባር ተለውጧል! ቃል ድርጊት ሆኗል! ድርጊት ከቃል ፈልቋል! በእናት ሀገርና በሚስት የለም ዋዛ! ይህ የጀግናው አርበኛ የደጃዝማች ታደሰ ይማም ወንድይራድ ድምፅ ነው! ደብረ ታቦር! 1928 ዓ.ም.! ታሪክ ይናገራል:: የተርብ ልጅ ተርብ ነው! ቀደምት ጀግኖች የታሪክ ጌጦች!

ጀግናው ታደሰ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እየገፋ መምጣቱን እንደ ሰማ የጋይንት ጀግኖችን አስተባብሮ ወደ ትግራይ በመዝመት ወርቅ አምባ በተባለ ቦታ በጦርነት ውሎው ከፍተኛ ጀብዱ ፈፅሟል:: ታሪክ ሰርቷል:: ወደ ትውልድ መንደሩ እንደተመለሰ ደግሞ በጋይንት ውስጥ በስማዳ ወረዳ በከፍተኛ ደረጃ የተጠናከረ ምሽግ አበጅቶ እንደ ጎልያድ በፉከራ ሽብር ይነዛ የነበረውን ዕብሪተኛ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለመደምሰስ ወሰነ:: ዕቅድ ነድፎ የድርጊት ስልትም ቀይሷል:: ነገር ግን አቅም አልነበረውም:: እንቅስቃሴው ተገትቷል:: ምን ያድርግ? እልህ ናጠው:: ወኔ ገፋተረው:: በማን ሀገር ማን ይደራጃል? በማን መሬት ማን ይንሰራፋል? ጀግናው ታደሰ ጥረት ያደርግ ገባ:: ብዙ አልቆየም:: የሰው ኃይል አግኝቷል:: የጦር መሳሪያም ለመሰብሰብ ችሏል:: ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የውጊያ አቅም አሁንም ያነሰ እንደ ነበር ግን አንዘነጋ:: ጀግናው ታጥቆ ተነስቷል:: ስማዳ ቀውጢ ሆነች:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተፍጨረጨረ:: ተስፋ ግን አልነበረውም:: በዚህ ሒደት ጎራዲት በተባለው ስፍራ በተጣለው ድንገተኛ አደጋ ብዙ የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች እንዳልነበሩ ሆነዋል:: ተደምስሰዋል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ተዋጊዎች ታጭደዋል:: ድል የአርበኞች ሆኗል:: የኢትዮጵያ ልጅ የጀግና ዘር!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን ሽንፈቱን ተቀብሎ ለኢትዮጵያ ጀግኖች ተገቢውን ክብር ለመስጠት ዝግጁ አልነበረም:: ይልቁንም ለጥቃት በእንቅስቃሴ ላይ ተሰተዋለ:: ወዲያው ታወቀ:: ጀግናው ታደሰ አላቅማማም! በገዛ ሀገሩ ማንን ይፈራል? በገዛ መሬቱ እንዴት ባዕድ ይገዛዋል? የውጊያ ስልት ቀየሰ:: ተከታዮቹ ተስማሙ:: ቀን ተቆረጠ:: በመቅደም አቋም ፀኑ:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጥቁሬ ማርያም በተባለ ቦታ መሽጓል:: እንክበበው! እንክበበው! ተስማሙ! ቃል ተግባር ይሆናል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአርበኞችን ተነሳሽነት በማስመልከት ጥርጣሬ አልነበረውም:: በፍፁም አልጠረጠረም:: የራሱን ጥንካሬ ከራሱ ጋር እየለካ ተቀምጧል:: ምሽጉ ተከብቧል:: እጁን የሰጠ ከጀግኖች ሰይፍ ይድናል:: ያቅማማ ይቀጣል! ይህ የጀግኖች ድምፅ ነው! አርበኞች ተኩስ ከፈቱ:: የአፀፋ ድምፅ ተሰምቷል:: ጥቁሬ ማርያም ሰፈር ቀውጢ ሆነ:: ማን ያሸንፍ ይሆን? አርበኞች የበላይነትን ይዘዋል:: በእርግጠኝነት የበላይነትን ጨብጠዋል:: አሁን ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአፀፋ ተኩስ ተቋርጧል:: አርበኞች ከብበዋል:: ከውጭ የጦር መሳሪያም ሆነ የቀለብ ማግኛ አቅጣጫ ሁሉ ተዘግቷል:: አርበኞች ግን የጦር መሣሪያ በማግኘት ላይ እንደ ነበሩ ተመልክቷል:: ቀናት አለፉ:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተጨነቀ:: በውኃ ጥምና በራሃብ ሊያልቅ ሆነ:: ከሁለቱ ሞት አንዱን መምረጥ የግድ ሆነ:: ተኩስ ከፈተ:: የአርበኞች የአፀፋ እርምጃ ቀላል አልነበረም:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተደመሰሰ:: አርበኞች ድል አደረጉ:: ጀግናው ታደሰ ተደነቀ::

ጠላትና ሙጃ ሳይዘሩት ይበቅላል:: እንኳን ባንዳ ጌቶችም አልቻሉትም:: ታደሰ ይማም ወንድይራድ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ በተግባር ተመዝግቧል:: ክንዱን የቀመሰ ያውቀዋል:: ባንዳ ምን ሊያመጣ ይችላል? ባዶ ገረወይና ድምፁ ትልቅ ነው! ደጃዝማች እጅጉ አያሌው ይባላል:: የጎንደርን ህዝብ በሙሉ አሳምኖ ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተገዥ ሊያደርግ እንደሚችል አፉን ሞልቶ በአፉ ገልጿል:: በጌታዋ የተማመነች በግ ላቷን ውጭ እንደምታሳድር አበው ተናግረዋል:: በሊሬ የተገዛ ባንዳና በአሞሌ የተሸመተ ባርያ አፋቸው እንዳመጣው እንደሚናገሩ ተስተውሏል:: የአጼ ቴዎድሮስን ሀገር እንዳለ ባንዳ ለማድረግ እንዴት ይታሰባል? ይህ ምኞት ብቻ ሆኖ ይቀራል:: ጎንደር ለባዕድ አይገዛም:: ጃንአሞራ ለጠገበ ጥይት ለተራበ እንጀራ! ጀግናው አርበኛ ታደሰ ዝግጅቱን አጠናቅቋል:: ወዮለት ለደጃዝማች እጅጉ አያሌው! አርበኛው በቀጥታ ወደ ፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ አመራ:: ባንዳው እጅጉ አያሌው ይፎክራል:: ጦርነት ተከፈተ:: አርበኛው በረታ:: ሰውዬው ታደሰ መሆኑን አንርሳ:: አንበሳው አገሳ! ባንዳ በትንፋሹ ተገፍትሮ ወደቀ:: ብትንትኑ ወጣ:: ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለባንዳ የተሠጠው የጦር መሳሪያ ከአርበኞች እጅ ገባ:: ብዙ ባንዳ ተገደለ:: እጅጉ አያሌው ግን በታንኳ ገብቶ በጣና ሐይቅ በኩል አድርጎ አመለጠ:: ያ ሁሉ ፉከራ እንደ ጉም በነነ:: ጀግናንና ፈሪን ለመለየት ተቻለ:: ባንዳው ሲሮጥ ውሎ አደረ::

ቆራጡ አርበኛ ታደሰ ባንዳው እጅጉ አያሌው በማምለጡ በጣም ተናደደ:: እንዴት ያመልጣል? በየቦታው የፍለጋ ቡድን አሰማራ:: ጠየቀ:: ከየት ይምጣ? ሆኖም ፍለጋው ቀጥሏል:: ከቀናት ፍለጋ በኋላ ተፈላጊው እጅጉ አያሌው ወሎ ውስጥ መታየቱ ተሰማ! ጀግናው ታደሰ ግን ለተመልካች ናቅ ያደረገው ለመምሰል ሞከረ:: ሙያ በልብ ነው! መረጃው ከጥቂት አርበኞች ውጭ እንዳይወጣ ጥንቃቄ እንዲደረግ በጥንቃቄ ትዕዛዝ ወረደ:: የህይወት ጉዳይ ነው! በነፍስ ላይ ቀልድ አልነበረም:: ምስጢር አልባከነም:: ወደ ወሎ ዘመቻ ሊደረግ ታስቧል:: ስንቅ ተሰናድቷል:: በገበያ መታየትና ከብዙ ሰዎች ጋር መገናኘት ደግ አይደለም:: ጀግናው ታደሰ ከአርበኞች ጋር በስፋትና በጥልቀት ተወያይቷል:: ያለ ልዩነት በእያንዳንዱ ነጥብ ከስምምነት ላይ ተደርሷል:: አሁን ለጉዞ ተነስተዋል:: ጫካ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በገላጣ መንገድ የቀን ጉዞ አልተወደደም:: በጥንቃቄና በጥርጣሬ ቀጥለዋል:: ካህን ለመምሰል ጠምጥመዋል:: ቦምቦችን በስልቻ ይዘዋል:: በጋቢ ጠብመንጃ ደብቀዋል:: በነፍስ ወከፍ ዝናር ታጥቀዋል:: በዘመኑ ምልከታ ሽፍቶች እንዳይመስሉ ተጠንቅቀዋል:: ጉዞ ወደ ወሎ ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! መልካም መንገድ!

ቆፍጣናው አርበኛ ታደሰ ጀግኖችን አስከትሎ አሁን ከባንዳው ደጃዝማች እጅጉ አያሌው መንደር ደርሷል:: ጥብቅ ምስጢር! የባንዳው ደጃዝማች መኖሪያ ተለይቶ ታውቋል:: ቦታው ኩሪብ ተብሎ ይጠራል:: ባንዳው ምንም አልጠረጠረም:: ሀገር ሰላም መስሎት ይዝናናል:: በመፈርጠጡ አርበኞች የተዉት መስሎታል:: እቤቱ ውስጥ መኖሩ ተረጋግጧል:: ከቤቱ ባጭር ርቀት ወጣሪ አርበኞች ቦታቸውን ይዘዋል:: አሁን የባንዳው ቤት ተከብቧል:: አርበኞች ተኩስ ከፍተዋል:: ይታረዳል! ለምን? በጀግኖቹ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የሕይወት መስዋዕትነት ተጠብቃ የኖረችውን ኢትዮጵያን እናታችንን ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ገፀ በረከት አድርጎ ለማቅረብ የበኩሉን ብዙ ጥሯል:: በማወናበድ የጎንደርን ህዝብ ለማሳመን ሞክሯል:: ከእሱ ጋር በተደረገው ጦርነት ጀግና አርበኞች ተሰውተዋል:: ወግና ማዕረግ ያየባትን እናቱን ኢትዮጵያን ክዷል:: ጥቁር ጣሊያን ሆኗል!! የጦር ሜዳ ፍርድ ተሰጥቷል:: ይታረዳል!

ጊዜ ማጥፋት ደግ አይደለም! አንድ! ሁለት! ሶስት! ከአርበኞች አንዱ ባንዳውን ደጃዝማች ገፍትሮ ጣለው:: ባንዳው ወደ ጎን ወደቀ:: አርበኛው ጠጋ በማለት በጆርባው አስተካክሎ አስተኛው:: ጀግናው ታደሰ ሳንጃውን መዝዞ አወጣው:: ዓይኖች ይጉረጠረጣሉ:: ከመፎከር ግን ታቅቧል:: ከተኩሱ በኋላ ምንም ድምፅ እንዳይሰማ ጥንቃቄ ተወስዷል:: ባንዳው ደግሞ ዓይኖቹ ይቁለጨለጫሉ:: ጀግናው ታደሰ ወደ ባንዳው ተጠግቷል:: ባንዳው በጸታ መለያው አካባቢ በተነፋነፍ ሱሪው ላይ ብዙ እርጥበት ይስተዋላል:: ጀግናው ታደሰ አሁን ጎንበስ ብሏል:: በጣም መጥፎ ሽታ መጥቷል:: ከባንዳው ደጃዝማች መቀመጫ ፈልቋል:: ጀግናው ታደሰ ሽታውን ለመከላከል የላይኛውን ከንፈሩን በከንፈሩ ወደ አፍንጫው እየገፋ የባንዳውን ማንቁርት ይዟል:: አለቀ! ደቀቀ! በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን! ጀግናው አርበኛ ታደሰ ይማም ወንድይራድ ባንዳውን ደጃዝማች እጅጉ አያሌውን እንደ ፋሲካ በግ አጋድሞ አረደው:: በጊዜአዊ ጥቅም ዘላለማዊ ክብሩን የሸጠው ምሱን አግኝቷል:: ለባንዳው ደጃዝማች እጅጉ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የተሰጠውን መሣሪያ ሁሉ አርበኞች ከእጃቸው አስገብተዋል:: ማርከዋል:: ጉሮ ወሸባ!

ጀግናው አርበኛ ታደሰ በአርበኞች ላይ ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው የኢትዮጵያ ጠላት በእጁ ስለወደቀለት ተንበርክኮ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቧል:: አሁንም ግን ፍልሚያ ይጠብቀዋል:: ሳይንት በተባለ ቦታ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መሽጓል:: ምንም ዕረፍት አልነበረም:: ስንቅ ግን አልቋል:: ትንሽ ባሶ ቀርቷል:: ከድል በኋላ ለፍልሚያ ተንቀሳቅሰዋል:: ጀግኖቹ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች አሁን ጅረት ካለበት ደርሰዋል:: ዛፎች የበዙበት ነበር:: የተወሰኑ አርበኞች አካባቢውን እንዲወጥሩ ተመደቡ:: የተቀሩት በሶ ለመበጥበጥ ወደ ጅረቱ ወረዱ:: ሶስት ዋንጫዎችን ብቻ ይዘዋል:: ተራ በተራ እየበጠበጡ ጠጥተዋል:: የበሶና የጭብጦ ስልቻዎች ባዶ ሆነዋል:: በድል የሰከሩ አርበኞች ወኔ እየገፋተራቸው መንገዳቸውን ቀጥለዋል:: ሳይንት ለመድረስ አሁን አንድ ምዕራፍ መንገድ ቀርቷል:: አካላቸው በደስታ ዝሏል:: በተስፋ ደክመዋል:: በአንድ ጠገራ ብር ሁለት በጎችን ገዝተዋል:: በሊሬ የሚገበያዩት በከተሞች አካባቢ ስለነበር ችግር አልገጠማቸውም:: ሥራ ተከፋፍለዋል:: ወጣሪዎች የአርበኞችን ደህንነት ይጠብቃሉ::ምደባው ከረጅም ርቀት በማየት ችሎታ መሆኑን ልብ እንበል:: የማብሰያ መገልገያ ዕቃዎችን ይዘዋል:: እንጀራና በርበሬ ለማኞች በጥንቃቄ ተሰማርተዋል:: አራጆች ሥራቸውን አጠናቅቀዋል:: ሌሊት እሳት እንዲነድድ አልተፈለገም:: በጊዜ ተመግበው ተኙ::

ዶሮ ሲጮኽ ተንቀሳቅሰዋል:: ጎበዝ መንገድ መሪ ይዘዋል:: ጎሕ ሲቀድድ ሳይንት ላይ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ ተከብቧል:: የጀግናው ታደሰ የውጊያ ጥበብ ይደነቃል:: ባጭር ጊዜ ወራሪዎች ሙትና ቁስለኛ ሆነዋል:: በርካታ የጦር መሳሪያና ቀለብ በምርኮ ተገኝቷል::

ኩራት ኩራት አይልሽም ወይ?

ታደሰ ይማም ወንድይራድ ያንቺ አይደለም ወይ?

ጀግናው ታደሰና ተከታዮቹ አሁን ዋድላ ደላንታ ገብተዋል:: መደበኛ ጦርነት አቁመዋል:: በሽብር ተሰማርተዋል:: በባንዳነት የተጠረጠሩ ሰዎችን እየተከታተሉ ማሸበርን ቀዳሚ ተግባራቸው አድርገዋል:: የግድያ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል:: በተናጠል ነጥለው ገድለዋል:: ይህ በእንዲህ እንዳለ 1933 ዓ.ም. ደረሰ:: ጀግናው አርበኛ ታደሰ ይማም ወንድይራድ በወሎ ውስጥ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን የአካባቢው አዛዥ ማረከ:: ጀግናው የጀግና ዘር፤ ጀግናው የጀግና ልጅ የባንዳነት ጥላሸት ሳይነካው በጀግንነት ፀንቶ የኢትዮጵያን ድል አድራጊነት ተመለከተ:: በ53 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል:: የት እንደ ተቀበረ መረጃ አጥተናል::

ጀግናው አርበኛ ታደሰ ይማም ወንድይራድ በጎንደር ክፍለ ሀገር በስማዳ ውስጥ በ1890 ዓ.ም. ተወለደ:: በልጅነቱ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተከታትሏል:: መሣሪያ መፍታትና መግጠም አጥንቷል:: በወረዳ ገዥነት አገልግሏል:: በሊጋባነትም መስራቱ ታውቋል::

አካኪ ዘራፍ ገዳይ በእርግጡ፤

አሽማጣጭ ታጥቆ በረጅም ሽንጡ::

# የመጅሊስ አመራሮች በቅርቡ

... ከገፅ 1 የዞረ

ህዝብ ሙስሊሙ በመረጣቸው ኮሚቴዎች መሆን አለበት ብለው ቢጠይቁም ተቀባይነት ሳያገኙ እንደቀሩ ተናግረዋል::

ከትላንት በስቲያ ግንቦት 1 ቀን 2004 ዓ.ም. የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት እና የአዲስ አበባ ፍትህና ፀጥታ ቢሮ በማዘጋጃ ቤት በጠሩት ስብሰባ ላይ በካርድ የተጠሩ የመጅሊስ ደጋፊዎች ብቻ የተጋበዙ ሲሆን ባለፉት ስምንት ወራት የተሰጡ ስልጠናዎችን መገምገማቸውንና በየመስጂዱ በዓርብ ፀሎት ላይ የሚደረጉ ‹‹ሁከቶችን›› እንዲያስቀሙና ሰዎቹንም አሳልፈው እንዲሰጡ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ሰይድ ግዛው እና የአዲስ አበባ ፍትህና ፀጥታ ቢሮ ኃለፊ አቶ ፀጋዬ ኃ/ማርያም እንዲሁም ከአዲስ አበባ ፖሊስ የተወከሉ አንድ ኮማንደር ጠይቀዋል ሲሉ በአዳራሹ የነበሩ ተሳታፊ ለፍትህ ገልፀዋል::

በዕለቱም በርካታ ሙስሊሞች በማዘጋጃ ቤት ስብሰባ ላይ አትገቡም ተብለው ውጪ የተሰበሰቡ ሲሆን ይህን ትዕይንት በሞባይል ስልክ ሲቀርፁ ነበር የተባሉ 6 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው ትላንት ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ፖሊስ ተጨማሪ የምርምራ ጊዜ ጠይቆባቸው ለሰኞ መቀጠራቸውን ለማወቅ ተችሏል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለሕዝበ ሙስሊሙ ጥያቄዎች መፍትሄ ለማፈላለግ የተቋቋመው ኮሚቴ ‹‹ሃይማኖት›› በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱ ሕገወጥ እንደሆነ ሁሉ፣ መንግስትም በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ስልጣን ስለሌለው ባለስልጣናቱንና መዋቅሩን ይቆጣጠር፣ በመላ ሀገሪቱ ያለው ህዝባዊ ጥያቄ ተመሳሳይ በመሆኑ መንግስት ካነሳነው ጥያቄ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለእስር የተዳረጉ እንዲፈቱ፣ ማስፈራራቶች እና የኃይል እርምጃዎች እንዲቆሙ ያድርግ ሲል በጋዜጣዊ መግለጫው አስታውቋል::

‹‹ሕገ መንግስቱን የሚያከብርና የሚያስከብር የራሱንም መተዳደሪያ ደንብ የሚያከብር የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ቢዋቀር ኖሮ እኛም ህዝባዊ ጥያቄ በመያዝ የመንግስት ቢሮዎችን ማንኳኳት ባላስፈለገን ነበር›› ያለው ኮሚቴው፣ ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ያልተመረጠ አመራርም ሲጥሰው የቆየውን መተዳደሪያ ደንቡን መርምሮ ራሱን ከኃላፊነት ለማግለል በመወሰኑ ህዝብ ሙስሊሙ ያነሳው ጥያቄ ምላሽ የማግኘት ሂደት ላይ መሆኑን እንገነዘባለን:: ነገር ግን የስልጣን ሽግግሩ ህዝባዊነት በሌለውና የመጅሊሱ መዋቅር አካልና አጋር በሆነውና መዋቅራዊ አቅም ለሌለው የኡላማዎች ምክር ቤት መሰጠቱ አግባብ እንዳልሆነም ይሰማናል ሲል የገለፀው ኮሚቴው ህዝበ ሙስሊሙ በቅርቡ በሚደረገው የመጅሊስ ምርጫ ይሆነኛል የሚላቸውን ተወካዮች ለመምረጥ ብርቱ ዝግጅት ከማድረግ በተጨማሪ ከኮሚቴው ጎን በመሆን አፈፃፀሙ ነፃ፣ ሰላማዊ፣ ግልፅና ፍትሃዊ መሆኑን በንቃት እንዲከታተል ጥሪ እናደርጋለን›› ሲል አስታውቋል::

ዕንቊ የቤተሰብዎ መፅሔት

ነገ በገበያ ላይ ትውላለች

“ነፃነቴን ከመሠለ መብቴ ውጪ አንድም ሀብት የለኝም”

ኢንተርናሽናል የስፖርት ሰው ፍቅሩ ኪዳኔ

“የፊልም ሽልማቶች ከግለሰብ ባለቤትነት መውጣት አለባቸው”

የፊልም ባለሙያ ያሬድ ሹመቴ

ጋሞሌ አምባ መንደር

ጌጡ ተመስገን

አስደንጋጭ አሀዞቹ እና የጠ/ሚኒስትሩ ተግሳፅ ምን እና ምን?

በገዛኸኝ ፀ.

ቪያግራ፣ ያልተፈለገ እርግዝና እና የአባላዘር በሽታዎች “ዝምድና”



## 21 የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንደታሰሩ ይገኛሉ

### አንድ ተማሪ በጥይት ቆስሏል፣ በከባድ ሁኔታ የተደበደቡ ተማሪዎች በርካታ ናቸው

‹‹በርካታ ፖሊሶች በዩኒቨርስቲው ግቢና ውጪ በመኖራቸው በነፃነት መንቀሳቀስ አልቻልንም››
/ተማሪዎች/

ከእሁድ ሚያዚያ 28/2004 ዓ.ም. አመሻሽ ጀምሮ በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ከምግብ ጥራት ጋር በተያያዘ በተነሳው ተቃውሞና ፖሊስ በወሰደው የኃይል እርምጃ ሳቢያ ተማሪዎች እስከ አሁን ድረስ በመደበኛ የትምህርት ገበታቸው ላይ አለመሆናቸውን የፍትህ ምንጮች አረጋግጠዋል፡ ፡

እሁድ ዕለት በተነሳው ተቃውሞ አብዛኛው ተማሪ ቁጣውን የዩኒቨርስቲውን መስታወቶች በመሰባበር እንደገለፀና ምሽት ላይ በድንገት ወደ ግቢ የገቡት ታጣቂዎች በተማሪዎቹ ላይ ከመጠን ያለፈ ኃይል በመጠቀም ጉዳት እንዳደረሱ የአይን እማኞች ተናግረዋል።

ተማሪዎቹ እሁድ እና ሰኞ የተፈጠረው ችግር የአንድ ቀን የእራት ችግር ሳይሆን የታወቀ የፍትህ፣ እኩልነትና ነፃነት ማጣት ብሶትና በደል ውጤት መሆኑን ጠቅሰው ሃሳባቸውን ያለፍርሃት ሲገልፁ መሰማታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያስረዳል።

የተቃውሞው መነሻ ምክንያትም አንድ ተማሪ የምግብ ቤት አስተናጋጇን ‹‹ዛሬም ሽሮ ነው?›› ሲላት፤ አስተናጋጇ መልሳ ‹‹የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪ እንኳን ሽሮ እንጨት ቢሰጡት ይበላል›› በማለቷ የቆየው የተማሪዎች ችግር መፈንዳቱን የፍትሕ ምንጮች ይገልፃሉ።

ተማሪዎቹ ‹‹ዩኒቨርስቲው እየተመራ ያለው በዩኒቨርስቲው አመራሮች አይደለም። በአራቱ የኢህአዴግ የፖለቲካ ድርጅቶች አስተባባሪ ነው። ጽ/ቤታቸውም ከግቢ ይውጣ... በመማር ማስተማሩ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። የድርጅቱ መሪዎች መታወቂያ ይቀሙናል፣ ያስፈራሩናል። በተለይም ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅቶች ውጭ ያለን ተማሪዎች ችግራችን ተነግሮ አያልቅም›› የሚል ቅሬታም አላቸው።

የዩንቨርስቲው ተማሪዎች ችግራችን ቢፈታልን ብለው ለፓርቲ አስተባባሪዎች ጥያቄ ቢያቀርቡም ‹‹ሞክሩትና እንተያይ›› የሚል መልስ እንደተሰጣቸው በመጥቀስ ዩኒቨርስቲው የትምህርት መስጫ ተቋም ሳይሆን የፖለቲካ (የኢህአዴግ) ማዕከል መሆኑንና ተማሪው ሀሳቡን በነፃነት እንዳይገልፅ መደረጉን ምንጮቻችን ያስረዳሉ።

የተማሪዎቹ መሰረታዊ ጥያቄዎች ‹‹የፖለቲካ ድርጅቱ ከግቢ ይውጣ›› የሚል መሆኑንም ምንጮቻችን ጨምረው ገልፀዋል።

በተፈጠረው ረብሻም ከ60 ያላነሱ ተማሪዎች ታስረው እንደነበረ፣ አሁንም 21 የሚሆኑት ታስረው እንደሚገኙ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች መደብደባቸው፣ አይናቸው በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዱ መኖራቸው፣ እጅና እግራቸው የተሰበሩ፣ በመኪና የተገጩና በተፈጠረው ሁኔታ በስነ ልቦና የተረበሹ መኖራቸው ታውቋል።

‹‹ከቁርጭምጭሚቴ በላይ በጥይት ከተመታው በኋላ በደብረማርቆስ ሆስፒታል ሕክምና ተደርጐልኝ ወጣሁ›› የሚለው የ2ኛ አመት የማናጅመንት ተማሪ ኢብራሂም መሃመድ፣ ዛሬ በድጋሚ ሆስፒታል ቀጠሮ እንዳለው ለፍትሕ በስልክ የተናገረው በአቅራቢያው የሚገኝ ዘመድ ቤት እንደተጠለለ ነው። በፖሊስ ዱላና ሽመል ጀርባውና ደረቱ ላይ ከፍተኛ ድብደባ ደርሶበት ማክሰኞ ዕለት ከሆስፒታል መውጣቱን ለፍትሕ የተናገረው ደግሞ የ1ኛ ዓመት የሲቪል ኢንጂነሪንግ ተማሪ ገብረኪዳን ብርሃኔ ‹‹ስቃይ እየተሰማኝ ነው›› ብሏል።

ዩኒቨርስቲውም ‹‹በእስር ላይ ያሉ ልጆች በቂ ቅጣት እስኪሰጣቸው ድረስ እናንተ ተማሩ›› የሚል ማስታወቂያ አውጥቶ እንደነበረ የሚገልፀው ተማሪ ገብረኪዳን ተማሪዎች ‹‹ጓደኞቻችን ታስረው፣ ሆስፒታል ተኝተው እንዴት እንማራለን? አንማርም!›› ብለው ማተሚያ ቤት እስከገባንበት ትላንት ምሽት ድርስ ትምህርት አለመጀመራቸውን ለፍትሕ ገልጿል።

ከዚሁ ጋ ተያይዞ ባገኘነው መረጃ መሰረት ተማሪዎች በአስተማሪዎቻቸውና በተማሪዎች ተወካይ አማካኝነት በካፍቴሪያ ለመመመገብ፣ በዶርሚተሪ ለመጠቀም፣ በትምህርት ገበታ ላይ ለመገኘትና በግቢው ውስጥ ለመንቀሳቀስ ‹‹ጊዜያዊ ወረቀት›› የመውሰድ ግዴታ ከትላንት ጀምሮ እንደተጣለባቸው ነው። ይሄንን ያደረጉ ተማሪዎች መኖራቸውንም ፍትህ ለማወቅ ችላለች። ነገር ግን፣ የታሰሩ ተማሪዎች ከእስር ተፈትተውና በድብደባ ጉዳት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች አገግመው ወደ ትምህርት ገበታቸው በሰላም ካልተመለሱ በስተቀር ትምህርት ለመጀመር ብዙሃኑ ተማሪ ዝግጁ አለመሆኑን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ተማሪዎች ለፍትህ ተናግረዋል። በተጨማሪም የታጠቁ በርካታ ፖሊሶች በሁለት በኤፍ ኤስ አር መኪና ተጭነው በመምጣት በዩኒቨርስቲው ዙሪያና ውስጥ ፈስሰው እንደሚገኙ የተናገሩት ምንጮች ግቢው የትምህርት ተቋም እንጂ ወታደራዊ ካምፕ አለመሆኑን በመጥቀስ ተማሪዎች ‹‹ፖሊሶች ከግቢያችን ይውጡ›› እያሉ ይገኛሉ ብለዋል። ተማሪዎቹም በፍርሃትና በስጋት ውስጥ እንደሚገኙም ለፍትህ አልሸሸጉም፡ ፡ በፍትህ በኩልም ስለጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ለማነጋገር ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡ ፡

## መትረየስና ጠመንጃ የሰረቁ በእስራት ተቀጡ

### የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ ባልደረቦች ይገኙበታል

አንድ ብሬን መትረየስ እና አንድ ባለሰደፍ ጠመንጃን የሰረቁ ስምንት ግለሰቦች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 15 ወንጀል ችሎት ከትናንት በስቲያ ስምንት አመት በሚደርስ እስርና በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ አስተላለፈ።

1ኛተከሳሽ መቶ አለቃ ደረጀ ተስፋዬና 2ኛ ተከሳሽ መቶ አለቃ ዘመድኩን ገ/ዮሐንስ በአገር መከላከያ ሚኒስቴር በሎጀስቲክ ዋና መምሪያ የኦርድናንስ መምሪያ የናዝሬት ጦር መሳሪያ ዲፖ የግምጃ ቤት ኃላፊዎች መሆናቸውን የክሳቸው ዝርዝር ያስረዳል።

3ኛ ተከሳሽም ሃምሳ አለቃ ዲጋሞ ደፈ በጥበቃ ስራ ላይ ተመድቦ የሚሰራ የሰራዊቱ አባል ሲሆን ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሳቸው ለማግኘትና ለ4ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ለማስገኘት አስበው ነበር።

1ኛ ተከሳሽ ከ2ኛና 3ኛ ተከሳሽ ጋር በመመሳጠር በኃላፊነት ከሚቆጣጠረውና በአደራ ከተረከበው የጦር መሳሪያ ግምጃ ቤት ውስጥ የመለያ ቁጥር ኤ-ቢ 049 የሆነ አንድ ብሬን መትረየስ እና የመለያ ቁጥሩ 782288 የሆነ አንድ ባለሰደፍ ክላሽ ጠመንጃዎችን ፈታትቶ በማዳበሪያ ይጠቀልላል። ከዚያም የ3ኛ ተከሳሽ የጥበቃ ሽፍት ጊዜ በሆነበት ሐምሌ 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ከምሽቱ 3፡00-4፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ አውጥቶ ጠመንጃዎቹን ለሚያሻሽጠው 4ኛ ተከሳሽ እንዲሰጥ ለ3ኛ ተከሳሽ ይሰጣል።

3ኛ ተከሳሽም ጠመንጃዎችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተረክቦ የጦር መሳሪያ ዲፓ ከሚገኝበትና ከሚጠብቀው ካምፕ አጥር ውጪ አውጥቶ በማስቀመጥ 4ኛ ተከሳሽ ጠመንጃዎቹን ከደበቁበት ቦታ አንስቶ እንዲወስድ አድርጐ ነበር። 2ኛ ተከሳሽም ቀደም ሲል በሰው የተዋወቀውን 4ኛ ተከሳሽ የሚሸጥ የጦር መሳሪያ እንዲያፈላልግለት በነገረው መሰረት ከላይ የተጠቀሱትን ጠመንጃዎች 1ኛ ተከሳሽ እንዲሸጥለት በማሳመን መሳሪያዎቹ በ3ኛ ተከሳሽ አማካኝነት እንዲመጡ ያስደርጋል።

ከዚያም 4ኛ ተከሳሽን በስልክ በመጥራት ጠመንጃዎቹን እንዲወስድ በማስደረጉ 4ኛ ተከሳሽም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች መሳሪያዎቹ ከተደበቁበት አንስቶ እንዲወስድ በስልክ ደውለው በነገሩት መሰረት ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ጠመንጃዎቹ ከተደበቁበት ቦታ አንስቶ በመውሰድ ናዝሬት ከተማ ቀበሌ 09 ክልል ውስጥ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ያስቀምጣል።

በነጋታው ሐምሌ 23/2002 ዓ.ም. በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን ለ7ኛ ተከሳሽ ለማስረከብ እና ጠመንጃዎቹ የተሸጡበትን ዋጋ ብር 18000 ብር በመቀበል ከዚሁ ብር 16100 ብር ለ1ኛ ተከሳሽ፣ ለ2ኛ ተከሳሽ ደግሞ 2000 ብር መስጠቱን የሚያስረዳው ክሱ ነው።

1ኛ ተከሳሽ ሐምሌ 25/2002 ዓ.ም. ካምፕ ውስጥ 3ኛ ተከሳሽን በመጥራት ‹‹ድርሻህ ነው›› ብሎ 2000 ብር ሰጥቶታል። እንዲሁም 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾችም 7ኛ ተከሳሽ የጦር መሳሪያዎቹን ጭኖ ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ የሚወስድ ተሽከርካሪ ይዘው እንዲመጡ በነገራቸው መሰረት ሐምሌ 23/2002 ዓ.ም. አንድ የቤት መኪና ከ8ኛ ተከሳሽ ይኮናተራሉ።

ቀጥሎም ተከሳሾች ናዝሬት በመድረስ የጦር መሳሪያውን ከ4ኛ ተከሳሽ ቤት አውጥተውና በልብስ ሻንጣ ጭነው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ቃሊቲ ፍተሻ ጣቢያ ላይ ለመያዝ ችለዋል።

በሁለተኛ ክስ የተከሰሰው 8ኛ ተከሳሽ ብቻ ነበር። ተከሳሽም ከላይ የተጠቀሱት የጦር መሳሪያዎች በሙስና ወንጀል ድርጊት የተገኙ ለመሆናቸው በቂ ምክንያት እያለው እንዳላወቀ በመምሰል በቃሊቲ ፍተሻ ጣቢያ ላይ እጅ ከፍንጅ እስኪያዝ ድረስ አገባብ ላለው ባለስልጣን ሳያሳውቅ በመቅረቱ ክሱ ሊቀርብበት ችሏል።

ፍርድ ቤቱም 1ኛ፣ 2ኛ፣5ኛና 6ኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በስምንት አመት ፅኑ እስራትና በ5000 ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ ውሳኔ ሲያስተላልፍ በሌሎቹም ላይ እንደወንጀላቸው መጠን የፍርድ ውሳኔ ሰጥቷቸዋል።

## በመድረክ ከፍተኛ አመራር ላይ አራት የመከላከያ ምስክሮች ትናንት ተደመጡ

### . እነ እስክንድር ነጋ ዛሬ ለፍርድ ይቀርባሉ

በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በማረሚያ ቤት የሚገኙትና የፍርድ ሂደታቸውን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በመከታተል ላይ ከሚገኙት መካከል የመድረክ ከፍተኛ አመራር በሆኑት አቶ በቀለ ገርባ ላይ አራት የመከላከያ ምስክሮች በትናንትናው እለት በችሎት ቀርበው ምስክርነታቸውን ሰጡ።

ምስክሮችም አቶ አንዱዓለም አራጌ፣ አቶ አልባና ሌሊሳ፣ አቶ ጉቱ ሙሊሳ እና ወ/ሪት በቀለች ደገፉ ሲሆኑ እነዚህም ጠቅለል ባለ ሁኔታ ምስክርነታቸውን የሰጡት የአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተሳሳተ ማስረጃን ተንተርሰው መመስከራቸውን በማስረዳት ነው። አቶ ኢማና ኢርኮ በሚል የአቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ የቀረበው ግለሰብ ትክክለኛ ስሙ ሽፈራው ኤቢሳ እንደሚባልና ነዋሪነቱም አምቦ እንጂ ነቀምት አለመሆኑን ከተከላካይ ምስክሮቹ መካከል ለፍ/ቤቱ ማስረዳታቸውን ያገኘነው ማስረጃ ያስረዳል። አቶ አንዱዓለምም ኢዮስያስ ስለሚባል ልጅ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ፍ/ቤቱም ቀጣይ የተከሳሽ ተከላካይ ምስክሮችን ቃል ለማድመጥ ለግንቦት 17/2004 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

በተያያዘ ዜናም እነ እስክንድር ነጋ ዛሬ በዚሁ በችሎቱ ለፍርድ ይቀርባሉ። ፍ/ቤቱ ሚያዚያ 3 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተከሳሾችን የመከላከያ ሁለት የኦዲዮ ቪዲዮ-ማስረጃዎችን አዳምጦ ማጠናቀቁ የሚታወስ ሲሆን በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም ተከሳሾች ያቀረቧቸውን የመከላከያ ማስረጃዎች መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ለዛሬ ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር። በመሆኑም በዛሬው ዕለት ፍ/ቤቱ በተከሳሾች ላይ ጥፋተኛ መሆን አለመሆን ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል።

## ‹‹ከመቃብር ተመልሶ የመጣውን የሳንሱር መቀስ እንቃወማለን፤ ወደ መቃብሩ እንዲመለስ እንታገለዋለን››

### አንድነት ፓርቲ

አንድነት ለለፍትሕና ለዴሞክራሲ (አንድነት) ፓርቲ ከሁለት ሳምንት በፊት ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ያወጣውን ‹‹የህትመት ስራ ስታንዳርድ ውል››ን አጥብቆ እንደሚቃወም ትናንት ባወጣው መግለጫ አስታወቀ።

ለጥቂት ነፃ ጋዜጦች ማፈኛ ሲባል ከተዘጋጁት የፕሬስ ሕግ፣ የፀረ ሽብርተኝነት ሕግና እንደ አዲስ ዘመን አይነት ከመንግስት ሚዲያዎች ላይ ከሚሰነዘሩ ማስፈራሪያዎች በተጨማሪም በማተሚያ ቤት በኩል የሳንሱር ሕግ በማበጀት ለማጥፋት የተያዘው መንገድ አጥፊና ለሀገርም፣ ለሕዝብም፤ ለመንግስትም የሚጠቅም አለመሆኑን መግለጫው ያስረዳል።

የመንግስት ተቋም የሆነው አታሚ ድርጅቱ ‹‹እንፈራረም›› በማለት ያወጣውን የሳንሱር ሕግ እንቃወማለን፣ መቃወም ብቻ ሳይሆን እንታገለዋለን›› ያለው አንድነት የሚመለከተው ህገ-መንግስት አስከባሪ የሆነው የመንግስት አካል ድርጊቱ እንዲቆም ማድረግ ይገባዋል ብሏል። እንዲሁም አፈሩን አራግፎ ከመቃብር የተነሳውን የሳንሱር መቀስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመቃወም የሞት አፋፍ ላይ ያለውን ፕሬስ እንዲታደገው የሚል ጥሪ በማስተላለፍ ‹‹ከማተሚያ ቤት ጀርባ ያለው ድብቅ እጅም እንዲሰበሰብ እንጠይቃለን›› ሲል ፓርቲው ገልጿል።

## አቡነ ጳውሎስ የሲኖዶስ ውሳኔን በመጣስ የልማት ኮሚሽኑን ሊቀጳጳስ አቡነ ሳሙኤልን ከቼክ ፈራሚነት ሰረዙ

### . ሲኖዶሱ በመነጋገሪያ አጀንዳዎች ላይ እየተወያየ ነው

ፓትርያሪክ አቡነ ጳውሎስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀጳጳስ የኾኑት አቡነ ሳሙኤል በኮሚሽኑ ስም በተከፈቱት የተንቀሳቃሽና ቁጠባ ሒሳቦች ላይ ፊርማቸው እንዲሰረዝ ለአምስት ባንኮች የጻፉት ደብዳቤ በፓትርያሪኩና በሊቀጳጳሱ መካከል የተዳፈነውን አለመግባባት ዳግመኛ እንደቀሰቀሰው ምንጮቻችን አረጋግጠዋል። አቡነ ጳውሎስ የፊርማ ስረዛውን ትእዛዝ የሰጡት በለጋሾች፣ በመንግሥት አካላት እና በኮሚሽኑ የጋራ ስምምነት ተፈርሞ በመጣው ገንዘብ ላይ ለበርካታ ጊዜ የሚያቀርቡትን አግባብ ያልኾነ ጥያቄ ሊቀጳጳሱ አቡነ ሳሙኤል በተደጋጋሚ በመቃወማቸውና በማገዳቸው መኾኑ ተገልጧል።

ፓትርያሪኩ በአቡነ ሳሙኤል ምትክ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቡነ ፊልጶስ ከኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጋራ በጣምራ ፊርማ ቼኮቹን እንዲያንቀሳቅሱ ለኮሚሽኑ ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት እንዳላገኘ የኮሚሽኑ ምንጮች ለፍትሕ ጋዜጣ ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ አቡነ ፊልጶስ የፓትርያሪኩ ጥያቄ ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተወስኖ በሥራ ላይ በዋለው መመሪያ አንቀጽ 17 ቁጥር 2፡- ‹‹በኮሚሽኑ ስም የተከፈቱ የባንክ ሒሳቦች ሁሉ በኮሚሽኑ ሊቀጳጳስ፣ በኮሚሽነሩና በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከሦስቱ በሚገኙት በሁሉ ጣምራ ፊርማ ይንቀሳቀሳሉ›› የሚለውን እንደሚፃረር በመጥቀስ በኮሚሽኑ በተከፈቱ ተንቀሳቃሽም ኾነ የቁጠባ ሒሳቦች ላይ እንደማይፈርሙ ሚያዝያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም ለኮሚሽኑ በጻፉት ደብዳቤ አስታውቀዋል።

የአቡነ ፊልጶስ ተቃውሞ አላገዳቸውም የተባሉት አቡነ ጳውሎስ በቁጥር ል/ጽ/439/301/04 በቀን 29/8/2004 ዓ.ም በቀጥታ ለአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አራት ቅርንጫፎች፣ ለወጋገን ባንክ እና ለአቢሲኒያ ባንክ በጻፏቸው ደብዳቤዎች ‹‹ብፁዕ አባ ፊልጶስ ሌላ ጉዳይ ስላጋጠማቸው አልተመቻቸውም›› በሚል የኮሚሽኑ የፋይናንስ መምሪያ ሓላፊ አቶ ከበደ በየነ ተተክተው ከኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጋራ ሒሳቦቹን በጣምራ ፊርማ እንዲያንቀሳቅሱ ባንኮቹ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው መጠየቃቸው ተመልክቷል።

ፓትርያሪኩ ጥያቄያቸው ተፈጻሚ እንዲኾን ትእዛዝ የሚያስተላልፉት በኮሚሽነሩ ኮሚሽነር ዶ/ር አግደው ረዴ በኩል ሲኾን የኮሚሽኑ ሊቀጳጳስ አቡነ ሳሙኤል በበኩላቸው የኮሚሽኑ ሥራ ሕግንና ደንብን ተከትሎ እንዲከናወን በማሳሰብ ኮሚሽነሩ ዶ/ር አግደው ረዴ ‹‹ለግለሰባዊ ፍላጎትና ሐሳብ ቅድሚያ ከመስጠትና ተባባሪ ከመኾን እንዲቆጠቡ›› መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም እና ሚያዝያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በቃል እና በጽሑፍ ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል።

## የስካይ ባስ ሲስተም አ.ማ. ለፍርድ እንዲቀርብ የሟች ቤተሰቦች ጠየቁ

ከአዲስ አበባ ወደ ጐንደር ሲጓዝ ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም. ረፋዱ ላይ አባይ በርሃ ውስጥ ተገልብጦ በቃጠሎ ከ42 የማያንሱ መንገደኞች ህይወታቸው ያለፉባቸው ቤተሰቦች፣ ቀላልና ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በህይወት የተረፉ ተጎጂዎች የስካይ ባስ ሲስተም አ.ማ. በፈፀመው አስከፊ ድርጊት መንግስት ለፍርድ እንዲያቀርበው ትላንትና ባካሄዱት የፓናል ውይይት ላይ ጠየቁ።

የሟች ቤተሰቦችና ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች የትራንስፖርት ድርጅቱ ‹‹አደጋው በደረሰ ጊዜ የአደጋውን መጠን መቀነስ አልቻለም፣ ከአደጋው በኋላ የተገኘውን አስከሬን አያያዝ፣ የቀብር አፈጻጸም የአንድ ዜጋ ሰብዓዊና ህጋዊ ክብርን የጠበቀ አልነበረም፣ ቀብራቸው የተፈፀመው በጅምላ ነው፣ ያለማንም ፈቃድ ቀብራቸው ሲፈፀም የቤተሰቦች በቀብሩ ላይ እንዲገኙ አልተደረገም፣ በአደጋው ወገኖቻቸው የሞቱባቸው ቤተሰቦች ያለጡዋሪ ቀባሪ የቀሩ ወላጆች ያለወላጅ እና ረዳት የተበተኑ ቤተሰቦች ተገቢ ድጋፍ አልተደረገላቸውም። ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች የህክምና ወጪ አልተከፈላቸውም። ይህ ህግ ባለበት ሀገር ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅ አይደለም›› ሲሉ አማረዋል።

‹‹በዚህ አደጋ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከአንድ እስከ አራት ሰው ህይወት ከፍሎበታል። ነገር ግን የሚያሳዝነው ፍትህ ማጣታችን ብቻም አይደለም የምርመራ ጉዳዩን የያዘው የሰሜን ሸዋ ወረጃርሶ ፖሊስ የሟቾችን ንብረት እንዳንጠይቅ አድርጐናል ›› ሲሉ ገልፀዋል።

በፓናል ውይይቱ ላይ በሟቾቹ መካነ መቀበር ላይ ስለሚሰራው መታሰቢያ ተነስቶ ‹‹አደጋውን ያደረሰው የስካይ ባስ ኃላፊዎች መጀመሪያ ላይ መግባባት ላይ ቢደረስም ቆይቶ 247000 ብር አልችልም ይልቁንም ባቡር ጣቢያ አካባቢ በፈረሰብን የመጋዘን ፍራሽ 42 መቀመጫ ያለው አንድ ክፍል ልስራ›› በማለቱ መግባባት ላይ እንዳልደረሱ ተነግሯል። ስለዚህም የሟች ቤተሰቦችና ተጎጂዎች በራሳችን አቅምና በበጎ ፍቃደኞች እርዳታ ቀብራቸው በተፈፀመበት ቤተክርስቲያን የመታሰቢያና መገልገያ አዳራሽ እንዲሁም አደጋው በደረሰበት በአባይ መግቢያና መውጫ ላይ የሚያስጠነቅቅ የመንገድ ምልክት ለማሰራት መወሰናቸው አስታውቀዋል።

# <<እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ>>

ማቴ.ወንጌል ም.23 ቁ.4

በመንግስት ዙፋን ላይ ራሳቸውን በከፍታ ያስቀመጡ ብዙ ግለሰቦች አሉ:: ከዋናዎቹ አገር መሪዎች ጀምሮ እስከታች ያሉ አስተዳዳሪዎቻችንን ጨምሮ ማለት ነው:: እነዚህ ግለሰቦች በየደረጃቸው የሚገባቸውን ሳይሆን የማይገባቸውን መንበር በመቆናጠጣቸው ምክንያት ከሁሉ የበለጡ እየመሰላቸው ለራሳቸው መታበይን አስተምረዋል:: የመረጣቸውን ህዝብ ንቀዋል:: ያከበራቸውንም ፈጣሪ ረስተዋል:: ከፍ ሲሉ ከከፍታው አምላክ ጋር ለራሳቸው የሰጡት ግምት ዝቅ እንዳይሉ አይናቸውን ጋርዶባቸዋል:: በተሰጣቸው ህዝብን የማገልገል ኃላፊነት ስም እራሳቸው ተገልግለውብታል:: እራሳቸው ህግ ያወጣሉ፣ ይነጋገራሉ፣ ይጨምራሉ፣ ይቀንሳሉ፣ ያፀድቃሉ ሲያሻቸው ደግሞ ያወጧቸውን ደንቦች እና ህግጋት ይሽራሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው አይነት ጥንተ እስራኤልን ቁም ስቅሏን ያበሏት እንደነበሩት ፃፎችና ፈሪሳውያን መስለዋል:: ፃፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ላይ በመቀመጣቸው ብቻ በህዝቡ ላይ በደልን ያከታትሉበት ነበር:: ህዝቡ በእነዚህ መሪዎች እጅግ የተማረረበት ጊዜ ነበር:: በስተመጨረሻም ለህዝቡ የመፅናኛ ቃል ከእየሱስ ክርስቶስ መጣ:: በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ቁጥር 1-8 እየሱስ ለህዝቡ ፈሪሳውያንን አስመልክቶ የሰበካቸው የስብከት ክፍል እንዲህ ይላል::

**‹‹በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፡- ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል:: ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፤ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉምና እንደ ስራቸው አታድርጉ:: ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፡ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም:: ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ስለዚህ አሸንክታባቸው ያሰፋሉ፡ ዘርፋንም ያስረዝማሉ፡ በምሳም የከበሬታ ስፍራ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር በገበያም ሰላምታና፡- መምህር ሆይ መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ››** ይላል ቅዱስ ቃሉ፡-

አዎ የዚያን ጊዜው በሙሴ መንበር ላይ የተቀመጡ ፈሪሳውያን አይነት አሁን በእኛም አገር አሉ:: የፈለጉትን ያደርጋሉ:: ለትዕዛዞቻቸው ከልካይ የለባቸውም:: የማንንም ተናጋሪነትም አይሹም:: ትችትን እንደጦር ይፈራሉ:: በእጅጉ ይፀየፉማል:: ክርስቶስ ስለፈሪሳውያኑ እንዳለው ‹‹እየተናገሩ አያደርጉም›› እንደተባሉት ጻፎች ሁሉ የእኛዎችም በዙፋኑ የተቀመጡት የአሁኖቹ ፈሪሳውያን በኃላፊነት ለማስተዳደር የተረከቡት ህዝብ ቃል ከመግባትና በተስፋ ከማንጠልጠል ውጭ አንዳችም እርባና ያለው ነገር አላደረጉልንም:: በቀን ሶስቴ ህዝቡ እንዲበላ በአጭር ጊዜ ውስጥ እናደርጋለን አሉ:: ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነን የቀየስነው አዋጭ የልማታችን እቅዳችን ነው የሚል ነበር:: እንዲህና እንዲያ እያሉ ትርክት ከማቅረብ ውጭ በቀን ሶስቴ መብላቱ ቀርቶብን እየተባባሰ፣ እየከፋ የመጣውን የኑሮ ውድነት እንኳን ሊያረጋጉልን አልቻሉም:: ከግድቦቻችን በሚመነጩ የኃይል አቅርቦቶች መስፋፋት ምክንያት መብራት ከራሳችን ተርፎን ለጐረቤት አገራትም እናዳርሳለን አሉ:: ይህንንም ውጤት በአጭር ጊዜ ታዩታላችሁ አሉን:: አንዱ ግድብ ተሰርቶ በተመረቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ አገልግሎት መስጠት ሲሳነው አይተን እንዳላየ አሳለፍን፣ ሌላው ትልቅ ግድብ ደግሞ የውጭ አገራት ለጋሾች የገንዘብ እርዳታ በመከልከላቸው ምክንያት ተመርቆ ለማየት ሌላ ብዙ አመታትን ለመጠበቅ እንገደዳለን:: ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ይከሰት የነበረውና የአገራችን መገለጫዎች ናቸው የሚባሉትን ችጋርና ስደት ከእንግዲህ ወዲህ በኢትዮጵያ ምድር አይኖሩም አሉን:: በአሉን ቀረ እንጂ:: በታሪካችን በየትኛውም አገዛዝ አይተነው የማናውቀውን የሰዎች ስደት በዚህ ዘመን አየን:: ኢትዮጵያ ውስጥ ከመኖር ህዝቡ የበረሃ እባብ፣ የባህር አሣንና የሌሎች አገራት ዜጎች ባሪያ መሆንን መረጠ:: ጦርነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዳግም ላይመለስ ጓዙን ጠቅልሎ ተሸኘ ተባለ:: የምናየው የተነገረንን እውነት ሳይሆን ተቃራኒውን ሆነ:: ወታደሮቻችን መቋጫ በሌለው የቀንዱ አገራት ግጭት እየተንከራተቱ ሰላም ለማስከበር በሚል ተልዕኮ፣ ትርፉ ለማይታወቅ ኪሳራው ለበለጠ ጦርነት ውድ ህይወታቸውን ገበሩ:: ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በእጅ ላይ እንዳሉ የተለያዩ ጣቶች ህብር ፈጥረው በፍቅርና በሰላም የሚኖሩባትን ፌዴራላዊ ስርዓት ዘረጋን አሉ:: ምንድን ነው የሆነው ግን? ከጊዜ ወደ ጊዜ የፌዴራል ስርዓቱ ከብሔራዊ አንድነታችን ይልቅ በክልል ማንነታችን ላይ ትኩረት በመስጠቱ ምክንያት እርስ በርሳችን ማን ነህ? ምንድን ነህ? እዚህ ምን ታደርጋለህ? ለምን ወደ ክልላችን መጣህ? አሁንስ ወዴት ነህ? መባባል ጀመርን:: የአንድ አገር ዜጐች ነን ብለን የምናስብ ትውልዶች ከጨቋኙ ነህ ወይንስ ከተጨቋኙ ወገን ነህ? መባባል ጀመርን:: በጣም ብዙ ነገሮችን እያነሳን ያሉንን ነገር ግን ሊያደርጉልን ያልቻሏቸውን ቀቢፅ ተስፋዎች መዘርዘር በተቻለ ነበር:: ህዝቡም ይህንን ሁሉ መከራ እያወቀ እንዳላወቀ ሆነ:: በተደጋጋሚ ገገርዎቻችን ያወጧቸውን አፋኝ ህጐች ሁሉ አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ፣ ተበድሎ እንዳልተበደለ ዝም አለ:: ዝምታው ፍርሃት አልነበረም:: ያለማወቅም አይደለም:: እንዲህም ተደርጎ ከታሰበ ስህተት ነው:: ክርስቶስ ለእስራኤላውያን ስለፈሪሳውያን የነገራቸውን ምክር በማስተዋል እንጂ:: ‹‹ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፡ ጠብቁትም ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ›› ይላልና ነው:: ጠቢቡ ሰለሞን እንዳለው ‹‹ለሁሉም ጊዜ አለው››::

ከባድና አስቸጋሪ ሸክም በላያችን ላይ ጭነዋል:: ወደፊት በአገራችን ህልውና፣ በአብሮነታችን ላይ ጥያቄ ምልክት በማስቀመጥ ለማለፍ እየጣሩ ነው:: ብሔርን ከብሔር፣ ክልል ከክልል፣ ኃይማኖትን ከኃይማኖት ጋር በጥርጣሬ አይን እንዲተያዩ የተለያዩ ሸረባዎችን በተግባር በሚታይ መልኩ ቆምረዋል:: እነዚህ ሁሉ መከራዎች ግን በገዢዎቹ ደጃፍ ላይ እንኳንስ አልደረሱም:: በስልጣን ላይ እስካሉ ድረስም አይደርሱምም:: ርሃብ እና ቸነፈሩን አያውቁትም፣ ስደት የሚባል ጦስ እጣ ፈንታቸው አይደለም፣ በእርስ በርስ ግጭት ምክንያት በሚደርሰው የንብረት ውድመት፣ የቤተሰብ መፈናቀልና መበታተን ተጠቂ አይደሉም:: አንዳችም እስከዛሬ ባደረጓቸው ነገሮች ፀፀት የለባቸውም:: ከማስፈራራትና ከስድብ ውጭ አንደበታቸው መልካም ነገርን አያውቅም:: በሰሩት ስራ አንዳችም ቀን ተፀፅተው፣ ይቅርታ ጠይቀው አያውቁም:: ሁሉንም ነገር በአደባባይ ከማድረግ አይቆጠቡም:: መፅሐፉ እንደሚለው ‹‹ለሰውም እንዲታይ ስራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ:: ስለዚህ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ ዘርፋንም ያስረዝማሉ፣ በምሳም የከበሬታ ስፍራ፣ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር በገበያም ሰላምታና መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ›› እንደሚል:: የሰሩት ክፉ ስራ በፍፁም ከመድረኩ አይሸሽጋቸውም:: ፎቶአቸውን ባደባባይ ከመለጠፍ አይቦዝኑም:: እኛ ከሌለን ይቺ አገር ፈራሽ ናት የሚለው ማስፈራሪያቸው የየዕለት ነው:: መሪ መሆናቸው ህዝቡ እንዲያውቅላቸው ብቻም ሳይሆን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከፍ ከፍ እንዲያደርጋቸው ይሻሉ:: መሪዎቻችን ያላወቁት ነገር ቢኖር ከእነርሱ በብዙ የተሻሉት ከፖለቲካው በመራቃቸው ምክንያት ሊገዟቸው በሚችሏቸው ሰዎች ተገዝተው እያገለገሉዋቸው መሆኑን ነው:: መፅሐፉ እንደሚለው ‹‹እራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፣ ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል›› የሚለው ትእዛዝ እስኪፈፀም ድረስ ያዘዙንን ሁሉ እናደርጋለን::


## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

### የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮግራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል:: ለትግሉ ስኬትም የእርስዎ ድጋፍ ወሳኝ ነው::

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ግንቦት 25 ቀን 2004 ዓ.ም የሚካሄድ የራት ፕሮግራም አዘጋጅቶአል:: ለመግቢያም ባለ 1,000፣ ባለ 500 እና ባለ 300 ብር ካርዶችን አዘጋጅቶ በመሸጥ ላይ ይገኛል:: በዕለቱም ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ::

የራት ዝግጅት የሚካሄድበትን ሆቴል ግንቦት 13 ቀን በሚወጣው ፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣ ላይ እንገልጻለን:: በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች ሀገር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች አማካኝነት ካርዱን መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን::

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት፡- የቢሮ ስ.ቁ 0118-400811 ወይም በሞባይል፡- 0911-618434 ይደውሉ:: ኢ-ሜል andientfinance@yahoo.com or andinet@andinet.org ላይ ይጠቀሙ::

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት መመስረት፤ ሁላችንም ካርዱን በመግዛት የድርሻችንን እንወጣ!!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)፤ የሂሳብ ቁጥር፡- 510 ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ